ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሂማኒቲስ ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# የመምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር በደቡብ ወሎ የተንታና መቅደላ ወረዳ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች በ9ኛ እና በ10ኛ ክፍል መምህራን ተተኳሪነት

በ

አስማረ ዳምጠው አመኑ

ነሐሴ 2013 ዓ.ም

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሂማኒቲ ስኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# የመምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር በደቡብ ወሎ የተንታና መቅደላ ወረዳ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች በ9ኛ እና በ10ኛ ክፍል መምህራን ተተኳሪነት

ለትምህርት ማስተር ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ

በ

አስማረ ዳምጠው አመኑ

አማካሪ

ዶ/ር ለማ ንጋቱ /ፒ ኤች ዲ/

ረዳት አማካሪ

ኤባ ቴሬሳ /ዶ/ር/

ነሐሴ 2013 ዓ.ም

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ጅማ ዩኒቨርስቲ

የሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

የኢት/ያ ቋንቋዎችና ሥን ጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳትና ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር በደቡብ ወሎ ት/ቤቶች በታንታና መቅደላ 2ኛ ደረጃ ት/ቤች በ9ኛ ና 10ኛ ክፍል መምህራን ተተኳሪነት

ለሁለተኛ ዲግሪ ማሚያነት የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ

ሀ/ በፈታች ቦርድ አባላት የቀረበ ማረጋገጫ ይህ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር በደቡብ ወሎ ት/ቤቶች በተንታና መቅደላ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች በ9ና በ10ኛ ክፍል መምህራን ተተካሪነት በሚል ርዕሰ ለ2ኛ ደግሪ ማሚያ አስማረ ደምጠው ያቀረበው ጥናት የዩኒቨርስቲውን የውጥኑን መስፈርት ስለማሟላቱ በፈታኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል።

የፈታኝ ቦርድ አባላት

| | | |
|---|---|---|
| የአማካሪ ስም | ፊርማ | ቀን |
| የውስጥ ፈታኝ ስም | ፊርማ | ቀን |
| የውጭ ፈታኝ ስም | ፊርማ | ቀን |

## ለ በአጥኚው የቀረበ ማረጋገጫ

ይህ የአማኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ጥናት በሚል ርዕስ በጅማ ዩኒቨርስቲ የሶሻል ሳይንስና ሂውማኒትስ ኮሌጅ የኢትዩጱያ ቋንቋዎችና ስነ- ጽሁፍ የአማርኛ ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረብብት ጥናት ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ የራስ ወጥ ስራ መሆኑንና የተጠቀምኩባቸውን ድርሰናት በትክክል ዋቢዎች የሆኑና ጅማ ዩኒቨርስቲም የጥናቱ ህጋዊ ባለቤትነት ያለው መሆኑን በፊርማየ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም አስማረ ዳምጠው

ፊርማ -----------------------------------

ቀን-------------------------------------

# ምስጋና

አስጀምረህ ለመፈፀም ያበቃኸኝ የድንግል ልጅ ለአንተ ምስጋና እንጂ ምን ይሰጥሃል፡፡

በዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ሥራዩ ውስጥ ከመጀመሪያው አንስቶ እስከአሁኑ ድረስ ሙያዊ የሆነ ድጋፍ በመስጠት የጥናት ሥራዬ ከዚህ ደረጃ እንድደርስ አስፈላጊውን ሁሉ በማድረግ ባለመታከት ውድ ጊዜያቸውን የሰጡኝ አማካሪዎት ለማንጋቱ /ዶ/ር/ እና ኤላ ቴሬሳ /ዶ/ር/ የማቀርብላቸው ምስግና እጅጉን ላቅ ያለ ነው፡፡

በትምህርት ቆይታዬም ሆነ በጥናታዊ ጽሁፍ ተግባሬ ውስጥ የብርታት ዘንግ በመሆን ያልተነጠለችኝ ባለቤቴ ወ/ሮ አሳመን አረጋ እና ልጆቼ እንዲሁም አክባሬ ቤተሰቦቼ እናንተ በልቤ ውስጥ የተለየ ቦታ አላችሁ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ጥናታዊ ጽሁፍን በማጠናቀቅ ለወ/ሮ ሐረጓ ስለሺንና ለዚህ እንዲበቃ የረዳችሁኝ የአስፈወሰን ት/ቤት መምህራንና ሠራተኞች ተጠኝዎቼ ጋር ለመሰረት የበኩላችሁን የደገፋችሁኝ የሁሉም ት/ቤት አመራሮች እና ደጋፍ /ተባባሪ/ የጥናት አጋሬ የጉድኝት ሱፐርቫይዘርን አመሰግናለሁ፡፡

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በደቡብ ወሎ የተንታና መቅደላ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ የሚከተሏቸውን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች መመርመር ነው፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎች በደቡብ ወሎ የተንታና መቅደላ ወረዳ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች የ9ኛ ና 10ኛ ክፍል መምህራን የሆኑትን 31 መምህራን የአስፋወሰን ፣ የአጅባር ፣ የደበቅ ፣ የወርጠጀና የመቅደላ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ናቸው፡፡ በጥናቱ ውስጥ ለመረጃ መሰብሰቢያነት በሥራ ላይ የዋሉት መሳሪያዎች ምልከታና ቃለ መጠይቅ ናቸው፡፡ የጥናቱ ዋነኛ የመረጃ ማሰብሰቢያ መሳሪያ ምልከታ ሲሆን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበር ደረጃዎችን በተመለከተ ለቅድመ ንባብ ፣ ለሂደታዊ ንባብ /ጊዜ ንባብ/ እና ድህረ ንባብ አተገባበርን ምልከታ የሚረዱ ቸክሊስት በማዘጋጀት 31ዱም ተጠኝ መምህራን ለእያንዳንዳቸው ሁለት ክ/ጊዜ በድምሩ 62 ክፍለ ጊዜ የሽፈነ ምልከታዎች ተከናውነው መረጃው በአይነታዊ ዘዴ በመቸኛ ተሰልቶ ተከናውኗል፡፡ የምልከታ መረጃውን መሠረት በማድረግ የተሰበሰበውን መረጃ ለማጠናከረና መምህራን በአተገባበሩ ሂደት ያላቸውን ተሳትፏዊ ግንዛቤ ያለበትን ሁኔታ በማሳየት የሚያስችሉ በ3ቱም የአተገባበር ደረጃዎች ላይ የተመረኮዙ ከ20 በላይ የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች ተዘጋጅተው በምልከታ ጊዜ በታዩ የአተገባበር ሁኔታ አመላካች የሆኑ ዝቅተኛ አተገባበር ላይ የሚገኙ 6 መምህራን በአላቸው ደረጃ ተለይተው ከአጠቃላዩ የተጠኝ ናሙናዎች የተመጣጠነ ውክልና ባላቸው የመምህራን ቁጥር ላይ መረጃ የተሰበሰበ ሲሆን በዚህም ተጽእኖ ሊያደርሱ የሚችሉ ተለወጦዎች የሚያሳዩትን ሁኔታ ማየት ተችሏል፡፡ በምልከታና ቃለ መጠይቁ የመምህራኑ የአተገባበር ደረጃ የተለያየ ቢሆንም በ3ቱም የአተገባበር ደረጃዎች ማለት በቅድመንባብ ፣ በጊዜ/ሂደታዊ/ንባብና ድህረ ንባብ የአተገባበር ብልሃቶች የመምህራን የክፍል ውስጥ አተገባበር ያለበት ደረጃ በአማካይ በቅድመ ንባብ ጊዜ ዝቅተኛና መረጃ ያልተተገበሩ 74.8 ሲሆኑ 25.2 ከፍተኛና መካከለኛ ሆኖ የመምህራን አተገባበር ደረጃ ዝቅብሎ ታይቷል፡፡ በጊዜ ንባብ /ሂደታዊ ንባብ ደግሞ 77.% ዝቅተኛና ጭራሽ ያልተተገበረ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም ሂደታዊ ንባብ በአተገባበር የአንብቦ መረዳት ብልሃት ያልተሳካ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ የቀጣዩ የድህረ ንባብ የመምህራን አተገባበር በተነፃፃሪነት ሲታይ ከሁለቱ ሻል ያለ ነገር ግን ከችግር ውስጥ ያለ መሆኑ በአማካይ 60.06 ዝቅተኛና ጭረሻ ያልተተገበረ ተግባር ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመምህራን የአንብቦ መረዳት አተገባበር ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ተለወጠዎች /ሁኔታዎች/ በጥቅም ላይ ከዋሉት ምልከታና ቃለ መጠይቅ በተገኘው መረጃ መሠረት ተከታታይነት የለው የመምህራን ሙያዊ የሥራ ላይ ሥልጠና አለማግኘት ፣ የመምህራን የርስ በርስ ልምድ ልውውጥ የተነሳሽነት ማነስ ጎልተው የታዩ ችግሮች ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ይህንኑ መሠረት በማድረግ ጥናቱ ለወደፊቱ ይጠቅማሉ የሚል በችግሮቹ መፍቻ የመፍትሄ ገሳቦች ጠቁሟል፡፡

# ማውጫ

ርዕስ ገፅ


ምዕራፍአንድ ... 1

መግቢያ ... 1

1.1 የጥናቱዳራ ... 1

1.2 የጥናቱአነሳሽምክንያት ... 4

1.2 የጥናቱዓላማ ... 7

1.3.1 ንዑሳንዓላማዎች፦ ... 7

1.4የጥናቱአስፈላጊነት ... 7

1.5የጥናቱወሰን ... 8

1.6 የጥናቱውስንነት ... 8

1.7 ቁልፍቃላትናጽንሰሃሳቦች ... 9

ምዕራፍሁለት ... 10

ክለሳድርሳናት ... 10

2.1 ጽንሰ ሀሳባዊ ቅኝት ... 10

2.1.1 የአንብቦ መረዳት ክሂል ምንነት ... 10

2.2 የአንብቦመረዳትክሂልጠቀሜታ ... 12

2.3 የአንብቦመረዳትብላሀቶችአስፈላጊነት ... 13

2.4 የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች የክፍል ዉስጥ አተገባበር (ቅድመ ንባብ፤ በንባብ ጊዜ እና በድህረ ንባብ ) ... 16

2.5 በአንብቦመረዳትብልሀቶች /ተግባራትየክፍልዉስጥትግበራተጽዕኖየሚያሳድሩሁኔታዎች ... 22

2.5.1 የተማሪዎችተነሳሽነት ... 22

2.5.2 በአንድክፍልዉስጥየሚገኙተማሪዎችብዛት ... 22

2.5.3 የተማሪዎችቅድመእዉቀትእናየቋንቋችሎታመለያየት ... 22

2.5.4 አቀላጥፎአለማንበብ ... 23

2.5.5 ወቅታዊ ስልጠና እና የልምድ ልዉዉጥ ... 23

2.1.3. የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች አስፈላጊነት ... 24

2.1.4. የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ... 25

2.1.5. በአንብቦ መረዳት ብልሀቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ላይ ተፅዕኖ ሁኔታዎች /ተላወጦዎች/ ... 26

2.3 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ... 26

□□□□ □□□ ... 28

□□□□ □□□ □□□□□ .......... 28
3.1 የጥናቱ ስልት .......... 28
3.2 የጥናቱ ተሳታፊዎች አመራረጥ .......... 28
3.3 የመምህራን ናሙና አመራረጥ ዘዴ .......... 29
3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች .......... 29
3.4.1 ምልከታ .......... 30
3.3.2 ቃለ መጠይቅ .......... 30
3.4 የአጠናን ሂደት .......... 31
3.5የመረጃ አተናተን .......... 32
ምዕራፍ አራት ፡- .......... 33
የውጤት ትንተና እና ማብራሪያ .......... 33
4.1 የውጤት ትንተና .......... 33
4.1.1 የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ትንታኔ .......... 33
ሰንጠረዥ 4.2 የጥናቱ ተሳታፊ መምህራን የቅድመ ንባብ ብልሃቶች ክፍል ውስጥ አተገባበር .... 34
ሰንጠረዝ 4.3 የጥናቱ ተሳታፊ መምህራን የምንባብ ጊዜ ብልሃቶች ክፍል ውስጥ አተገባባር ...... 37
ሰንጠረዥ 4.4 የጥናቱ ተሳታፊ መምህራን የድህረ ንባብ ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር.... 40
4.1.2 የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ትንታኔ .......... 43
4.1.2.1 የቅድመ ንባብ ብልሀቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ትንታኔ .......... 44
4.1.2.2 የንባብ ጊዜ ብልሀቶች የክፍል ዉስጥ አተገባበር ግንዛቤ .......... 46
4.1.2.3 የድህረ ንባብ ብልሀቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ትንታኔ .......... 48
4.2 የውጤት ማብራሪያ .......... 53
ምዕራፍ አምስት፡- .......... 57
ማጠቃለያ መደምደሚያና መፍትሄ .......... 57
5.1 ማጠቃለያ .......... 57
5.2 መደምደሚያ .......... 58
5.3 መፍትሄ .......... 59
ዋቢ መፅሐፍት .......... 60
ሰንጠረዥ 4.1 የጥናቱ ተሳታፊ መምህራን የቅድመ ንባብ ብልሃቶች የክፍል ዉስጥ አተገባበር.. 66
ሰንጠረዥ 4.2 የጥናቱ ተሳታፊ መምህራን የንባብ ጊዜ ብልሃት አተገባበር .......... 67
ሰንጠረዥ 4.3 የጥናቱ ተሳታፊዎች የድህረ ንባብ ብልሃት አተገባበር .......... 68
አባሪ ለ፡-የምልከታ ማጠቃለያ መረጃ .......... 69
የንባብ ጊዜ ብልሀቶች .......... 75
ድህረ ንባብ ተግባራት .......... 81

አባሪ ሐ - ቃለ መጠይቅ....87
ቅድመንባብ ብልሀቶችን የተመለከቱ ጥያቄዎች ....87
የንባብ ጊዜ ብልሀቶችን የተመለከቱ ጥያቄዎች ....88
ድህረንባብ ብልሀቶችን የተመለከቱ ጥያቄዎች ....88

## ምዕራፍአንድ

## መግቢያ

### 1.1 የጥናቱዳራ

የማንበብን ምንነት አስመልክቶ የተለያዩ የቋንቋ ምሁራን የተለያ ብያኔዎችን ይሰጣሉ፡፡ ማንበብ ከመቀበያ ክሂሎች አንዱ ነው፡፡ የዚህ ክሂል መዳበር ተማሪዎች በሚማሩበት ቋንቋ በወጉ መጠቀም እንዲችሉ የቋንቋ ግብአቶችን (language inputs) ለመሰብሰብ ያስችላቸዋል፡፡ ማንበብ አንድን ፅሁፍ የመረዳት የመተርጎም ሂደት ቢሆንም በጣም ውስብስብ ተግባር ነው፡፡ የማንበብ ትምህርት አካላዊ አዕምሮአዊን ብዙውን ጊዜ አካላዊ ምላሾችን የሚጠይቅ ነው በማለት (Pihuja 2002) ይገልፃሉ፡፡የማንበብ ትምህርት በትምህርትነት የቀረበውን የቋንቋ ፊደላት ከመለየት አንስቶ የቀደመ እውቀትና ግላዊ ምናብ በመጠቀም አንድን ፅሁፍ እስከ መረዳት ድረስ ያለውን ውስብስብ አዕምሯዊ ሂደት ይመለከታል፡፡(ማረው አለሙ እና ሰፋ መካ(1999፡103)) በሙያ መስክ ማስተማር በተባለ ሞጁል ላይ አብራርተውታል፡፡ ስለዚህም ተማሪዎች ንባብ የሚማሩት በማንበብ ቢሆንም ትምህርቱ የተማሪዎቹን የችሎታ ደረጃ ተከትሎ በተለያ የአቀራረብ ስልት መቅረብ ይኖርበታል፡፡ መምህራን የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችን መጠቀምም ይኖርባቸዋል፡፡ ተማሪዎቻቸውን መምህራን ማስተማር እንዲችሉ የተለያዩ የንባብ ትምህርት አቀራረቦችን ተግብረው ተማሪዎቻቸው ከቅድመ ንባብ፣ በንባብ ላይና በድህረ ንባብ ተግባራት መካከል ያሉትን ልዩነቶች በትክክል ተረድተውና ተጠቅመው ተማሪዎቹን የዚህ ክሂል ተጠቃሚ እንዲያደርጉ አዕምሯዊ ግንዛቤያዊ ክሂሎች የሚያመጡትን ችሎታዎች አዳብረው በአንብቦ መረዳት ችሎታ መልመጃዎችን እየመዘኑ ያሉበት ደረጃ በማወቅ ችሎታቸውን ከፍ የማድረግ ስራ ከመምህራኑ ይጠበቃል፡፡ ለዚህም የመምህራን የአንብቦ መረዳት የማስተማር ተግባር በክፍል ውስጥ ያለውን አተገባበር ማየት ያሻል፡፡

በየዘመኑ የተነሱ የአንብቦ መረዳት አቀራረቦች ሆኑ ምርምሮች አተገባበራቸውና ስልታቸው ቢለያይም በጋራ የሚያተኩሩት ከማንበብ ትርጉም የመፍጠር ችሎታ ላይ ነው፡፡ የማንበብ መሠረታዊ ትኩረትም በየደረጃዉ ትርጉም መገንባት ነው፡፡ (Grabe, 1991: Williams, 1984, Williams, Taylor, & Ganger,1981):: ይሁን እንጅ በማንበብ ሂደት ትርጉም መፍጠር የሚለው ፅንሰ ሀሳብ ለረጅም ጊዜ እጅግ አሻሚ ሆኖ ቆይቷል፡፡

በአተገባበሩ ሂደት የተለያዩ የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች ቢኖሩም ቁልፉን ድርሻ የሚይዘው የአንባቢውን የቀድሞ እውቀት በመቀስቀስአዲስ ከሚቀርበው ዕውቀት ጋር ማገናኘት ነው Conley(1992)፣ Adjudhi(2006):: የቀደመ እውቀትን መጠቀም መሰረቱ የ“ ስኬማ” ንድፈ ሀሳብ (schema theory) ይገልፃል፡፡ እንደ Adjudhi (2006) አገላለፅ ይህ ንድፈ ሀሳብ የሚያተኩረው የቀደመ እውቀት ላይ መሆኑ የተዋወቀው በ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአማኑኤል ካንት አማካይነት ነው፡፡

Broerን (1999)ን ዋቢ አድርገው Adjudhi (2003) እንደገለፁት በርትሌት የተባሉ የመስኩ ባለ ሙያ እስከ 1920 ድረስ የስኬማ ንድፈ ሀሳብን በማጎልበቱ በ1970ዎቹና በ1980ዎቹ ውስጥ በአዕምሯዊ ሳይኮሎጅ (cognitive psychology) እና በአዕምሯዊ ሳይንስ( cognitive science) ላይ የራሱ የሆነ ፋይዳ እንዳለው ይገልፃሉ፡፡ የተለያዩ የቋንቋው ምሁራን የተለያዩ ጥናቶችና ግኝቶች መሰረት ያደረገ መፅሀፋም Barttlet (1932) መፃፍ የስኬታማ ንድፈ ሀሳብ የአንድ ነገር ቅርፅ የሚይዘው በሰዎች ግምት ወይም የቀደመ እውቀት እንደሆነና ይህም የቀደመ እውቀት የሚመጣው በአዕምሮ ውስጥ የተለየ "ስኬማቲክ" መስክ ነው ሲሉ የዚህ ንድፈ ሀሳብ ሁነት Barttlet (1932) ይገልፃሉ፡፡ ማንኛውም ሰው ቢሆንም የቀደመ እውቀት አለው፡፡ በክፍል ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎችም ስለሚያነቡት ፅሁፍ የቀደመ እውቀት አላቸው፡፡ ስለሆነም ይህንን የቀደመ እውቀት በመቀስቀስና በመገንባት አዲስ ከሚያገኙት ዕውቀት ጋር እንዲያስተሳስሩት የሚያስችሏቸውን ብልሃቶች መሰረት አድርገው እንዲያነቡ ማድረግ የመምህሩን ድርሻ ይሆናል በማለት Adjudhi(2006) ይገልፃሉ፡፡

የአንብቦ መረዳት ጉዳይ በዳራዊ ዕውቀትና አሁን በሚነበበው ፅሁፍ ውስጥ መካከል አንባቢው የሚያደርገው መስተጋብራዊ ሂደት ነው(Alcualy 2012)፡፡ ስለሚነበበው ፅሁፍ የተሻለ ዳራዊ ዕውቀት ያላቸው ተማሪዎች ቁንፅል ዳራዊ እውቀት ካላቸው ተማሪዎች በተሻለ መልኩ አንብበው መረዳታቸውን ጥናቶች ይገልፃሉ፡፡

ይህንኑ ሀሳብ Conley (1992)ሲገልፁት ስለሚነበበው ፅሁፍ ተጨማሪ ዳራዊ እውቀት ያላቸው አንባቢዎች በሚያነቡበት ጊዜ ትኩረት የሚያደርጉት ጠቃሚና ሰፊ ፅንሰ ሀሳብ ላይ ነው፡፡ ይህም የፅሁፉን ጭብጥ በፍጥነት እንዲረዱና ጠቃሚ የሆኑ ዝርዝር ጉዳዮችንም እንዲገነዘቡ ይረዳሉ፡፡ አንብቦ መረዳት በተከታታይ በሚደረግ ልምምድ ደረጃ በደረጃ እየዳበረ የሚሄድ ክሂል ነው፡፡

በተመሳሳይ Anderson (1999)ን ዋቢ አድረገው G.Negga (2007) ሲገልፁ የአንብቦ መረዳት ትምህርት ተቀባይ ወይም ተመልካች የሚሆኑበት ሂደት አይደለም፡፡ ይልቁንም የቀደመ ዕውቀታቸውን በመጠቀም ከሚነበበው ፅሁፍ ጋር በማገናኘት ንቁ ተሳትፎ የሚያደርጉበት ነው ይላሉ፡፡ ከዚህ ጥናታዊ ውጤት አገላለፅ የምንረዳው በአንብቦ መረዳት ሂደት ተማሪዎች የቀደመ ዕውቀታቸውን ተጠቅመው አዲስ የቀረበውን ንባብ ማንበብና መረዳት መቻል በአዕምሮ ውስጥ በፍጥነት የሚከወን የላቀ ክሂል መሆኑንና ለተደራጀ የዕውቀት ሽግግር ከፍተኛ ጥቅም ያለው መሆኑን ነው፡፡

በአጠቃላይ ስለ አንብቦ መረዳት ትምህርት ሲታሰብ ከመምህሩን የሚጠበቀው ተግባር ተማሪዎችን ንቁ አንባቢ እንዲሆኑ በማስተማር ዘዴያቸው ውስጥ የአንብቦ መረዳት ብልሀቶችን እንዲያዩና መቼ እንደሚጠቀሙባቸው እያሰላሰሉና እየተገበሩ በማሳየት አርዓያ በመሆን በድጋፍ እያለማመዱ በሂደት ተማሪዎች ራሳቸውን ችለው እንዲተገብሩ ማድረግ ነው፡፡ የንባብ ክንዋኔዎችን የተማሪዎችን የንባብ ችሎታ ለመለካትም እንደሚያስችሉ በዚህ ረገድ ተከታታይነት ባለው ሁኔታ ደረጃ በደረጃ መፈፀም ያለባቸው ተግባርት መኖራቸውና የተለያየ የክፍል ውስጥ አተገባበር እንዳለ(Ur1996) ይገልፃሉ፡፡ ከዚህ የምንረዳው ደግሞ

ተማሪዎቻቸውን መምህራኑ የተለያዩ የንባብ ክንዋኔዎችን በመስጠት ማገዝ መደገፍና የክሂሉ ተጠቃሚ ማድረግ ያለባቸው መሆኑን ነው፡፡

የተለያዩ የዘርፉ ባለሙያዎች ከላይ የተገለፁትን የመምህራን ሚና ለማጎልበት የሚረዱ የማስተማር ብልሀቶችን ይጠቅማሉ ማለት ነው፡፡ በዚህ ረገድ (Ur 1996) መምህራን አንብቦ መረዳትን በበለጠእንዲረዱት የሚያከናውኗቸው የአተገባበር ደረጃዎች እንዳሉ የቅደመ ንባብ ጥያቄ መስጠት፣ ርዕስ መስጠት፣ አንተው ራስህ ስራው ጥያቄዎች፣ ማጠቃለያ መስጠት፣መደምደም ፣ ክፍተት ያለው ፅሁፍ መሙላት ፣ ስህተት ማውጣት፣ ማነፃፀር ምላሽ መስጠትና ይዘቱን በሌላ መልክ ማቅረብ በሚል የማስተማር ተግባሩን በክፍል ውስጥ መተግበር ያለባቸው መሆኑን ያብራራሉ፡፡

በዚህ የአተገባበር ቅደም ተከተል መሰረት መምህራኑ የሚያከናውኑት የክፍል ውስጥ መማር ማስተማር በሁለትዮሽ በመምህሩና በተማሪው መካከል በውጤታማነት ሲከናወን የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ክሂልየሚያድግ መሆኑን ከመምህሩና ከተማሪው መጽሀፍት የሚገኙ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ስለሆነም መምህራን እነዚህን ብልሀቶች ተጠቅመው ማስተማራቸው የመምህራንን አርዓያነት ደጋፊ መሆንን ያሳያል፡፡

መምህራን ተማሪዎቹ በዚህ የክፍል ደረጃ ከፍ ወዳለ የዕውቀት ደረጃ የሚያደርሳቸውን "ለመማር ማንበብ" የሚደርሱበት በመሆኑ ለቋንቋው ትምህርት ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም ትምህርቶች አንብቦ መረዳት በጣም አስፈላጊው ክሂል መሆኑን ተረድተው ማስተማር ይጠበቅባቸዋል፡፡ የተለያዩ የፅሁፍ መረጃዎችን አንብበው የመተርጎም የመተንተንና የመጠቀም አቅማቸውን እንዲያሳድጉ አድርጎ ማስተማር የመምህራንን አቅም የሚጠይቅ ተግባር ነው፡፡ ስለሆነም መምህራንና ተማሪዎቻቸው ጥሩ አንባቢ ማድረግ አለባቸው ማለት ነው፡፡ በዚህ መሰረት አጥኚው ከላይ የተጠቀምኳቸውን ምሁራን አጠቃላይ ሀሳብ ሳይንሳዊ ትንታኔያቸውን መሰረት በማድረግ የስኬማን ንድፈ ሀሳብ መሰረት በማድረግ አማኑኤል ከንት በ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ግልፅ አድርጎ የአንብቦ መረዳት ትኩረት ማዕከላዊ ነጥብ በቀደመ ዕውቀት ላይ ያተኩራል በማለት የሰነዘረውን ሀሳብ በመጠቀም በአንብቦ መረዳት ሂደት ላይ ውጤታማ አተገባበር ላይ ትኩረት በማድረግ ጥናቱን አካሂዷል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ Conley (1992) እና Davis(2011) እንደሚሉት ጥሩ አንባቢዎች ብልሀተኞች ናቸው፡፡ የአንብቦ መረዳት ብልሀቶችን በመጠቀም ውስብስብ የሆነውን የአንብቦ መረዳት ሂደት እንዴት ማለፍ እንዳለባቸው ያውቃሉ፡፡ አንብቦ መረዳት ብልሀቶችን መጠቀም የክፍል ውስጥ አተገባበሩ ምን ሁኔታ ላይ እንዳለ በማጥናት በክፍል ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው የሚለያዩ ሊሆን እንደሚችል ከተለያዩ ጥናታዊ ፅሁፎች መረዳት ተችሏል፡፡ ከእነ Conley (1992) እና Davis (2011)የተወሰደው ሀሳብ (ትምህርት) የተማሪዎችን የአንብቦ የመረዳት ችሎታ መለየት ምክንያት የአዕምሯዊ ብቃት መለያየት ብቻ ሳይሆን ብልሀቶችን ካለመረዳት ሊመጣ የሚችል መሆኑን ያሳያል፡፡ ስለዚህ በልዩነቱ መምጣት ሂደት መምህራን የክፍል ውስጥ የአንብቦ መረዳት ስልት /ብልሃት/ አጠቃቀምና አተገባበራቸው በሚኖረው መስተጋብር ሊወሰን ይችላል፡፡ ስለሆነም ተማሪዎች

በተለያየ ሁኔታ የሚቀርቡላቸውን ጽሁፍ አንብበው የመረዳት ችሎታ እንዲያዳብሩ የብልሀቶቹን አጠቃቀም የማገዝና የመምራት ሀላፊነት በመምህራን ላይ የተጣለ ነው፡፡

ይህ ጥናት ከዝህ በፊት ከተደረጉ ጥናቶች አንፃር ሲታይ በብለሀቶች የተማሩ ተማሪዎች ብልሃቶችን ካልተማሩት ተማሪዎች የላቀ የአንብቦ መረዳት ውጤት እንዳስመዘገቡ ያሳያል፡፡ /እንድሪስ 2000/፡፡

በዚህም መሠረት ብልሃቶችን የተማሩ ተማሪዎች በብልሀቶች አተገባበር ዙሪያ የነበራቸው ዝቅተኛ አተገባበር ተሻሽሎ በመታየቱ ብልሀቶችን መማር አስፈላጊ ነው፡፡ /እንድሪስ 2000/ በአንብቦ መረዳት ብለሃቶች ላይ ባደረጉት ጥናት ከተወሰደው ሃሰብ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብለሀትን በአተገባበሩ ሥርዐት መሠረት በመምህሩ መምሪያ የቀረቡትን ስልቶች ሲጠቀሙበት በተማሪዎች አንብቦ መረዳት ብልሃት ላይ ለውጥ ከማስገኘቱም በላይ በምንባቡ ውስጥ የሚከናወኑትን መልመጃዎች እንዳሰሯቸውና ከዚህም አልፎ የጥሩ አንባቢ ባህሪ በመላበስ ለሌሎች ትምህርቶች ከፍተኛ ድጋፍ ይሰጧቸዋል፡፡ ከንባብ የሚገኙ መረጃዎችን የመሰብሰብ የመተንተን ፣ የመተርጎምና የመጠቀም ብቃት ያመጣል ተብሎ ይታሰባል፡፡

## 1.2 የጥናቱአነሳሽምክንያት

በቋንቋ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ጉዳይ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው ነው፡፡ ተማሪዎች በማንኛውም ትምህርት የተሻለ ዕውቀትና አረዳድ እንዲኖራቸው ና ዘላቂ አድርጎ የመቀጠል ዕድገት የሚመጣው በአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ በመስራት ነው፡፡ Dymock (2005) እንደገለፁት በአሁኑ ወቅት የሚታየው የንባብ ክሂል እጦት ተማሪዎች ከንባብ ጋር ሳይተዋወቁ ጥሩ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ሳይኖራቸው የከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ሲያጠናቅቁ ይታያሉ፡፡ ይህ ደግሞ በማንኛውም ትምህርት ዓይነት ብቁና ተወዳዳሪ እንዳይሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡ የዳበረ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ስለማይኖራቸውም ምንባብን ከመመልከት ባለፈ የቀረበውን ፅሁፍ መረዳት መተርጎም መተንተንና መጠቀም ባለመቻላቸው በትምህርት ውጤታቸው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል ሲሉ Dymock (2005) ይገልፃሉ፡፡

ዓለም እየዘመነ ባለበት ሰአት ማንበብ መቻል አማራጭ ወይም ቅንጦት ሳይሆን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አስዳጅነት ያለበት ነው(Rapp,Van den Broek,McMasster,kndeou,& Espin,2007:Taboada &Buehl,2012)ተማሪዎች በትምህርት ቤት ከሚማሯቸው ክሂሎችም ከፍተኛትኩረት ለማንበብ ሊሰጠውእንደሚገባ የሚናገሩጸሐፍት(conley,1992; Guthrie, Schafer, wang, &Afflerbach,1995,Heilaman,Blair,&Ruphley,1998)መኖራቸው የክሂሉን አስፈላጊነት ያሳያል፡፡

ከክሂሉ አስፈላጊነት አኳያም ተማሪዎች አንብቦ መረዳትን እንዴት መማር አለባቸው? ስኬታማ የአንብቦ መረዳት ትምህርትንስ እንዴት ማቅረብ ይቻላል? የሚሉት ጥያቄዎች የየዘመኑ ከፍተኛ

ጥያቄዎች ሆነው ይገኛሉ። ይህም አንብቦ መረዳት የአለም የይዘት ፡የብልሀትና የቋንቋ እውቀት አላባዎችን በጥምረት በመተግበር የሚከወን ውስብስብ ክሂል በመሆኑ የመነጨ ነው(chun,2000Drokchandra 2010 ውስጥ እንደጠቀሱት)።

ማንበብበ በብልሀት ትምህርት መደገፍ እንዳለበት ከሚመክሩት ባለሙያዎች በተቃራኒ ደግሞ የብልሀት ትምህርት አላስፈላጊ ብሎም መጥፎ ውጤትን እንገሚያስከትል የሚገልፁ አሉ(Guthrie et al,1995 ያደረጓቸው Bech&hynds,1991)::ምክንያታቸውም ተማሪዎን ለተዝናኖት ማንበብ መሰረት ከሆነው ኪናዊ የማንበብ ልምድ እንዲፋቱ ስሚያደርግ መረዳትን ከማዳበር ይልቅ ያዳክማል፤የሚል ነው።እንዲሁም የብልሀት ትምህርት በተናጠል ክሂል ላይ የሚያተኩር ፤ከጊዚያዊ ለውጥ ያለፈ ዘላቂነት ያለው ውጤት የማያመጣ እንደሆነ ያስረዳሉ(pressley et al,1992)::ከዚህም ሌላ paris et al.(1986) የጠቀሷቸው Tierney and Cunningham(1984)እና Singer(1995) ተማሪዎች የመረዳት አሳላጭ አዕምሯዊ መሳሪያናዎችን እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው ከማስገንዘብ ይልቅ ለጥሩ መረዳት እንዲፈጥሩ ማድረግ የበለጠ ጠቃሚ እንደሆነ ይገለፃሉ።በተጨማሪም የማንበብ ብልሀቶች ትምህርት በአንብቦ መረዳት ላይ ለውጥ የሚያስከትለው ከወራት እንደውም ከአመታት ብቻ(Drop, Van Elsacker,Voeten & Verhocvon 2016)እንደሆነ መከራከሪያ ሲቀርብ ይታያል።

በአንብቦ መረዳት ትምህርትና በብልሀት መካከል ዝምድና መኖሩን ጥናቶች አሳይተዋል።ይሁን እንጅ በብልሀት ትምህርት የአነብቦ መረዳት እንዲያሻሽል አስቻይ ምክንያቶችን አልዳሰሱም (Drop et al,2016)::Moets(1999) እንደገለፁት በመማር ማስተማር ሂደት ማንበብ አስፈላጊ መረጃን ለማግኘት አስፈላጊ ክሂል ነው።

በኢትጵያም በየደረጃው ተማሪዎች በአማርኛም ሆነ በእንግሊዝኛ ቋንቋ አንበብው የመረዳት ችሎታቸው በሚፈለገው ደረጃ እንዳልዳበረ አመልካች ጥናቶች አሉ(Silehi,2007፤ተስፋየ 2001 ዓ.ም፤ማስተዋል፤1989 ዓ.ም )። Ethiopian Education Training Quality Assurance Agency(2008)ን ዋቢ በማድረግ Early Grade Reading Assement-EGRA(2010)እንዳስፈረው በሀገሪቱ የአንብቦ መረዳት ችሎታ በየጊዜው እየቀነሰ መጥቷል።

የአንብቦ መረዳት ግብ ተማሪዎች ራሳቸውን ችለው አንብበው እንዲረዱ ማስቻል ነው። ተማሪዎች አንድን ፅሁፍ በሚያነቡበት ጊዜ እንዲያሰላስሉ፤እንዴት ማንበብ እንዳለባቸው ራሳቸውን እንዲቆጣጠሩ እንደሚከታተሉና እንዲገመግሙ ብቁ ያደርጋቸዋል።/Davis (2011) እና Aluculy (2006)። ይህን ሀሳብ በማጠናከር Tanchersley(2005) ትክክለኛ መረዳት አንባቢ የሚያነበውንና የሚያዳምጠውን ፅሁፍ በሜታ ኮግኒቲቭ ደረጃ መስተጋብር ሲፈጥሩ ነው። እነዚህ ሜታ ኮግኒቲቭ ብልሀቶች ባለመኖራቸው የአንብቦ መረዳት ችሎታ ተፈላጊ ደረጃ ላይ አለመድረሱን ጥናቶች ያመለክታሉ።Mayer(1980) Armbruster and Alderson (1987) ባካሄዱት ጥናት የአንብቦ መረዳት ጉዳይ ተጠንቶ ያልተጠናቀቀ መሆኑ አጥኚዎቹ ተጨማሪ ጥናት እንደሚያስፈልገው ጠቁመዋል።

የዚህ ጥናት አቅራቢ በ2ኛ ደረጃ መምህርነት ለአስራ ሁለት ዓመታት በማስተማር ሙያ ላይ እየሰራይገኛል፡፡ በእነዚህ የመማር ማስተማር አመታት ሲገነዘቡ በቆዩት መሰረት የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችግር አስተውሏል፡፡ ስለዚህም  በክፍል ውሰጥ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችግር የመጣው ምናልባትም የመምህራንን የአንብቦ መረዳት የክፍል ውስጥ አተገባበር በተገቢው ሁኔታ ተቃኝቶ አለመከናወኑና ብልሀቶቹን በመተግበር አለመጠቀም ሊሆን ይችል ይሆናል የሚል ስሜት ስለፈጠረበት በ2ኛ ደረጃ የ9ኛእና በ10ኛ  ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች የክፍል ውስጥ አተገባበርን የሚመለከት ጥናት ለማድረግ አነሳስቶታል፡፡ በመሆኑም በሁለተኛ ደረጃ በ9ኛ እና በ10ኛ ክፍል ደረጃ የመምህራን የአንበቦ መረዳት ብልሀቶች አተገባብር ላይ እየገጠሙ ያሉትን ችግሮች ለመፍታት እንደአንድ ስነ ትምህርት አቀራረብ አማራጭ ሆኖ ያገለግል ዘንድ መረጃ ይሰጣል፡፡ስለዚህም አጥኚው ብልሀቶችን በአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂል ማስትማር አውድ በመተግበር የመምህራን አተገባበር ውጤታማነት በመምህራን ተተኳሪነት ላይ መፈተሸ አስፈላጊ ሆኖ አግኝቶታል፡፡በአጠቃላይ አጥኘው በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ጥናቱን ለመስራት ከላይ የተጠቀሱት ንድፈሀሳባዊ ምርምራዊ እና ተሞክሯዊ ክፍተቶች መኖራቸውን በመገንዘቡ ነው፡፡

ስለሆነም ጥናቱ ለሚከተሉት መሰረታዊ ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣል፡፡

1ኛ.የ9ኛ የ10ኛ ክፍል የማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሀቶችን በክፍ ውስጥ ምን ያህል ተግባራዊ ያደረጋሉ?

2ኛ. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ያላቸው ግንዛቤ ምን ይመስላል?

3ኛ. በመምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የክፍል ውስጥ ትግበራ ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ሁኔታዎች ምን ምን ናቸው?

## 1.2 የጥናቱዓላማ

የጥናቱ ዋና አላማ፡- በደቡብ ወሎ የተንታና መቅደላ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች የ9ኛና 10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ የሚከተሏቸውን የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች መመርመር ነው፡፡

### 1.3.1 ንዑሳንዓላማዎች፡-

1ኛ. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሀቶችን በክፍል ውስጥ ምን ያህል ተግባራዊ እያደረጉ እንደሆነ ለመፈተሽ፤

2ኛ. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለአንብቦ መረዳት ብልሀቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ያላቸውን ግንዛቤ ለማሳየት፤

3ኛ. የአንብቦ መረዳት ብልሃት የመምህራን የክፍል ውስጥ አተገባበር ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ሁኔታዎችን መፈተሽ፤

## 1.4የጥናቱአስፈላጊነት

አንብቦ መረዳት የማስተማር ብልሃቶች አንባቢዎች ፅሁፉን በቀላሉ የመረዳትና ሀሳብን በአረጂም ጊዜ ለማስታወስ አቅም ይሰጣል፡፡ በንባብ ጥሩ ውጤት ላይ ለመድረስ ምንባቡ በምን አይነት እንደተዋቀረ ማወቅ ጠቀሜታ አለው (Dymock 2005)፡፡

ይህ ጥናት ቀጥሎ ያሉትን ጠቀሜታዎች ያመጣል ተብሎ ይታሰባል፡፡
1ኛ. መምህራን በጥናቱ ውጤት መሰረት የአንብቦ መረዳት ብልሀቶችን ተጠቅሞ ሲያስተምሩ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማዳበር የሚያስገኘውን ጥቅም ተገንዝበው ትኩረት ሰጥተው እንዲያስተምሩ ሊረዳ ይችላል፡፡
2ኛ. መምህራን የቀረቡትን ምንባቦች በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ በቀረቡበት አውድ መሰረት እንዲያስተምሩ ለማስቻል፡፡
3ኛ. በጥናቱ የሚገኘውን ውጤት መሰረት በማድረግ የመምህራኑን የአንብቦ መረዳት የክፍል አተገባበር አቅም ለመገንባት በሚያስችል የስራ ላይ ልዩ ልዩየመምህራን ስልጠናዎች ግብዓት ይሆናል፡፡
4ኛ. ለወደፊት ይህን መሰል ጥናት ለሚያጠኑ መምህራንና የስርዓተ ትምህርት አዘጋጆች እንደ መነሻ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡

## 1.5የጥናቱወሰን

የዚህ ጥናት ዋነኛ ትኩረት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን  የአንብቦ መረዳት  ብልሀቶች የክፍል ውስጥ አተገባበርን አስመልክቶ የሚካሄድ ነው፡፡
ጥናቱ በአማራ ብሔራዊ ክልል በደቡብ ወሎ የተንታና መቅደላ ወረዳ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች በ9ኛና በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራንየአንብቦ መረዳት ብልሀቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ላይ የተመሰረተነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት የዚህ ክፍል ተማሪዎች የ1ኛ ሳይክል ትምህርትን አጠናቀው በ2ኛው ሳይክል መጀመሪያ ላይ በሚገኘው የክፍል ደረጃ ላይ ሲደርሱ የሚፈለገውን የማንበብ አላባውያን አሟልተው በትክክል፣ በፍጥነት እና በጥሩ አገላለፅ ማንበብን አለመቻላቸውና በቴክስቱ ላይ የቀረቡ መልመጃዎችን በአግባቡ የመመለስ ችግር ስላለባቸው ይህን ችግር መፍትሄ ለመስጠት  ጥናቱ በአንብቦ መረዳት የመምህራን የክፍል ውስጥ አተገባበር ላይ አተኩሯል፡፡

የአንብቦ መረዳት ብልት ርእሰ ጉዳይ በተለያዩ አቅጣጫዎች ሊመረመር ይችላል፡፡ በመሆኑም በመማሪያና ማስተማሪያ መጽሐፍቱ ዉስጥ በተለያዩ ምእራፎች ዉስጥ የቀረቡትን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የክፍል ዉስጥ አተገባበርን ያካትታል፡፡ ከጥናቱ አላማ እና ትኩረት አንጻር የቀደመ እዉቀት መቀስቀስ (ማነሳሳት) ፣ የምንባቡን ሃሳብ መገመት፣ ምስል መከሰት(መገንባት) ፣ እንደገና( እያነበቡ መገመት)፣ ማሳታወሻ መያዝ ፣ የምንባቡን ዋና ሃሳብ መገንዘብ(መለየት)፣ ጥያቄና ምላሽ ፣ ማጠቃለልና በራስ አባባል መግለጽ እንዲሁም የመምህሩ አርአያ መሆን፣ ክትትል፣ ግምገማ፣ ግብረ መልስና ድጋፍ የማደረግ አቀራረብ ብልሃቶችን አካቶ ይዟል፡፡

## 1.6 የጥናቱውስንነት

ጥናቱ በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ሂደት ውስጥ በአዕምሯቸው ውስጥ ተነቦ የተገኘውን ዕውቀት ለማየት የሚያስችል አዕምሮአዊ የሆነ ውስብስብ ተግባር ከመሆኑ አንፃር በዚህ ክፍል ደረጃ ያሉ ተማሪዎች በተሰጠው ትምህርት እና በመምህራኑ አተገባበር ወቅት በተጨባጭ ወድያውኑ ለማየት የሚያስችል ላይሆን ይችላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከጥናቱ ወሰን ስፋት አንፃር እና ከወቅታዊ ሁኔታዎች አንፃር የተጠኝዎችን መረጃ ለመሰብሰብ የጊዜ እጥረት ችግር ቢያጋጥምም ለተግባሩ ትኩረት በመስጠት በአግባቡ መጠቀም እንዲቻል ተደርጓል፡፡

## 1.7 ቁልፍቃላትናጽንሰሃሳቦች

አንብቦ መረዳት ፡ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች ትምህርት አጠቃቀምና ስኬማ ንድፈ ሃሳብ የሚሉ ጽንሰ ሃሳቦች በጥናቱ ዉስጥ ቁልፍ ጉዳይ ናቸዉ። የአጠቃቀም ብያኔያቸዉም እንደሚከተለዉ ነዉ።

አንብቦ መረዳት ፦ ተማሪዎች የቀደመ እውቀታቸውን ማገናዘብና መጠቀም አንድን ጽሁፍ አንብበው የማስታወስ፣የመረዳት፣የመተርጎምና የመገምገም ሂደት ነው።

የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች፦አእምሮአዊ ግንዛቤን ከፍ በማድረግ ጽሁፉን ለመረዳት የሚያስችሉ ብልሃቶች ወይም ቴክኒኮች ሲሆኑ እነሱም የቀደመ እውቀትን መቀስቀስ፣መተንበይ(መገመት)፣ እንደገና መተንበይ (መገመት) ፣ምስል መፍጠር ፣የጽሁፉን ሀሳብ በራስ አባባል መግለጽ ፣ማጠቃለል እና መገምገም ናቸው (Davis 2011)።

የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች ትምህርት አጠቃቀም፦ በመምህር ድጋፍ የሚከናወን አእምሮአዊ ብስለትን ለማምጣት የሚያስችል ተግባር ሲሆን ተማሪዎች አንድን ጸሁፍ አንብበው እንዲረዱ ዳራዊ እውቀታቸውን እንዲጠቀሙ፣ በመቀስቀስ ፣የብልሀቶችን አጠቃቀም አርአያ ሆኖ በማሳየት፣ተማሪዎች ከመምህራቸው ጋር አብረው እንዲሰሩና ቀስ በቀስ በራሳቸው እንዲያከናውኑ የሚያደርግ ተግባራዊ ሂደት ነው።

ስኬማ ንድፈሀሳብ፦አንባቢዉ በአእምሮዉ ዉስጥ የሚገኝን ዳራዊ እዉቀት በቀጣይ ወደ አንባቢዉ አእምሮ የሚመጣዉን አዲስ እዉቀት ለመረዳት መሰረት የሚሆን ጽንሰ ሀሳብ ነዉ።

## ምዕራፍሁለት

## ክለሳድርሳናት

### 2.1 ጽንሰ ሀሳባዊ ቅኝት

ያለፉ ጥናቶች የምርምር ችግሩ ቲወሪ ተግባራዊ መነሻ ሆነው በማገልገል ለምርምሩ መነሻ መንደርደሪያ ይሆናሉ በማለት ያለው /2009፣29/ ይጠቁማሉ። ይህ ትልመ ጥናት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ላይ አተኩሮ እንዲጠና የሚመራ ነው። በዚህም መሰረት የአንብቦ መረዳት የክፍል ውስጥ አተገባበርን በተመለከተ በርዕሱ ዙሪያ የተደረጉ ጥናቶችና ጽንሰ ሀሳቦችን ይዟል።

#### 2.1.1 የአንብቦ መረዳት ክሂል ምንነት

ማንበብ ከመቀበያ ክሂሎች አንዱ ነው። የዚህ ክሂል መዳበር ተማሪዎች በሚማሩበት ቋንቋ በወጉ መጠቀምን እንዲችሉ በርካታ የቋንቋ ግብዓቶችን (language inputs) ለመሰብሰብ ያስችላል።

ማንበብ የአንድን ፅሁፍ የመረዳት/ የመተርጎም ሂደት ቢሆንም ውስብስብ አካላዊ አዕምሯዊና ብዙውን ጊዜ ስሜታዊ ምላሽን ይጠይቃል Pihuja(2002)።

የአንብቦ መረዳት ክሂል አንባቢው በፅሁፍ ከቀረቡ መረጃ ጋር መስተጋብር በመፍጠር መረዳትና እውቀት መጨበጥ የሚቻልበት ተግባር ነው። የአንብቦ መረዳት ክሂል ውስብስብ ዘርፈ ብዙና በሂደት የሚዳብር ነው Thunkrsley (2005) እና Moets (1999)። በተመሳሳይ Kni and Zemerson (1997) እንደገለፁት የአንብቦ መረዳት ክሂል የአንባቢውን በጥልቀት የማሰብ ከፅሁፍ ጋር ግንኙነት ለመፍጠር የቀደመ ልምድንና ዕውቀትን ለመጠቀም እንድሁም ከሚነበበው አድስ ፅሁፍ ጋር እያስተሳሰሩ ፀሀፊው ሊያስተላልፍ የፈለገውን መልዕክት መገንዘብን የሚጠይቅ ነው። Johonson(2008) የአንብቦ መረዳት ክሂል መሰረቱ መግንዘብ ነው። አንባቢው ለማንበብ የቀረበን ትምህርት/ፅሁፍ/ ከቀደመ እውቀቱ ጋር በማገናኘትና በማለማመድ በፅሁፍ ትርጉም መስጠት መቻል ነው። የማንበብ ክሂል በፅሁፍ ውስጥ ያለን አንድ ንዑስ ክሂል ከሌሎችም ሀሳብ ጋር የማገናኘት ተግባር ነው። በፅሁፍ ውስጥ ያሉ ሀሳቦችን ትርጉም ባለው መልኩ ማደራጀት መቻል አንዱና ጠቃሚ ጉዳይ መሆኑን አብራርተዋል።

Grant (1987) በበኩላቸው አንብቦ መረዳት የአንባቢውን ግልፅ መልዕክት መረዳትና ማብራራት በዚህም መነሻነት ያልተብራራውን መልዕክት በመመርመር የምንባብን አጠቃላይ መልእክት ከአንባቢው ገጠመኝ የቀደመ ዕውቀትና ችሎታ ጋር የማገናኘት ደረጃ መድረሱን የሚለይበት ነው

ሲሉ ይገልፃሉ፡፡ ከዚህ በላይ የቀረቡት ፅንሰ ሀሳቦች አንብቦ መረዳት ውስብስብ የሆነና ዘርፈ ብዙ ሆኖ በሂደት እየዳበረ የሚሄድ ከተማሪዎች አዕምሯዊ እድገት ጋር በየደረጃው እያደገ የሚሄድ ክሂል እና በቋንቋው ትምህርት ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም የትምህርት አይነቶች ተማሪዎችን የማገዝና ዕውቀታቸውን የመሙላት ሚናው ከፍተኛ መሆኑን የተገለጹት የምሁራን ብያኔዎች ያስረዳሉ፡፡

የብልሃቶችን ምንነት እና አጠቃቀም ማወቃቸው በቅድመ ንባብ ፤ በንባብ እና በድህር ንባብ ጊዜ ትምህርቱን ለመከታተል እና ተግባራቱን ማከናወን ፍላጎት እንዲኖራቸው ይረዳቸዋል፡፡

እንደ Adduclhi (2006) Aliculsy (2012) Conley (1992) እና Ephram (2009)አገላለጽ በአንባቢዎች እና በጽሁፍ መካከል የሚደረግ ብልሀታዊ መስተጋብር ለአንብቦ መረዳት መሰረት ይጥለል፡፡ የአንብቦ መረዳት ችሎታን በማጎልበት የሚርዱ የተለያዩ ብልሀቶች አሉ፡፡ ከዚህም መካከል የአንባቢዎችን የቀደም ዕውቀት በመቀስቀስ /በመገንባት/ ከሚነበበው ጽሁፍ ጋር ማገናኘት ትላቁን ሚና ይጫወታል፡፡ ይህም ጸሀፊው ያቀረበውን መረጃ ከዚህ በፊት በአዕምሯቸው ውስጥ ከነበረ መረጃ ጋር በማስተሳሰር መልዕክቱን እንዲረዱት ያግዛቸዋል፡፡ በተመሳሳይOnthario /2003/ እና Block (1997) እንደገለጽት አንባቢዎች በቅድመ ንባብ ፤ በንባብ እና በጽህር ንባብ ጊዜ የቀደመ እውቀታቸውን አጠቅመው ቢያነቡ ጽሁፍን ከዚህ በፊት ካነበቡት ጽሁፍ እና ከካባቢያቹው ነባራዊ እውንታ ጋር ስለሚያስተሳስሩት አረዳዳቸው ከፍ እንዲል ያደርጋል፡፡

/2002/ እንግሊዝኛ በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማሩ 400 ቻያናዊያን የሁለተኛ እና የከፍተኛ ደረጃ ተማሪዎች ላይ ጥናት አካሂደዋል፡፡ ጥናቱ የቀደመ እውቀት ለአንብቦ መረዳት ያለውን ሚና የመረመረ ሲሆን ፤ የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየው የቀደመ የስነ ልሳን እውቀት ያላቸው የጥናቱ ተሳታፊ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ማህበራዊ እና ባህላዊ የቀደመ እውቀት ያላቸው የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች አንብቦ ለመረዳት እንደረዳቸው አመላክታል፡፡

እንግዳ /1992/ /የቀደመ እውቀትን መሰረት ያደረገ/ የንባብ ማስተማሪያ ሞደል በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት ችሎታን ለማዳበር ያለው ተግባራዊነት እና ውጤታማነት ለመመርመር ሙከራዊ (experimental) ጥናት አሂደዋል፡፡ ጥናቱ 160 የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በሚገኙበት ሁለት ድድኖች የተካሄደ ሲሆን የሙከራ ቡድኑን በ"ቶፕዳውን" የንባብ ትምህርት አቀራረብ መሰረት ፤ በቁጥጥር ቡድኑን ደግሞ በተለመደው ዘዴ እንዲማሩት ተማሪዎች በልማዳዊ የማስተማሪያ ዘዴ ከተማሩት ተማሪዎች የበለጠ ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ በመሆኑም የ"ቶፕዳውን" የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል በአማርኛ ቋንቋ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማሻሻል ስለሚያስችል መምህራን ተግባር ላይ ሊያውሉት እንደሚገባ በጥናታቸው ማጠካለያ ገልጸዋል፡፡

የኔሰው /1990/ በበኩላቸው አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማሩ /በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ / ተማሪዎት አማርኛ አንብቦ መረዳት ክሂላቸውን ለማዳበር "አራክቧዊ " (interactive) ሞድላ ያለውን አስተዋጽኦ በባሌ ዞን በአዳባ ሁለተኛ ደረጃ በሚገኙ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች በፍትነታዊ የምርምር ዘዴ ለመፈተሽ አልሞ የተነሳ ነው፡፡ በመሆኑም ለጥብቅ ቡድን በጥናታዊ (traditional) የንባብ ክሂል ማስተማሪቲያ ሞዴል መሰረት በተዘጋጀው የማስተማሪያ መሳሪያ እና የክፍል ውስጥ ክንውን በተደገፈ ሁኔታ ፤ ለተጠኚ ቡድን ደግሞ በ"ተራክቧዊ" የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞደል መሰረት በተዘጋጁ የማስተማሪያ መሳሪያዎች እና የክፍል ውስጥ ክራውን በተደገፈ ለአምስት ሳምንታት ከተማሩ በኃላ ለሁለቱም ቡድኖች አንድ አይነት የድህረ ትምህርት ፈተና ተሰቷቸዋል፡፡ በጥናታቸው ውጤት እንደገለጽትም ተጠኚ ቡድን በተራግቧዊ ሞዴል በመማሩ የተሻለ ውጤት እንዳሳየ ገልጸዋል፡፡

## 2.2 የአንብቦመረዳትክሂልጠቀሜታ

እንደEphram(2009) ገለጻ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ተማሪዎችአዲስ እዉቀት እንዲገበዩ እና ህይወታቸዉ የተሳካ እንዲሆን የሚያስቺል ነዉ፡፡ በተመሳሳይ Moets (1999) ሲገልጹ ተማሪዎች በማንኛዉም ትምህርት የተሻለ እዉቀት እየገነቡ የመቀጠል ህልዉና በአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ የተመሰረተ ነዉ ፡፡በአንጻሩ ይህ ብቃት ከሌላቸዉ ማንኛዉንም ትምህርት ለመማር ይቸገራሉ ፤ ከተለያዩ ምንጮች መረጃ የማግኘት ብቃታቸዉም ደካማ ይሆናል፡፡

መምህራን የአንብቦ መረዳት ትምህርት የማስተማራቸዉ አስፈላጊነት ተማሪዎቻቸዉ በክፍል ዉስጥ የሚማሩትን የትምህርት ይዘት ለማሳካት ብቻሳይሆን በዕለት ተዕለት ህይወታቸዉ የሚያከናዉናቸዉን ተግባራት እዲያሳኩም ጭምር ነዉ (Thunkerslay 2005 እና Ephram2009 )፡፡

Conley (1992)Alicouley (2012) እንደገለጹት በአንብቦ መረዳት ሂደት አንብቦ መረዳትን ለማጎልበት የሚያስችሉ የተለያዩ ብልሀቶች ቢኖሩም የአንባቢዉን የቀደመ እዉቀት በማነሳሳት ወይም በመገንባት አዲስ ከሚቀርበዉ እዉቀት ጋር በማገናኘት መዘንጋት የሌለበት ቁልፍ ጉዳይ ነዉ፡፡ ምክንያቱም የቀደመ እዉቀት በአንብቦት መረዳት ላይ የሚያሳድረዉ ተጽእኖ ከፍተኛ ነዉና፡፡

በተመሳሳይ Hill (2011) የዳበረ አንብቦ መረዳት መገለጫ መስተጋብራዊ እና ብልሃታዊ ሂደት ነዉ፡፡ በዚህ ሂደት ማለፍ ሲቻል የአንብቦት መረዳቱ ዉጤት ያድጋል፡፡ የሚነበበዉ ምንባብ ብቻዉን የተሟላ ሳይሆን መነሻ በመሆኑ ከአንባቢዉ የቀደመ እዉቀት ጋር መገናኘት አለበት ፡፡ እንዲሁም መረዳትን የሚያጎለብቱ ብልሀቶችን መጠቀም አስፈላጊ መሆኑን የሚያመለክት ነዉ፡፡

በአጠቃላይ የአንብቦት መረዳት ክሂል ያለፈን መረጃ ከአዲሱ ጋር ለማገናኘት የሚያስችል እንዲሁም የወደፊቱን ለመተንበይ የሚረዳ ወሳኝ ኪሂል ነዉ፡፡ ተማሪዎች ይህን ብቃት ካላቸዉ ተፈላጊዉን መረጃ መለየት ፤መረዳት እና መተርጎም ይችላል፡፡በመኖኑም ክሂሉ በሁሉም የክፍል ደረጃ እናበሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ጠንካራ መሰረት ሊኖረዉ ይገባል፡፡

## 2.3 የአንብቦመረዳትብላሀቶችአስፈላጊነት

የአንብቦት መረዳት ብልሃቶች የማንበብ መሳሪያዎች ናቸዉ፡፡አንባቢዎችጽሁፍንበንቃት ተከታትለዉ በማንበብ እንዲረዱ እና ባልተረዱ ጊዜ ደግሞ ምን ማድረግ እንዳለባቸዉ ያመላክታሉ ፡፡ዉጤታማ መምህራን የተማሪዎችን የቀደመ ዕዉቀት በመቀስቀስ ፤ምንባቡን ከማንበባቸዉ በፊት እና እያእያነበቡ እንዲገምቱ በማድርግ በአእምሮአቸዉ ምስል በመክሰት በንቃት እንዲያነቡ በመረዳት ፤ ጥያቄዎችን በመጠየቅ እና ምላሽ እዲሰጡ በመጋበዝ፤ የጽሁፍን ሀሳብ በራሳቸዉ አባባል እዲገልጹ እና ማጠቃለያ እንዲሰጡ ፤በጥቅሉ ብልሀቶችን ከተግባር ጋር በማዋሀድ እንዲያነቡ ይጋብዛሉ፤ ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡ Davies(2011)፤ Onthario( 2003)፤ እና Harvey ዓ/ም)፡፡

Ephram (2009)፤Duk እና Pirson (2002)ን ጠቅሰዉ Folio (2011)እንደገለጹት የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የየራሳቸዉ መጠሪያ እና ምንነት ቢኖራቸዉም ለአንብቦ መረዳት ትምህረቱ በተናጥል የሚቆሙ አይደሉም፤ ይልቁንም እርስበርሳቸዉ የተሳሰሩ እና የሚገንዘባቡ ናቸዉ፡፡አንባቢዎች የብልሃቶችን ምንነት እና አጠቃቀም ማወቃቸዉ በቅድመ ንባብ ፤ በንባብ እና በድህረንባብ ጊዜ ትምህርቱን ለመከታተል እና ተግባራቱን ማከናወንፍላጎት እነዲኖራቸዉ ይረዳቸዋል ፡፡

እንደ Adjudhi(2006) ፤ Alicuouly (2012)፤ Conley (1992) እና Ephram (2009)አገላለጽ በአንባቢዎች አና በጽሁፍ መካከል የሚደረግ ብልሀታዊ መስተጋብር ለአንብቦ መረዳት መሰረት ይጥላል ፡፡ የአንብቦ መረዳት ችሎታን በማጎልበት የሚርዱ የተለያዩ ብልሀቶች አሉ፡፡ ከዚህም መካከል የአንባቢዎችን የቀደም ዕዉቀት በመቀስቀስ (በመገንባት )ከሚነበበዉ ጽሁፍ ጋር ማገናኘት ትላቁን ሚና ይጫወታል፡፡ይህም ጸሀፊዉ ያቀረበዉን መረጃ ከዚህ በፊት በአዕምሯቸዉ ዉስጥ ከነበረ መረጃ ጋር በማስተሳሰር መልዕክቱን እንዲረዱት ያግዛቸዋል ፡፡ በተመሳሳይ Onthario (2003) እና Block(1997) እንደገለጹት አንባቢዎች በቅድመ ንባብ ፤ በንባብ እና በድኅር ንባብ ጊዜ የቀደመ እዉቀታቸዉን አጠቅመዉ ቢያነቡ ጽሁፍን ከዚህ በፊት ካነበቡት ጽሁፍ እና ከካባቢያቸዉ ነባራዊ እዉንታ ጋር ስለሚያስተሳስሩት አረዳዳቸዉ ከፍ እንዲል ያደርጋሉ፡፡

ሊን (2002) እንግሊዝኛ በሁለተኛ  ቋንቋነጽ በሚማሩ 400 ቻያናዊያን የሁለተኛ  እና የከፍተኛ ደረጃ ተማሪዎች ላይ ጥናት አካሂደዋል ። ጥናቱ የቀደመ እዉቀት ለአንብቦ መረዳት ያለዉን ሚና የመረመረ ሲሆን ፤ የጥናቱ ዉጤት እንደሚያሳየዉ የቀደመ የስነ ልሳን እዉቀት ያላቸዉ የጥናቱ ተሳታፊ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን ማህበራዊ  እና ባህላዊ  የቀደመ እዉቀት ያላቸዉ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ  ተማሪዎት አንብቦ ለመረዳት እንደረዳቸዉ ያመለክታል።

እንግዳ (1992) ዮቶፕዳውን (የቀደመ እዉቀትን መሰረት ያደረገ ) የንባብ ማስተማሪያ ሞደል በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት  ችሎታን ለማዳበር ያለዉ ተግባራዊነት እና ዉጤታማነት ለመመርመር ሙከራዊ (experimental) ጥናት አሂደዋል። ጥናቱ 160 የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በሚገኙበት ሁለት ቡድኖችየትካሄደ ሲሆን የሙከራ ቡድኑን በ"ቶፕዳዉን" የንባብ ትምህርት አቀራረብ መሰረት ፤ የቁጥጥር ቡድኑን ደግሞ በተለመደዉ ዘዴ እንዲማሩ ከተደረገ በኃላ በፈተና ተመዝነዋል ። በጥናታቸዉ ዉጤት እንደተገለጸዉ በብልሀቱ የተማሩት ተማሪዎች በልማዳዊ የማስተማሪያ ዘዴ ከተማሩት ተማሪዎች የበለጠ ዉጤት አስመዝግበዋል ። በመሆኑም የ "ቶፕዳዉን" የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል በአማርኛ ቋንቋ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማሻሻል ስለሚያስችል መምህራን ተግባር ላይ ሊያዉሉት እንደሚገባ በጥናታቸዉ ማጠካለያ ገልጸዋል ።

የኔሰዉ (1990) በበኩላቸዉ አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማሩ (በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸዉን የፈቱ) ተማሪዎች አማርኛ አንብቦ መረዳት ክሂላቸዉን ለማዳበር " ተራክቧዊ " (interactive) ሞድላ ያለውን አስተዋጽኦ በባሌ ዞን በአዳባ ሁለተኛ ደረጃ በሚገኙ የ11ኛክፍል ተማሪዎች በፍትነታዊ የምርምር ዘዴ ለመፈተሽ አልሞ የተነሳ ነዉ። በመሆኑም ለጥብቅ ቡድን በጥናታዊ (traditional ) የንባብ ክሂል ማስተማሪቲያ ሞዴል መሰረት በተዘጋጀዉ የማስተማሪያ መሳሪያ እና የክፍል  ዉስጥ ክንዉን በተደገፈ ሁኔታ ፤ ለተጠኚ  ቡድን ደግሞ በ " ተራክቧዊ " የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞደል መስረት በተዘጋጁ የማስተማሪያ መሳሪያዎች እና የክፍል ዉስጥ ክንዉን በተደገፈ ለአምስት ሳምንታት ከተማሩ በኃላ ለሁለቱም ቡድኖች አንድ አይነት የድህረ ትምህርት ፈተና ተሰቷቸዋል ። በጥናታቸዉ ዉጤት እንደገለጹትም ተጠኚ ቡድን በተራግቧዊ  ሞዴል በመማሩ የተሻለ ዉጤት  እንዳሳየ ገልጸዋል።

ከቀረቡት ጥናቶችውጤትመረዳት የሚቻለዉ በአንብቦ መረዳት ትምህርት ሂደት የአንብቦ መረዳት ብልሀቶችን መጠቀምፋይዳው የጎላ መሆኑን ነዉ ። በመሆኑም ተማሪዎችበብልሀቶች በተደገፈ ሁኔታ እንዲማሩ ቢደረግ የአንብቦ መረዳት ችሎታቸዉ ሊጎለብት እንደሚችል የሚያስገነዝብ ነዉ።ስለዚህ የኔ ጥናት የአንብቦ መረዳት ብልሀት አተገባበር ላይ ተጽዕኖ የማሳያነት ፈትሾ በችግሩ መፍትኄ ለመስጠት ይረዳል ።

የርስበርስ መማማር የአንብቦ መረዳት ብልሀት ( reciprocal teaching ) በአራቱ ብልሃቶች ላይ ያተኩራል ። ማለትም ፤ መገመት ፤ ማብራራት ፤ ጥያቄ እና መልስ እና ማጠቃለል ብልሀት ላይ ያተኩራል ። ( C&I2010 ):: ሮይና ሮስ(2006)ን ጠቅሰዉ Ephram (2009) በተመሳሳይ እንደገለጹት ፤ በአንብቦ መረዳት ትምህርት ተማሪውችን የሚረዱ ወሳኝ ብልሀቶች አሉ።እነሱም ፤መገመት ፤በራስ አባባል መግለጽ ፤ጥያቄ እና መልስ እና ማጠቃለል ናቸዉ ። የመገመት ብልሀት ተማሪዎች ጽሁፍን ከማንበባቸዉ በፊት እና እያነበቡ ቀጥሎ የሚመጣዉን የምንባብ ይዘት እንዲገነዘቡ ፤ተነሳሽነት እንዲኖራቸዉ እና በጥረት እንዲያነቡ ይረዳል ።በራስ አባባል መግለጽ ደግሞ አንባቢዉ የተገነዘበዉን በራሱ አገላለጽ ማንጸባረቅ እንዲችል የሚያደርግ ነዉ ። የማጠቃለል ብልሀት ጽሁፍን ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በትኩርት ማንበብ ሀሳቡን ጨምሮ ለማዉጣት ያስችላል ። ጥያቄ እና መልስ ብልሀት ተማሪዎች ለጥያቄዎች ምላሽ ለማግኘት ጽሁፍን በትኩረት እንዲያነቡ ይረዳል።

Armbuster እና Asburn (2002)ን ዋቢ በማድረግ ማረዉ (1998) እንደተገለጹት አንብቦ መረዳት በማስተማር ሂደት ከንባብ በፊት ፤ በንባብ ጊዜ እና ከንባብ በኋላ ጥሩ ጥያቄዎች መጠየቅ ለዉጤታማ ትምህርት ያበቃል ።በእያንዳንዱ ደረጃ የሚጠየቁ ጥያቄዎች ተግባርም ይለያያል ።በቅድመ ንባብ ጊዜ የሚጠየቁ ጥያቄዎች የሚነበበዉን ጽሁፍ ርዕሰ ጉዳይ አስመልክቶ ተማሪዎች የተሟላ ዳራዊ እዉቀት እዳላቸዉ እንደሌላቸዉ ለመፈተሽ ፡ ወደ ዋናው ንባብ በሚገቡበት ጊዜ ምን ማድረግ እንደሚጠበቅባቸዉ አስቀድመዉ እንዲዘጋጁ ፡ የጋራ ግንዛቤ ይዘዉ እንዲያንቡ ስለሚያነቡት ጽሁፍ ይዘት እንዲገምቱ እና ይማንበብ ፍላጎታቻ እንዲነሳሳ ፡ ቀድመዉ የሚገምቱትን ከሚያነቡት ጽሁፍ ጋር እያነጻጸሩ እንዲያነቡ ያግዛሉ ። በንባብ ጊዜ የሚጠየቁ ጥያቄዎችም ተማሪዎች የሚያነቡት ምንባብ መረዳታቸዉን ለመቆጣጠር ጠቃሚ ናቸዉ።ድህረ ንባብ ጥያቄዎች ደግሞ የተማሪዎችን ግንዛቤ ለማቅ የሚያግዙ ፡ ተማሪዎችያነበቡትን ለመከለስ ፡ ለማጠቃለል፡ካነበቡት ጽሁፍ ያገኙትን አዲስ መረጃ ከዳራዊ እዉቀታቻዉ ጋር ለማዋሃድ ይጠቅማሉ።

Rubison እና ሌሎች(2002)ን በመጥቀስ Feeters እና ሌሎች (2011) በጥናታቸዉ እንደጠቀሱት የንባብ እና ድህረ ንባብ ብልሀቶችን መሰረት ያደረጉ ትምህርት የተማሪዎችን አንብቦ መረዳት ከናሳደጉመ ባሻገር ሌሎች የትምህርት አይነቶችን የምማር ሁኔታ በማሻሻል ረገድ ከፍተኛ አለዉ።Conley (1992) ፤ Tankersley (2005)እና Aloqaili (2012) እንደሚገልጹት ብልሃታዊ አንባቢዎች አንብበዉ ለመረዳት የተሸለ ክህሎት አላቸዉ።አዲስ የሚነበበዉን ጽሁፍ ከቀደመ አዉቀታቸዉ ጋር ትስስር ለመፍጠር የሚያስችሏቸዉን ብልሀቶችን ተጠቅመዉ ተፈላጊዉን እዉቀት  እና መረጃ ያገኛሉ።ከልምድ እንደሚታየዉ ብዙ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችግር አለባቸዉ ። ይህን ብልሀቶችን እንዴት መጠቀም እንዳለባቸዉ አለማወቅ አንዱ መሰረታዊ ጉዳይ ነዉ ። ይህን ችግር ለማስወገድ መምህራን ትልቅ ሚና ሊጫወቱ ይገባል።

ዉጤታማ መምህራን ተማሪቻቸዉ ንቁ አንባቢዎች እንዲሆኑ ይጥራሉ፡፡ ንቁ አንባቢዎች ብልሀታዊአንባቢዎች ናቸዉ፡፡የአንብቦ መረዳት ብልሀቶችን መቼ እንዴት እና ለምን አላማ እንደሚጠቀምባቸዉ ያዉቃሉ፤ ጽሁፍን አንብበዉ ይረዳሉ (Davis 2011 እና ደንቶን እና ሌሎች 2007)፡፡

Lauau እና Chan (2003) አንብቦ መረዳት ብልሀቶችን ጠቀሜታ እና ከዉስታዊ ተነሻሽነት ጋር ያለዉን ተዛምዶ በ 83 ጥሩ በ76 ደካማ አንባቢ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ያካሄዱት ጥናት ፤ ደካማ አንባቢዎች የማንበብ ብልሀቶችን ተጠቅመዉ ያስመዘገቡት ዉጤት ከጥሩ አንባቢዎች ዉጤት ያነሰ ነዉ፡፡ እንዲሁም ደካማ አንባቢዎች ከጥሩ አንባቢዎች ያነሰ ዉስታዊ የማንበብ ተነሳሽነት እንዳላቸዉ ጠቁሟል፡፡ይህም የሚያመለክተዉ ማንበብ ብልሀቶችን የመጠቀም ብቃት አንብቦ መረዳት እና ከዉስጣዊ ተነሳሽነት ጋር የጠነከረ ትስስር መኖሩን ሲሆን ፤ በተጨማሪም ጥሩ አንባቢዎች ብላሀቶችን በመጠቀም በኩል የተሻለ ብቃት እንዳላቸዉ ነዉ ፡፡

አንብቦ መረዳት ብልሀቶች መጠቀም ከቀረበዉ ጽሁፍ የተደራጀ መልዕክት የመረዳት ችሎታን ለማዳበር ፤ ያገኙትን መረጃ በአእምሮ ዉስጥ ለረጅም ጊዜ ለማቆየት አእምራዊ ችሎታን ከፍ በማድረግ አገናዛቢነትን ለማዳበር ይረዳል ( Middleton በ1989)፡፡የPanikisornና Browen (1984)ን የጥናት ዉጤት Alfassi (1998)ሲገልጹ ጥናቱ የርስበርስ መማማር የማንበብ ብልሀት (reciprocal teaching );ከተለመደዉ የማንበብ ትምህርት(traditional teachimg) አንብቦ መረዳት ያለዉን ብልጫ የመረመረ ነዉ ፡፡ ጥናቱ ለ5 ክፍለ ጊዜ በብልሀቱ የተማሩ በ53 ተማሪዎችን እና በተለመደዉ የተማሩ 22 ተማሪዎችን አሳተፈ ሙከራዊ ጥናት የተካሄደበት ሲሆን የጥናቱ ዉጤትእንደተመለከተዉ ፤ በብልሀቱ የተማሩት ተማሪዎች በተለምዷዊ ከተማሩት ዉጤታቸዉ አድጎ ታየቷል፡፡ በመሆኑም መምህራን የተማሪዎቻቸዉን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ብልሀቱን በክፍል ዉስጥ ተግባራዊ ሊያደርጉት ይገባል፡፡

በአጠቃላይ የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች የተማሪዎችን ወይም የአንባቢዎችን ማንበብ ዉጤታማ ለማድረግ የሚገለግሉ መሳሪያዎች ናቸዉ፡፡ በመሆኑም የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማጎልበት የብልሀቶችን ጠቀሜታ እና አጠቃቀም ተገንዝቦ መተግበር ያስፈልጋል ፡፡

## 2.4 የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች የክፍል ዉስጥ አተገባበር (ቅድመ ንባብ፤ በንባብ ጊዜ እና በድህረ ንባብ )

አንብቦ መረዳት ከአንድ ጽሁፍ ተፈላጊ መረጃ ለማግኘት መቻል ነዉ ፡፡ይህን ክሂል በአንድ ጊዜ የሚዳብር ሳይሆን በንባብ ሂደት ደረጃ በደረጃ በሚደረግ አዕምሯዊ ክንዉን ወይም ብልሀታዊ ልምምድ የሚመጣ እድገት ነዉ (Tankersley 2005)፡፡ የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች ትምህርት በሁለት መስክ ሊቀርብ እንደሚችል የመስኩ ባለሙያዎች ይገልጻሉ ፡፡ Omahaley እና Chamet

(1990)ን ዋቢ በማድረግ ተክላይ (2000) ሲገልጽ፤ አንደኛዉ የብልሃቶች አቀራረብ ብልሀቶችን ከሌላዉ ትምህርት በመነጠል የቀጥታ ማስተማር ሲሆን ሁለተኛዉ ብልሀቶችን ከትምህርት እና ከተግባራት ጋር አቀናጅቶ የማስተማር አቀራረብ ነዉ። ምንም እንኳን ሁሉም አቀራረቦች የየራሳቸዉ ጠንካራ እና ደካማ ጎን ቢኖራቸዉመም ከትምህርት እና ከተግባራቱ ጋር ተቀናጅቶ የሚቀርበዉለመምህራኑ አነስተኛ ስልጠና በመስጠት ተግባራዊ ለማድረግ ጠቀሜታ አለዉ።ተማሪዎችም በመምህሩ መሪነት ከቀረቡላቸዉ የማስተማሪ መሳሪያዎች እና ተግባራት ተነስተዉ ብልሀቶችን ተግባራዊ ያደርጋሉ ።

አንብቦ መረዳት የአንድን ጽሁፍ ሀሳብ መገንዘብ የሚጠይቅ ዉስብስብ ሂደት ነዉ። በመሆኑም ተግባራቱን በቅደም ንባብ፤ በንባብ እና በድህረ ንባብ ደረጃዎች በመክፈል በአግባቡ መከወንን እንደሚጠይቅ Onthrio (2003) ገልጻል ። Chomikin (2007)ን ጠቅሰዉ Ephram (2009) እንደሚያስረዱት ተማሪዎችምንባብን ከማንበባቸዉ በፊት ስዕልን ፤ ካርታን ፤ አብይ እና ንዑስ ርዕሰ ጉዳዮች ወዘተ በመመርመር ስለጽሁፍ ይዘት እንዲገምቱ በማድረግ የቀደም እዉቀታቸዉን ማነሳሳት ይገባል ።ይህም ተማሪዎች ወደ ማነንበቡ ተግባር ከመግባታቸዉ በፊት ከርዕሱ ፤ከስዕሉ፤ከተዛማጅ ጽንሰ ሀሳቦች ወዘተ በመነሳት ጥያቄዎችን መጠየቅ እና ሀሳባቸዉነው እንዲሰነዝሩ በማድረግ ማነቃቃት የጠይቃል ።ይህ ካልሆነ የማንበብን ዓላማ ማሳካት አይችሉም።

በተመሳሳይ Davis (2011) እና Tankersley (2005) በክፍል ዉስጥ ማንበብ ትምህርት ተማሪዎችቅድመ ንባብ ተግባራትን እንዲያከናዉኑ ማድረግ ለቀጣዩቹ ደረጃዎች ቀና መንገድን ማመቻት ነዉ።ተማሪዎች ምንባቡን ለምን እንዲያነቡ እንዲገነዘቡ መረዳት ፤ ምንባቡን በሚመለከት ያላቸዉን ዳራዊ እዉቀት እንዲያስታዉሱ ፤ በአእምሯቸዉ ምስል በመከሰት ምንባቡን በሙሉ ስሜት እንዲያነቡ ፤ ከምንባብ ርዕስ ጋር አዛምደዉ ስለይዘቱ እንዲገምቱ እና ስለምንባቡ ይዘት የጋራ መነሻ እንዲይዙ ድጋፍ ቢደረግ ፤ባጠቃላይ ምንባቡን በማንበብ ተነሳሺነት ቢፈጠርላቸዉ በሚያነቡት ጊዜ ምንም እንደማያዉቁ እንዳማይሰማችዉ እና በትኩረት እንዲያነቡ ይረዳቸዋል ። አንብቦ መረዳት ሂደት በዋናነት አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድረዉ የሚነበበዉን ጽሁፍ ከአንባቢዎች የቀደመ እዉቀት እና ልምድ ጋር ያለማገናኘት ጉዳይ ነዉ።

Fielding እና Pirson (2004) ሲገልጹ በ1970ዎቹ መጀመሪያ የተካሄዱት የጥናት ዉጤቶች እንደሚያሳየዉ በቀደመ ዕዉቀት እና በአንብቦ መረዳት መካከል ዘላቂ እና ጠንካራ የርስበርስ ግንኙነት መኖሩን ነዉ። በመሆኑም የቀደመ እዉቀቱ ያልተቀሰቀሰ (ያልተገነባ) አንባቢ የአንብቦ የመረዳት ችሎታዉ አነስተኛ መሆኑን ጠቁምዋል ።

Hedge (1985) በአፍ መፍቻ ቋንቋ የተካሄዱ የጥናት ዉጤቶችን ቃኝተዉ እንደገለጹት ፤ የዳበረ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያላቸዉ ተማሪዎች የቀደመ እዉቀታቸዉን በመጠቀም ስለምንባቡ አጠቃላይ መልዕክት አስቀድመዉ በመገመት ስለሚያነቡ ከምንባቡ ዉስጥ የተወሰኑ ፊደሎችን እና ቃሎችን ቢገድፉ እንኳ መልእክቱን ለመረዳት አያዳግታቸዉም። የአንብቦ መረዳት ጥረታቸዉ

የማይደናቀፈዉ ዳራዊ እዉቀታቸዉን ከሚያነቡት ምንባብ ጋር አቀናጅተዉ ለማንበብ ጥረት ስለሚያደርጉ እና ስለ ምንባቡ ይዘት አስቀድመዉ በመገመት በትኩረት ስለሚያነቡ ነዉ ። የነዚህ የአንባቢዎቹ ትኩረት የሚያገኙትን ፍንጭ ሁሉ በመጠቀም የምንባቡን ጠቅላላ መልዕክት መረዳት ነዉ። በመሆኑም ተማሪዎቻቸዉ በዚህ ሂደት እንዲጓዙ መምህራን የድርሻቸዉን ሊወጡ ይገባል ።

Bensissan (1998) እንደሚያስረዱት የተማሪዎችን የቀደመ እዉቀት መቀስቀስ ለአንብቦ መረዳት ያለዉ ሚና ከፍተኛ ነዉ ። ይሁን እና የቀደመ እዉቀታቸዉ ተስማሚ ያልሆነ ወይም የተዛባ ከሆነ የጽሁፍን ሀሳብ ላይረዱት ይችላሉ።በሀይፋ ዩኒቨርሲቲ የእንግሊዝኛ ኮርስ የሚወስዱ 125 ተማሪዎችን የጥናትቱ ተሳታፊ በማድርግ ተስማሚ ያልሆን የቀደመ ዕዉቀት በአንብቦ መረዳት ላይ ያለዉን ተጽእኖ መርምረዋል። በጥናታቸዉ ዉጠየት እንደገለጹትም ተማሪዎች 23 ፐርሰንት የተሳሳተ መልክ የመለሱት ተስማሚ ያልሆኑ የቀደመ እዉቀት በነጠቀማቸዉ መሆኑ ገልጸዋል ።

ማንበብ ክሂል ትምህርት ዓላማ ያለዉ መሆን አለበት ። ተማሪዎች አንድ ጽሁፍ ከማንበባቸዉ በፊት አስቀድመዉ የሚያነቡትን ጽሁፍ ዓላማ ወይም ምን እንዲያነቡ በአግባቡ ሊያዉቁ ይገባል። ብዙ ጊዜ የተለመደዉ አተገባበር ተማሪዎች አንድ ጽሁፍ ካነበቡ በኋላ በማስከተል በምንባቡ መሰረት የሚመለሱ ጥያቄዎችን ማቅረብ ነዉ።ይሁን እና አስቀድሞ የተነበበዉ ጽሁፍ ዓላማ አልባ ነበር (ማረዉ 1998)።

Dorkion (1978- 1979) በጥናታቸዉ ዉጤት የረጋገጡትን Fielding እና Pirson (1994) ሲገልጹ መምህራን ለቅድመ ንባብ እና ለንባብ ጊዜ ተግባራት/ ብልሃቶች / ተግባራዊነት ጠሚስጡት ትኩረትም ሆነ ያላቸዉ ግንዛቤ ዝቅተኛ ነዉ ። በተቃራኒ ትልቁ ድርሻ የሚሰጡት ምንባቡ ከተነበበ በኋላ ከምንባቡ ለዉጡ በርካታ ጥቄዎች ተማሪዎች ምላሽ እንዲሰጡ ማድረግ እና መፈተን ላይ ነዉ።ይህ አይነቱ አተገባበር ዉጤታማ አለመሆኑን የጥናቱ ዉጤት በመጠቀሙ ፤ በ1980ዎቹ በርካታ አጥኒዎችን በማነሳሳት ትኩረታቸዉን አንብቦ መረዳት ትምህርት እና በብልሀቶቹ ላይ አድርገዋል ።

እንደ Ajideh (2006) ገለጻ በርካታ ጥናቶች የቅድመ ንባብ ተግባራትን አተገባበር በተመለከተ ገምግመዋል ። ቅድመ ንባብ ተግባራት የተማሪዎችን የቀደመ እዉቀት የሚያነሳሱ ፤ በቀጣዩ ደረጃ ምን መተግበር እንዳለባቸዉ ግንዛቤ የሚሰጡ መሆን አለባቸዉ ።

እንደ መስኩ ባለሙያዎች በአንብቦ መረዳት ትምህርት የቅድመ ምንባብ / ተግባራት የክፍል ዉስጥ አተገባበር ለንባብ እና ለድህረ ንባብ ተግባራት መሰረት ነዉ። በመሆኑም እንደ አተገባበሩ ሁኔታ አዉንታዊ ወይም አሉታዊ ተጽእኖ ማሳደሩ አይቀሬ ነዉ ።

በንባብ ጊዜ ተማሪዎች  ማንበባቸዉን እንዲከታተሉ እና የመረዳት ችሎታቸዉን እንዲያዳብሩ የሚያስችሉ ብልሀቶችእንዲጠቀሙ ማንስገንዘብን እና መጋበዝን ይጠይቃል ።

Tiherey እና Doctrew (2004) እንደገለጹት ዉጤታማ መምህራን ተማሪዎች ብዙ እንዲያነቡ ብቻ ሳይሆን ዉጤታማ የአንብቦ መረዳት ብልሀቶችን እንዲያዉቁ እና ከተግባራቱ ጋር እንዲያዋህዷቸዉ ያስገነዝባሉ ፤ ድጋፍ ያደርጋሉ። አንብበዉ መረዳታቸዉን በዉይይት የሚገኑበት ሰፊ ዕድል እንዲፈጠርላቸዉ ያመቻቻሉ። Tankersley (2005) እና Davis (2011) በበኩላቸዉ የንባብ ጊዜ ተማሪዎች ተስማሚ ብልሀቶችን በመጠቀም አንብበዉ እንዲረዱ የሚደረግበት ደረጃ ነዉ ። በዚህ ደረጃ ተማሪዎች በቂ ልምምድ እንዲያደርጉ ይጠበቃል ። በልምምዱ ተማሪዎች ሙሉ በሙሉ ተሳታፊ የሚሆኑበት እንጅ ተቀባይ የሚሆኑበት አይደለም ። የመምህሩ ሚና ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ ሊያተኩርባቸዉ የሚገቡ ፍንጮችን መጠቀም ፤ አስፈላጊ ሲሆን ከጓደኞቻቸው ጋር ሀሳብ እንዲለዋወጡ መጋበዝ ፤ መከታተል እና አስፈላጊ ድጋፍ ማድረግ ተጠቃሽ ናቸዉ ።

Alfassi (1998) በጥናታቸዉ እንደገለጹት በማንበብ ጊዜ ተማሪዎችአራት የአንብቦ መረዳት ብልሀቶችን መሰረት በማድረግ እንዲለማመዱ ይፈለጋል ። እነሱም ጥያቄዎችን እንዲያፈልቁ/ እንዲመልሱ፤ ያነበቡትን የጽሁፍ ክፍል ዋና ሃሳብ እንዲለዩ ፤ ትርጉማቸዉ ግልጽ ያልሆነላቸዉን ቃላት ትርጉማቸዉን ለማወቅ እንዲጥሩ እና በቀጣይ የጽሁፍ ክፍል ምን ሊከሰት እንደሚችል እንዲገምቱ ማድርግ ነዉ። ተማሪዎች እነዚህን ብልሀቶች በአግባቡ መጠቀም ከቻሉ ማንበባቸዉን እየተቆጣጠሩ የጽሁፉን ሀሳብ መገንዘብ ይቻላል ።

Ephram (2009) በጥናታቸዉ ግኝት እንደገለጹት መምህራነ ተማሪዎች ጽሁፍን አንብበዉ እንዲጨርሱ እድል መፍጠር ብቻዉን በቂ አለመሆኑን ሊገነዘቡ ይገባል ፤ይልቁንም ራሳቸዉ መምህራን ስለብልሀቶች ያላቸዉን ግንዛቤ በማሳደግ ተማሪዎቻቸዉን ማለማመድ  እና በመጨረሻም ራሳቸዉ ችለዉ ብላሀቶችን እየተጠቀሙ አንብበዉ እንዲረዱ ማድረግ ይጠቅማቸዋል። እኒሁ ባለሙያ ሲገልጹ ፤ በአንብቦ መረዳት ትምህርት የመምህራን ክትትል እና ድጋፍ ወሳኝ ነዉ።በተይለይ በማንበብ ጊዜ ተማሪዎችን መከታተል ጽሁፍን አንብበዉ መረዳት አለመረዳታታቸዉን ፤ መቼ የትኛዉ ብልሀት መጠቀም እንዳለባቸዉ ፤አንብበዉ ባልተረዱ ጊዜ ምን ማድረግ እንዳለባቸዉ፤ መቼ የጓደኛ ወይም የመምህር እገዛ እነደሚያስፈልጋቸዉ ለመወሰን ያስችላል ።

በድህረ ንባብ ጊዜ ተማሪዎች ያነበቡትን ጽሁፍ በተመለከተ ያላቸዉ የቀደመ እዉቀት ካነበቡት ጽሁፍ ጋር ትስስር መፍጠር መቻል አለመቻሉን ፤ያነበቡትን ጽሁፍ መገንዘብ አለመገንዘባቸዉን መፈተሽ የሚስችሉ ብልሀቶችን እንዲጠቀሙ ማበረታታት ያጠይቃል ። Davis (2011 )እና ዲንቶን እና ሌሎች (2007) እንደሚያስረዱት ዉጤታማ መምህራን ተማሪዎች በቅድመንባብ እና በንባብ ጊዜ ያከናወናቸዉን  የአንብቦ መረዳት ተግባራት እንዲያጠናክሩ ፤እንዲፈትሹ፤ዉሳኔ ላይ እንዲደርሱ ፤ ተጨማሪ መረጃ እንዲፈልጉ ይጋብዛሉ፤ ያበረታታሉ፤ይገመግማሉ።ለምሳሌ ግምታቸውን ከጽሁፉ ጋር እንዴት እንደተዛመዱ እና እንዳልተዛመደ እንዲያረጋግጡ ፤የጽሁፍን ሀሳብ ምን ያህል እንደተገንዘቡ ለጥያቄዎች ምላስ እንዲሰጡ ፤ስላነበቡት ጽሁፍ በዐይነ ሂሊናቸዉ ምስል እንዲፈጥሩ ፤ያነበቡትን ጽሁፍ ዋና እና ዝርዝር ሀሳብ እንዲለዩ ፤ የጽሁፍን ሀሳብ እንዲያጠቃልሉ ፤ገጸባህርያቱን ፤ አጋጣሚዎችን እና ይዘቱን ከራሳቸዉ ፤ ከነባራዊ ዓለም እና ከሌሎች ጽሁፎች ጋር እንዲያነጻጽሩ ፤ እርስ በርሳቸዉ ሀሳብ እንዲለዋወጡ እና ተጨማሪ መረጃ እንዲፈልጉ ያደርጋሉ።

Roy ና Rosse (2006)ን ጠቅሰዉ Epharaa (2009) እንደገለጹት የአንብቦ መረዳት ስኬት ተማሪዎች ከሚያነበበዉ ጽሁፍ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ፈጥረዉ ጸሀፊዉ በቀጥታ ያሰፈረዉን እና ያላሰፈረዉንም ሀሳብ መገንዘብ መቻል ነዉ። ተማሪዎች ብልሀቶችን ተጠቅመዉ በልምምድ ደጋግመዉ የሚያነቡ ከሆነ ይህን ችሎታ ያዳብራሉ፤ ለአጠቃላይ አንብቦ መረዳትም ብቁ ይሆናሉ።

Pearson ና Dol (1987) ዋቢ በማድረግ Faelding ና Person (1994) እና ሞስቶዉንና ቸን እንደገለጹት የአንብቦ መረዳት ልምምድ ሞዴል አራት ደረጃዎችን ይይዛል። እነሱም፡- መምህሩ ስለ ብልሀቱ ገለጻ መስጠት እና አርዓያ ሆኖ ማሳየት ፤ በድጋፍ ማለማመድ እና ቀስበቀስ ሃላፊነቱን ለተማሪዎች መስጠት ፤ ከዚያም ተማሪዎች በራሳቸዉ እንዲለማመዱ ማድረግ እና ስለአተገባበራቸዉ ግብረመልስ መስጠት ናቸዉ።

ማስተዋል (1989) ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለመመርመር በአዲስ አባባ በሚገኙ አራት ትምህርት ቤቶች ጥናት አካሂዷል። የጥናቱን ዉጤት የተማሪዎች ችሎታ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ገልጻዉ፤ አጥኚዉ በአማርኛ የንባብ ትምህርት ክፍለ ጊዜ በፍል ዉስጥ ገብተዉ ባካሄዱት ምልከታ እንዳረጋገጡት ፤ ለሚሰጠመወ የንባብ ትምህርት የሚዘወተርዉ የማስተማሪያ ዘዴ የቃል ንብብ (oral reading ) ማለትም መምህሩ/ተማሪዉ ሲያነብ ተማሪዎች እንዲያደምጡ የሚከናወን ነዉ። ትምህርቱ አንብቦ መረዳት ሳይሆን አድምጦ መረዳት ነበር ። እያዳመጡ መሆናቸዉንም ቢሆን መምህሩ ክትትል አያደርጉም ። በመሆኑም ምንባብ ሲነበብ አንዳንድ ተማሪዎች ሌላ ተግባር ሲከናዉኑ  ይታያሉ። በጥቅሉ የትምህርት አቀራረቡ ለታየዉ ችግር የጎላ ድርሻ እንዳለዉ አመላክተዋል ። በተጨማሪም የመምህራን ተግባር ለተማሪዎች ድጋፍ መስጠት ፤ችግር ሲገጥማቸዉ መረዳት ፤መማር ማስተማሩን መቆጣጠር ሆኖ እያለ አብዛኛዎቹን ተግባራት መምህሩ በማከናወኑ የተማሪዎች የክፍል ዉስጥ የንባብ ልምምድ ዉስን ሆኖ መታየቱ ገልጸዋል ።

በተመሳሳይ ይታያል (2003) የንባብ ትምህርት አተገባበር ግምገማ በቡለን ወረዳ በተመረጡ ሦስት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ8ኛ ክፍል ተተኳሪነት ያካሄዱት ጥናት ዉጤት ፤በትምህርት ቤቶች ይከናወን የነበርዉ የአንብቦ መረዳት ትምህርት በጥናታዊ ዘዴ (traditional method) ላይ የተመሰረተ ዕንደነበር አመልክቷል ። በአብዛኛዉ ትምህርቱ የተከናወነዉ ምንባብ ድምጹን ከፍ በማድረግ ከተነበበ በኋላ ከምንባቡ የወጡ መልመጃዎችን በማሰራት ነዉ። ይህ አይነቱ አተገባበር ብቻዉን የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ያለዉ ድርሻ ዉስን መሆኑን ገልጸዋል ። ምክንያቱም ተማሪዎች የምንባቡን መልዕክት ለመረዳት የሚረዱ ስልቶችን ከመለማመድ ይልቅ መልመጃዎችን መስራት ላይ የሚያቶኩሩ ከሆኑ ተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታቸዉን ለማዳበር የጎላ ፋይዳ አይኖረዉም ። ይህ የሚዘወትር ከሆነ ተማሪዎች አንብቦ መርዳት ሲባል መልመጃ መስራት መሆኑን አምነዉ መልዕክት መልዕክቱን ለመመርመር የሚያሰችለዉን የማንበብ ሂደት ችላ እንዲሉ እና የማንበብን ዓላማ በተሳሳተ መልኩ እንዲገነዘቡት ያደርጋል ። ከጥናታቸዉ ዉጤት በመነሳትም መምህራን ስለንባብ ትምህርት አተገባበር ያላቸዉ ግንዛቤ ዝቅተኛ በመሆኑ የተዘጋጁ ጽሁፎችን በማንበብ እና ከሙያ አጋሮቻቸዉ ጋር በመወያየት ግንዛቤአቻን ለማዳበር ቢጥሩ የሚል ጥቆማ ሰጥተዋል።

ጥናቱ እንደሚጠቁመዉ የመምህራኑ የአንብቦ መረዳት ትምህርት አተገባበር ከተለመደዉ ያልወጣ መሆኑን ነዉ።በአብዛኛዉ ትኩረት የሚሰጡት ምንባቡ ድምጽን በማሰማት እንዲነበብ ማድረግ (በመምህራን ወይም በተማሪዎች)፤ተማሪዎች የሚያነቡከሆን ስህተታቸዉን እንዲያስተካክሉ እርማት በመስጠት እንደገና አስተካክለዉ እንዲያነቡ ማድረግ ላይ ያነጣጠረ ነዉ።ምንባቡ ከተነበበ በኋላም ከምንባቡ ለዉጡ ጥይቂዎችበቃል መልስ እንዲሰጡ ፤አልፎ አልፎም ጽፈዉ እንዲያነቡ በመጠየቅ ነዉ።

Kelarc እና Silberton (19997) በጥናታቸዉ ማመቃለያ ያቀረቡትን ዋቢ በማድረግ እንግዳ (1992) ሲገልጹ፤የተማሪዎችን አንብቦ የመርዳት ችሎታ የሚያዳብር መማር ማስተማር ሲታሰብ፣ ተማሪዎች የሚነቡትን ምንባብ ዓላማ እና ግን ወስነዉ እንዲነሱ ምቹ ሁኔታዎች መፍጠር እና ማለማመድ ፤እንዲያከናዉኗቸዉ በሚቀርብላቸዉ ትምህርታዊ ክንዉኖችመሰረት ተስማሚ የማንበብ ብልሀቶችን እንዲጠቀሙ ማለማመድ ራሳቸዉን ችለዉ እንዲጠቀሙባቸዉ እድሉን መስጠት፣ ድጋፍ ማድረግ ፤ቢሳሳቱም ተስፋ እንዳይቆርጡ ማበረታት እና ማስተካከያ መስጠት ፤ተማሪዎች የሚቀርብላቸዉ ምንባብ መልዕክት እንዲገምቱ ፤ግምታቸዉ ተክክል ካልሆነእንደገና ንዲገምቱ መጋበዝ ፤ ምንባቡ ዉስጥ አስፈላጊ የሆነዉን ሀሳብ መለየት እንዲችሉ መርዳት ፤ድህረ ንባብ መልመጃዎችን በሚሰሩበት ጊዜ ምንባቡን መልስ ብለዉ በመቃኘት መልዕክቱን መረዳት እና መገምገም እንዲችሉ ማበረታታት ፤ዉይይት እንዲያካሂዱ መጋበዝ ተገቢ መሆኑን አመልክተዋል።

## 2.5 በአንብቦመረዳትብልሀቶች /ተግባራትየክፍልዉስጥትግበራተጽዕኖየሚያሳድሩሁኔታዎች

### 2.5.1 የተማሪዎችተነሳሽነት

እንደ Tirheri እና Doctrew (2004) ገለጻ ተማሪዎች ራሳቸዉን እንደ አንባቢ ካልቆጠሩ እና ምንባቡን ለምን እንደሚያነቡ ዓላማ ካላስቀመጡ አንብቦ መረዳት ተግባራት አተገባበር ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል ፡፡Guthri እና ሌሎች (2006) በበኩላቸዉ ተማሪዎችን ለአንብቦ መረዳት የሚያነሳሱ የተለያዩ ተግባራት እና ሁኔታዎች አለመኖር /አነስተኛ መሆን ፤ለምሳሌ መምህሩ የሚነበበዉን ጽሁፍ ዓላማ ከተማሪዎችን ለማነሳሳት የማይጠቀምበት ከሆነ ፤የሚነበበዉ ጽሁፍ ከተማሪዎች ፍላጎት ጋር ካልተመጣጠነ ፤ በአንብቦ መረዳት ትምህርቱ መምህሩ ጣልቃ እየገባ የተማሪዎችአረዳድ ክትትል ካላደረገ ፤ለተወሰነ ጊዜን የማንበብ ተነሳሽነትን የሚያመጡ እንደ ሺልማት፣ምስጋና፤ዕዉቅና ምስጠት እና የመሳሰሉት ተግባራት የማይደረጉ/አነስተኛ ከሆን ተጽዕኖ እንደሚያደርስ ገልጸዋል ፡፡

እንደ Nga (2007) አገላለጽ ደግሞ የተማሪዎች ተነሳሽነት ዝቅተኛ መሆን የመምህራንን የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች አቀራረብ ተነሻሽነት ይቀንሳል፡፡

### 2.5.2 በአንድክፍልዉስጥየሚገኙተማሪዎችብዛት

በአንድ መማሪያ ክፍል ዉስጥ ከሚሚፈለገዉ መጠን በላይ ተማሪዎች መኖር በመማር ማስተማሩ ሂደት ችግር መፍጠሩ አይቀሬ ነዉ፡፡ Deighton (1971) እንደገለጹት ብዛት ያላቸዉ ተማሪዎችበሚማሩበት ክፍላ ዉስጥ ተማሪዎች ፤የማዳመጥ የማናገር ፤የማንበብ እና የመጻፍ ክህሎት የማጎልበት እድላቸዉ ዝቅተኛ ነዉ ፡፡መምህሩ እያንዳንዱ ተማሪ የሚተገብረዉን ለመከታተል ፤ድጋፍ ለማድረግ እና ተገቢ ግብረ መልስ ለመስጠት አስቸጋሪ ይሆናል ፡፡

### 2.5.3 የተማሪዎችቅድመእዉቀትእናየቋንቋችሎታመለያየት

Fieding እና Pearson (1994) ጠቅሰዉ Tereheri እና Doctrew (2004)፤ Conley (1992) እና Aloqaili (2012) ሲገልጹ ፤ የቅድመ እዉቀት በአንብቦ መረዳት ትምህርት አተገባበር ላይ አዉንታዊ ወይም አሉታዊ ተጽእና ያሳድራል ፡፡ስለሚነበበዉ ጽሁፍ በቂ ዳራዊ እዉቀት የሌላዉ ተማሪዎች ጽሁፍን አንብበዉ የመረዳት ተነሳሽነታቸዉ አነስተኛ ነዉ ፡፡ ይህም ለመነበብ ከቀረበዉ ጽሁፍ ተጨማሪ አዉቀት ለማግኘት የሚያደርጉትን ጥረት እና መከወን ያለባቸዉን ተግባራት ይገደባል፡፡ እንደ Androwed (1987) አገላለጽ በአንድ የመማሪያ ክፍል ዉስጥ ያሉ ተማሪዎች የተለያየ ዳራዊ እዉቀት እና የቋንቋ ችሎታ እንደሚኖራቸዉ ኤጠራጥርም ፡፡ በመሆኑም በመማር ማስተማሩ ይህን የመፈተሻ ተግባር ቅድሚያ ሊሰጠዉ የሚገባ ጉዳይ ነዉ፡፡

### 2.5.4 አቀላጥፎአለማንበብ

አቀላጥፎ ማንበብ አንባቢዉ ቃላትን ከጽሁፍ ጋር በማገናኘት በትክክል የማወቅ ፤ጽሁፍን በተገቢዉ ሁኔታ እና ፍጥነት የማንበብ እና የመረዳት ችሎታ ነዉ፡፡ አቀላጥፎ ማንበብ ደረጃ መድረስ እንባቢዉ መረዳት ላይ እንዲያተኩር የሚስችል አላባ ነዉ፡፡ በተቃራኒ አቀላጥፈዉ የማነቡ ተማሪዎች ጽሁፍን በጥርጣሬ እና ያለስሜት ስለሚነቡ በአንብቦ መረዳት ትምህርት አተገባበር ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል ( Onthario 2003)፡፡

### 2.5.5 ወቅታዊ ስልጠና እና የልምድ ልዉዉጥ

በመማር ማስተማር ሂደት ተፈላጊ ተግባራትን ለማከናወን ፣በተለይ የመርሀ ትምህርት ማሻሻያ ሲደረግ መምህራን ወቅታዊ ስልጠና እንዲያገኙ እና የርስበርስ ልምድ ልዉዉጥ እንዲያደርጉ ምቹ ሁኔታን መፍጠር ጠቀሜታዉ የጎላ ነዉ፡፡ Nega ( 2007) ስድስት የቪይት ጋ ሁለተኛ ደረጃ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህራንን የጥናቱ ተሳታፊ በማድርግ መምህራን ስለአናብቦ መረዳት ብልሀቶች ያላቸዉን አመለካከት እና የክፍል ዉስጥ አተገባበር መርምረዋል ፡፡የጥናቱ ዉጤት በመምህራን መካከል የአመለካከት ፤ የጽንስ ሀሳብ እና የአተገባበር ልዩነት መኖሩን አመልክቷል፡፡ ይህን ልዩነት ለማጥበብ መምህራን ተገቢ ሙያዊ ስልጠና እንዲያገኙ እና የርስበርስ ልምድ ልዉዉጥ እንዲያደርጉ እድል መስጠት እንደሚያስፈልግ ተጠቁሟል፡፡

ንባብ ፊደላትን ማንበብ ብቻ ሳይሆን ፊደላቱ ተቀናጅተው የሚመሰርቱትን መዋቅር መረዳትን (መተርጎምን) ጭምር ይጠይቃል፡፡ ተማሪዎች የሚያነቡትን ነገር በወጉ መረዳት ይችሉ ዘንድ ንዑስን የምንበብ ክሂሎችን (sub reading skills) ማዳበር ይጠበቅባቸዋል፡፡ የንዑሳን የንባብ ክሂሎች አጠቃቀም ተማሪዎች ከሚያነቡት አላማ አንፃር ተግባራዊ የሚያደርጓቸው የንባብ አይነቶችና ስልቶች ጋርም የተያያዘ ነው፡፡ በአጠቃላይ የንባብ ትምህርት የተማሪዎችን በፍጥነት በትክክል ያለችግር የማንበብና የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ያስችላል፡፡ በዚህ ረገድ የተለያዩ ምሁራን ጥናቶች አገላለፅ መሰረት የአንብቦ መረዳት ክሂልን የተመለከቱ አስተያየቶች አሏቸው፡፡

እንደ Ephram(2009) ገለፃ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ተማሪዎች አድስ ዕውቀት እንድገበዩና ህይወታቸውም የተሳካ እንድሆን ያስችላል በማለት የዚህን ክሂል ጥቅም ገልፀዋል፡፡ በተመሳሳይ ደግሞ Moets(1999) ሲፈልፁ ተማሪዎች በማንኛውም ትምህርት የተሻለ እውቀት እየገነቡ የመቀበል ህልውና በአንብቦ መረዳት ችሎታ ላ የተመሰረተ ነው፡፡ በአንፃሩ ይህ ብቃት ከሌላቸው ማንኛውም ትምህርት ለመማር ይቸገራሉ፤ ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች መረጃ የምግኘት ብቃታቸው ደካማ ይሆናል ሲሉ የዚህን ክሂል ጉልህ ጥቅም ያስረዳሉ፡፡

መምህራን የአንብቦ መረዳት ትምህርት የማስተማራቸው አስፈላጊነት ተማሪዎቻቸው በክፍል ውስጥ የሚማሩት የትምህርት ይዘት ለማሳካት ብቻ ሳይሆን በዕለት ከዕለት ህይወታቸው የሚያከናውኗቸውን ተግባራት እንዲያሳኩ ጭምር ነው በማለት Thunkersly(2005) እና Ephram(2009)ይገልፃሉ፡፡ ይህ ደግሞ አንብቦ መረዳት ለመምህራን የማስተማር ውጤትን ለማምጣት የሚያስችል ጥናት ያለው መሆኑን ያስገነዝበናል፡፡ በሌላ በኩል Conley(1992)፣ Alicouly(2012) እና አጀድሄ(2006) እንደገለፁት በአንብቦ መረዳት ሂደት የአንብቦ መረዳትን

ለማጎልበት የሚያስችሉ የተለያዩ ብልሀቶች ቢኖሩም የአንባቢውን የቀደመ እውቀት በማነሳሳት ወይም በመገንባት አድስ ከሚቀርበው ዕውቀት ጋር ማገነኘት መዘንጋት የሌለበት ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡ ምክንያቱም የቀደመ ዕውቀት በአንብቦ መረዳት ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ ከፍተኛ ነውና ይላሉ፡፡ ከነሱ ገለፃ የተወሰደው ቁምነገር በአንብቦ መረዳት ሂደት የአንባቢውን የቀደመ እውቀት መቀስቀስ ለአንብቦ መረዳት ጉልህ አስተዋፅኦ ያለው መሆኑን ነው፡፡ በአጠቃላይ የአንብቦ መረዳት ክሂክል ያለፈን መረጃ ከአድሱ መረጃ ጋር ለማገናኘት የሚያስችል የወደፊቱን ለመተንበይ የሚረዳ በተማሪዎች ዘንድ ይህ ብቃት ሲረጋገጥ ለንባብ የቀረበውን ፅሁፍ መረጃ በመለየት መረዳትና በመተርጎምና በመጠቀም ለተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ዕውቀት ማደግ ጠንካራ መሰረት የሚጥል መሆኑን የምሁራን ገለፃዎች ይናገራሉ፡፡ ስለሆነም ተማሪዎች በዚህ ጥናት ክልል ውስጥ ያላቸውን የአንብቦ መረዳት ግንዛቤ አተረጓጎም አረዳድና አጠቃቀምን ለማጥናት መነሻ ሀሳብ ማግኘት መቻሉን አጥኚው አረጋግጧል፡፡

### 2.1.3. የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች አስፈላጊነት

የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች ማንበብና (ንባብን) ለመተግበር የሚያስችሉ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ በትምህርት የቀረበውን የተለያዩ ቴክስቶች(ንባባት) አንባቢዎች በንቃት ተከታትለው በማንበብ እንድረዳዱና ባልተረዱም ጊዜ ደግሞ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ያመለክታሉ፡፡ ውጤታማ መምህራን ንባብን የማስተማሪያ በተለይ ደግሞ የአንብቦ መረዳት የማስተማር ዘደዎችን ተጠቅመው የቀደመ እውቀታቸውን ምንባቡን ከማንበባቸው በፊትና እያነበቡም እያለ እንዳሰላስሉና እንድገምቱ ለማድረግ በአዕምሯቸው ምስል በመፍጠር በንቃት እንድያነቡ በማድረግ በመርዳት ጥያቄዎችን በመርሁ መሰረት በመጠየቅና ምላሽ እንድሰጡ ዕድል በመስጠት የፅሁፉን ሀሳብ በራሳቸው አባባል እንድገልፁና ማጠቃለያ እንድሰጡ ብልሀቶች ከተግባራቱ ጋር በማዋሀድ እንድያነቡ ይጋብዛሉ፣ ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡ Davis(2011) እና Onthario (2003)ሲሉEphram (2009) Dik and Pirson (2003) ን ጠቅሰው Folio(2011) እንደገለፁት የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች የየራሳቸው መጠሪያና ምንነት ቢኖራቸውም ትምህርቱ በራሱ በአንድ ወይም በተናጠል የሚከወን አይደለም፡፡ ከዚህ በበለጠም አንዱ ከአንዱ ጋር የተሳሰሩና በቅንጅት እየተተገበሩ ተጋባብተው የሚሄዱ ናቸው፡፡ አንባቢዎችና የብልሀቶቹን ምንነትና አጠቃቀም ማወቃቸው በየስልታቸው በቅድመ ንባብ፣ በንባብ ጊዜና፣ በድህረ ንባብ ጊዜ እንድኖራቸው የሚጠበቀውን ዕውቀት ለመያዝ ትምህርቱን ለመከታተልና ፍላጎት እንድኖራቸው በዚህ ረገድ ተጠኝዎች ያላቸው የመተግበር ደረጃ ያለበትን እንድያከናውን ይረዳል፡፡

እንደAdjudhi (2006)፣ Alicuouly(2012) እና Ephram (2009) አገላለፅ በአንባቢዎችና በፅሁፍ መካከል የሚደረግ ብላሀታዊ መስተጋብር ለአንብቦ መረዳት መሰረት ይጥላል፡፡ የአንብቦ መረዳት ችሎታን በማጎልበት ረገድ አጋዥ የሆኑ የተለያዩ ብልሀቶች አሉ፡፡ የቀደመ እውቀት በመቀስቀስ ወይም ደግሞ ዳራዊ ዕውቀት ማነቃቃት(መቀስቀስ) የተማሪዎችን ዳራዊ ዕውቀት ማነቃቃት ወይም ማለት ነው፡፡

ስለሚያነቡት ፅሁፍ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ከዚህ በፊት የሚያውቁት ይኖራል፡፡ ሆኖም ስለሚያውቁት ነገር መኖሩን ልብ ላይሉት ወይም ሊያስቡት ይችላሉ፡፡ ስለሆነም ለማነቃቃት ስለሚያነቡት ፅሁፍ ከዚህ በፊት ምን እንደሚያውቁ መጠየቅ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ሂደት የዳራዊ

እውቀታቸው በቂ መሆን አለመሆን ወይም የተለያዩ (የተዛባ) መሆኑንና አለመሆኑን ከተማሪዎቹ የአቀባበል ደረጃ ጋር ለማረጋገጥ ያግዛል፡፡ በተመሳሳይ Onthario(2003) እና Block(1997) እንደገለፁት አንባቢዎች በቅድመ ንባብና በድህረ ንባብ ጊዜ የቀደመ ዕውቀታቸውን ተጠቅመው ቢያነቡ ፅሁፉን ከዚህ በፊት ካነበቡት ፅሁፍና ከአንባቢያቸው ዳራዊ እውቀት ነባራዊ ሁኔታ ጋር አረዳድተው ከፍ እንድል ያደርጋል፡፡ የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች (resprocal teaching) በአራት ብልሀቶች ላይ ያተኩራል፡፡ ማለትም መገመት፣ ማብራራት፣ ጥያቄና መልስ ብልሀቶች ናቸው፡፡ Roniros(2006)ን ጠቅሰው Ephram(2009)በተመሳሳይ እንደገለፁት በአንብቦ መረዳት ትምህርት ተማሪዎችን የሚረዱ ወሳኝ ብልሀቶች አሉ፡፡ እነሱም መገመት በራስ አባባል መግለፅ ጥያቄና መልስ ማጠቃለያ ናቸው፡፡ ከዚህ ብያኔ በመነሳት በዚህ ጥናት የመምህራን አተገባበር ከዚህ ጋር ምን ያህል ተያያዥነትና ተተግባሪነት እንዳለው ይህን ዕውቀት ለማስጨበጥ እንደሚጠቅም ጥናቱ በዚህ ቲዎሪ ውስጥ መተግበሩን ማየት ያስፈልጋል፡፡

### 2.1.4. የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር

#### 2. 1.4.1. በቅድመንባብ ጊዜ ንባብና ድህረ ንባብ ጊዜ

አንብቦ መረዳት ከአንድ ፅሁፍ ተፈላጊ መረጃ ማግኘት መቻል ነው፡፡ ይህ በአንድ ጊዜ የሚዳብር ሳይሆን በንባብ ሂደት ደረጃ በደረጃ የሚደረግ አዕምሯዊ ክንውን ወይም ብልሀታዊ ልምምድ የሚመጣ ዕድገት ነውThunkersly(2005)፡፡ የአንብቦ መረዳት የአንድን ፅሁፍ ሀሳብ መገንዘብ የሚጠይቅ ውስብስብ ሂደት ነው፡፡ በመሆኑም ተግባራቱን በቅድመ ንባብ በንባብ ጊዜና በድህረ ንባብ ጊዜ በሚሉ ደረጃዎች በመከፈል በአግባቡ መከወን እንደሚጠይቅ Onthario(2003) ገልፀዋል፡፡ Thomson(2007)ን ገልፆ Ephram (2009) እንደሚያስረዱት ተማሪዎች ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት ስዕልን ካርታን አብይና ንዑሳን ርዕሰ ጉዳዮችን ወዘተ በመመርመር ስለ ፅሁፉ ይዘት እንደገምቱ በማድረግ የቀደመ ዕውቀታቸውን ማነሳሳት ይገባል፡፡ ይህም ተማሪዎች ወደ ማንበቡ ተግባር ከመግባታቸው በፊት ከርዕሱ ከስዕሉ ከተዛማጅ ፅንሰ ሀሳቦች ወዘተ በመነሳት ጥያቄዎችን መጠየቅና ሀሳባቸውን እንድሰነዝሩ በማድረግ ማነቃቃት ይጠይቃል ይህ ካልሆነ ግን የማንበብና ዓላማ ማሳካት አይችልም ይላሉ፡፡ ስለዚህ ይህ ጥናትም የመምህራንን የአንብቦ መረዳት የክፍል አተገባበር በዚህ ደረጃ ከላይ የተጠቀሱትን የአተገባበር ሂደት ቅደም ተከተሎች የምሁራን ሀሳብ ተመስርቶ በክፍል ውስጥ እየተሰራበትና ተሰርቶበትም ስለሚገኘው ውጤት በማጥናት ታስቦ የሚደረግ ነው፡፡

የማንበብ ክሂል ትምህርት ዓላማ ያለው መሆን አለበት፡፡ ተማሪዎች አንድን ፅሁፍ ከማንበባቸው በፊት አስቀድመው የሚያነቡትን ፅሁፍ ዓላማ ወይም እንደሚያነቡ በአግባቡ ሊያውቁ ይገባል፡፡ ብዙ ጊዜ የተለመደው አተገባበር ተማሪዎች አንድን ፅሁፍ በማስከተል በምንባቡ መሰረት የሚመልሱ ጥያቄዎችን ማቅረብ ነው፡፡ ይህ ከሆነ አስቀድሞ የተነበበው ፅሁፍ አላማ አልባ ነበር(ማረው1998)፡፡ ስለዚህ ጥናቱ መምህራን በዚህ አንፃር ያላቸው የክፍል ውስጥ አተገባበር ያለበትን ሁኔታና ያስከተለውን ተፅዕኖ መፈተሽ ላይ ተመስርቶ እንዲከናወን ይደረጋል፡፡

### 2.1.5. በአንብቦ መረዳት ብልሀቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ላይ ተፅዕኖ ሁኔታዎች /ተላወጦዎች/

#### 2.1.5.1. የተማሪዎች ተነሳሽነት

እንደ Thirhair and Doctrow(2004)አባባልተማሪዎች ራሳቸውን እንደ አንባቢ ካልቆጠሩ እና ምንባቡን ለምን እንደሚያነቡ ዓላማ ካላስቀመጡ በአንብቦ መረዳት ተግባራት አተገባበር ላይ ተፅዕኖ ላይ ያሳድራል፡፡ Guter andetal (2006) በበኩላቸው ተማሪዎችን ለአንብቦ መረዳት የሚያነሳሱ የተለያ ተግባራቶችና ሁኔታዎች አለመኖር /አነስተኛ መሆን ለምሳሌ መምህሩ የሚነበበው ትምህርት ፅሁፍ ከተማሪዎች ፍላጎትና የክፍል ደረጃ ጋር ካልተጣጣመ በአንብቦ መረዳት ሂደት መምህሩ ጣልቃ እየገባ ክትትል ካላደረገ በተወሰነ ጊዜ የንባብ ተነሳሽነትን የሚያመጡ ተግባራትን ካላደረገ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር ገልፀዋል፡፡

እንደ G.Negga(2007) አገላለፅ ደግሞ ተማሪዎች ተነሳሽነት ዝቅተኛ መሆን የመምህራንን የአንብቦ መረዳት አቀራረብ ብልሀት ተነሳሽነት ይቀንሰዋል፡፡ ስለዚህ ከተነሳሽነት (ከተማሪዎች ተነሳሽነት አንፃር የተገለፁት የምሁራኑ ትንታኔ በዚህ ጥናት ውስጥ የሚያሳድሩት ተፅዕኖ መኖር አለመኖሩን በዚህ ደረጃ ተጠኝ የሆኑት ክፍሎች ያላቸው የክፍል ውስጥ መስተጋብር ከዚህ አንፃር እንዲፈተሽ ማድረግ የጥናቱ ዋና አካል ሆኖ ይጠናል፡፡

## 2.3 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ጥናቶችና አንብቦ መረዳትን የተመለከቱ የቴክስት ውቅር ብልሃቶችንና የመምህራንን የክፍል ውስጥ አተገባበር ከተለያዩ የክፍል ደረጃዎች አቀራረብ አንፃር የተሰሩ ስራዎች ከጥናቱ ጋር ባላቸው ተዛማጅነት ምክንያት እንዲወሰዱ የተደረጉ ስራዎች አሉ፡፡

ከነዚህም ውስጥ የሚጠቀሱት የሙሉ ገበያው(2009)እና የጥሩወርቅ አይሸሽም(2008) ስራወች ተጠቃሽ ናቸው፡፡የጥናታቸውም መሰረታዊ አካሄድ በሚከተለው መልክኩ ይቀርባል፡፡ሙሉ ገበያው(2009) ጥናታቸው የተመሰረተው በአድስ ዘመን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ሲሆን ይዘቱ ያተኮረው በቴክስት ውቅር ብልሃቶች ሆኖ ዋነኛ አላማቸው መምህራን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማጎልበት የፅሁፍ ውቅርን እንዴት ማስተማር እንደሚችሉ ማሳየት ላይ ነው፡፡

ጥሩወርቅ አይሸሽም(2008) በበኩላቸው ያጠኑት ጥናት የሚያመለክተው በደብረብርሃን ከተማ በሚገኙ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአንደኛው ሳይክል ከአንደኛ እስከ አራተኛ ክፍል ባሉ የክፍል ደረጃዎች በናሙና ምርጫቸው በአራተኛ ክፍል ተተኳሪነት ሆኖ መሰረታቸውም በአድሱ አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ የአንብቦ መረዳት ብልሃት አተገባበር የተሰራውን ስራ ውጤታማነት በመፈተሽ ላይ ነው፡፡

በዚህ በተጨማሪ የ"እንግደ" /1992/ ጥናት የሚመለከተም የቶፐደውን /የቀደመ እውቀትን መሠረት ያደረገ/ የንባብ ማስተማሪያ ሞደል በአማርኛ ቋንቋ አንባቢ መረዳት ቶሎታ ማደበር ላይ የተግባሪዊነትና ውጤታማነት ለመመርመር መከራዊ ጥናት ሲሆን በ9ኛ ክፍል በድን ላይ በንባብ ትም/አቀራርበ ላይ ያተኮር ነው የኔ ሰው /1990/ በበኩለኛዊ አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማሩና /ኦሮመኛ ቋንቋዎችን የፊቱ/ የተማሪዎችን አንብቦ መረዳትን ክሂላቸውን ለማደበር ታሪክቧዊ (Interativc)ሞደል አስተዋፅኦ በባሌዘን አደበ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ለዘጠኝ ቡድኖች በተረክቧዊ የንባብ ክፍል ማስተማሪያነት ሞዴል መሠረት በተዘጋጀ የማስተማሪያ መሳሪያዎችና የክፍል ውስጥ ሞዴል መሠረት በተዘጋጀ የማስተማሪያ መሳሪያዎችና የክፍል ውስጥ ሞዴል መሠረት በተዘጋጀ የክፍል ውስጥ ክንውን የተክቧዊ ሞዴል ማስተማር ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

እንዲሁም ከላይ ከተቃኙት መረጃዎች ሌላ አጥኒው ከርዕስ ጋር በተዛማጅነት ሊጠቀስ የሚችል የአንድረስ /2000/ ጥናት ነው፡፡ በጥናቱ እንደተመለከተው ብልሀቶችን የተማሩ ተማሪዎች ብልሀቶችን ካልተማሩት ተማሪዎች የላቀ የአንብቦ መረዳት ውጤት አስመዝግበዋል፤ በዚህም መሰረት ብልሀቶችን የተማሩ ተማሪዎች በብልሀቶች አተገባበር ዙሪያ የነበራቸው ዝቅተኛ ግንዛቤ ተሻሽሎ በመታየቱ ብልሀቶችን መማር እንደሚያስፈልግ ጠቁሟል፡፡

የእንድሪስ /2000/ ጥናት በአንብቦ መረዳት ብልሀቶች ላይ በማተኮሩ ከዚህ ጥናት ጋር በተወሰነ መልኩ ቢመሳሰልም በሌላ በኩል በሰፊው ይለያል፡፡ ይህ ጥናት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሀቶችን የክፍል ውስጥ አተገባበር በ9ኛ 10ኛ ክፍል ደረጃ የሚፈተሽ ሲሆን የእንድሪስ ጥናት የአንብቦ መረዳት ብልሀቶችን መማር ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለውን ተዛምዶ ለመመርመር አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ በሙከራዊ ጥናት የተካሄደ ነው፡፡

ከላይ ከቀረቡት የውጭ ጥናቶች የኦትማንና ዛሪ /2013/፣ የፎሊ /2011/ እና የንጋ /2007/ ጥናቶች በአንብቦ መረዳት ብልሀቶች ላይ ያተኮሩ ሲሆን ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳሳይነትም ልዩነትም አላቸው፡፡ የኦትማንና ዛሪ /2013/ ጥናት እንግሊዝኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ የማሌዥያ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ብልሀቶችን አጠቃቀም ሁኔታ ፣ በአንብቦ መረዳትና የማንበብ ብልሀቶች መካከል ያለውን ግንኙነት ያጠና ነው፡፡ የፎሊ /2011/ ጥናት በቅድመ መደበኛ የክፍል ደረጃዎች የመምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች አተገባበርና በአተገባበር ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ተላውጦዎችን የመረመረ ሲሆን የንጋ /2007/ ጥናት ደግሞ መምህራን ስለአንብቦ መረዳት ብልሀቶች ያላቸውን እምነትና የክፍል ውስጥ አተገባበር ሁኔታ የፈተሸ ነው፡፡ ጥናቱ ቬትናም ውስጥ በሚገኝ አንድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ መምህራንን የጥናቱ ተሳታፊ በማድረግ የተካሄደ ነው፡፡ በአጠቃላይ ከላይ የተጠቀሱት ተዛማጅ ጽሁፎች አስተዋጽኦቸው የጐላ ነው፡፡ ስለሆነም ይህ ጥናት ከላይ የተጠቀሱትን ጥናቶች በተገቢነታቸው ላይ ተመስርቶ በዋቢነት የሚጠቀምባቸው ሲሆን በመሰረታዊ ብልሃቶቹ ላይ ክንውኑን መገምገምና ውጤቱን ለመለካት በሚያስችል የጥናት ስልትና ዘዴ መሰረት ተዘጋጅቶ ተጠንቷል፡፡

## □□□□ □□□

## □□□□ □□□ □□□□

በዚህ ክፍል ዉስጥ ጥናቱ ትኩረት በሚያደርግበት በ9ኛና በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ትምህርት የአንባቦ መረዳት የመማር ማስተማር ሂደት የመምህራን የክፍል ዉስጥ አተገባበር መመርመር ላይ ነው፡፡ ስለሆነም ጥናቱን ለማጥናት የምርምር /የጥናቱ /የአጠናን ዘዴ በሚያቅፋቸዉ ርእስ ጉዳዩች ዙሪያ ጥናቱ የሚከተላቸዉን ስልቶች ለማሳየት የሚቻልበት ክፍል ነው፡፡

### 3.1 የጥናቱ ስልት

ጥናቱ የተከተለው ስልት አይነታዊ የምርምር ስልት ሆኖ በገላጭ የምርምር ስልት ገምጋሚ (Evaluate research) ሂደትን የሚከተል ስልት ነው፡፡ ይህ የምርምር ስልት የተመረጠበት ምክንያትመምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሀትን ተጠቅመው የክፍል ውስጥ አተገባበራቸው እንዴት እንደሆነ ለመረዳት በቂ መረጃ ሊሰጥ ስለሚችል ነው፡፡ አሰራሩን በመከተል ዉጤቱንበደንብ ለማየት በ9ኛና 10ኛ ክፍልበእዉነተኛዉ አዉድ ዉስጥየሚከናወነዉን ትግበራ ማየት ስለሚያስችለን ነዉ፡፡

### 3.2 የጥናቱ ተሳታፊዎች አመራረጥ

የጥናቱ አካላይ በደቡብ ወሎ የተንታና መቅደላ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መምህራን ላይ ተተኳሪ ሆኖ በተጠቀሱት ሁለት ወረዳዎች ማለትም ከተንታ ወረዳአጅባር፣አስፋወሰን፣ ወርጠጅና ደበቅ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 14 የዘጠነኛ ክፍል መምህራንና 13 የአስረኛ ክፍል መምህራን ይገኛሉ፡፡ በአጠቃላይ ከዚህ ወረዳ 27 የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ሲገኙ በተመሳሳይ ከመቅደላ ወረዳ የመቅደላ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በዘጠነኛ ክፍል 2 የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና 2 የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ይገኛሉ፡፡ በአጠቃላይ በሁለቱ ወረዳወች በዚህ ጥናት ተሳታፊ የሚሆኑት መምህራን ከየትምህርት ቤቱ በተገኘው መረጃ መሰረት 31 መምህራን የጥናቱ ተሳታፊ ሆነው ጥናቱ በተመረጠው የመረጃ አሰባሰብ ስልት መሰረት ተከናውኗል፡፡

ለዚህ ጥናት የዘጠነኛና የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተመረጡበት ምክንያት በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች የሚገኙት ተማሪች የአንብቦ መረዳት ችግር እንዳለባቸው በስራው መስክ በመስማራት በየጊዜው ያላቸውን ብቃት ለመረዳት በመቻሉ ነው፡፡

ስለሆነም  በአማርኛ ቋንቋ የአንብቦ መረዳት የመምህራን የክፍል ውስጥ አተገባበር ላይ ቢያተኩር የተሻለ ውጤት ያመጣል ተብሎ ታምኗል፡፡ ስለሆነም ወደፊት በሚገኘው ውጤት መሰረት በሚደረግ ድጋፍ የመምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሀት የክፍል ውስጥ አተገባበር እየተሻሻለ ሲሄድ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የሚማሩት የዚህ ጥናት ተካላይ ተማሪዎች ወደፊት ለሀገር የሚጠቅምና የቋንቋውን እድገት ለማምጣት አስተዋፅኦ ሊኖራቸው ይችላል፡፡

የጥናቱ አካላዬች በደቡብ ወሎ ዞን ከሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ሲሆኑ በናሙናነት የተመረጡት በተንታና መቅደላ ሁለተኛ ደረጃ የ9ኛ የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ናቸው፡፡ የተመረጡት ትምህርት ቤቶች ከአጠቃላይ የተጠኚዎች ቁጥር ስፋት አንጻር በተጠቀሱት ወረዳዎች 30 እና በላይ /30 ተደምሮ 1/ መሆን እንድችሉ ተደርጐ ቁጥሩን ለመወከል በሚያስችል ሁኔታ በናሙናነት ተወስዷል፡፡

## 3.3 የመምህራን ናሙና አመራረጥ ዘዴ

በዚህ ጥናት ተጠኚ መምህራን አመራረጥ በተመለከተ የጥናቱ ተሳታፊ መምህራን ከዚህ በታች በተጠቀሱት ወረዳዎች ሁሉም የ9ኛ 10ኛ ክፍል መምህራን ላይ ያተኩራል፡፡ በዚህ መሰረት በተንታና መቅደላ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ናየ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን የሚያስተምሩ መምህራንን በጠቅላይ ናሙና አመራረጥ ዘዴ (comprehensive sampling) 31 መምህራን በጥናቱ ውስጥ ተካተዋል፡፡

ለዚህ ጥናት ይህ ናሙና የተመረጠበት ምክንያት የመምህራን የአንብቦ መረዳት ብህሃት የክፍል ውስጥ የተሳታፊዎች ቁጥር በትክክለኛው አውድ ለመውሰድ ስለሚያስችል ነው፡፡

### 3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ለጥናቱ አላማ መሳካት በስራ ላይ ከሚውሉት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አተገባበራቸውን ለመለካትና ያላቸውን ግንዛቤ ከአንብቦ መረዳት የክፍል ውስጥ አተገባበር ጋር አገናኝቶ ለመመርመርና የመምህራኑን ግንዛቤ ለመገምገም እንድሁም አንብቦ መረዳትን የተመለከቱ የማስተማር ዘዴዎችን አጠቃቀም የተመለከቱ መረጃዎች ለማግኘት እንዲቻል በመረጃ መሰብሰቢያነት ምልከታና ቃለ መጠይቅ በስራ ላይ እንዲውሉ ተደርጓል፡፡

3.4.1 ምልከታ

በተተኳሪው የክፍል ደረጃ በ9ኛና 10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ትምህርትን ሲያካሂዱ በመማሪያ ክፍል ውስጥ በፊት ለፊት ተገኝቶ የአንብቦ መረዳት መማር ማስተማር ሂደቱን በአንብቦ መረዳት ብልሀቶች የማስተማር ዘዴ ላይ ተመስርተው ስለማስተማራቸው እና አለማስተማራቸው ተከታታይ ምልከታ ተካሂዷል። የምልከታው ትኩረት በአንብቦ መረዳት የክፍል ውስጥ አተገባበር ቅድመ ንባብን፣ ጊዜ ንባብን እና ድህረ ንባብ አተገባበር እና በአንብቦ መረዳት ተግባራት ላይ የተመሰረቱ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች እና ምዘናዎች በአግባቡ መከናወንና አለመከናዎናቸውን ለመፈተሽ የሚጥር ምልከታ ተደርጓል።

ምልከታውከመከናወኑበፊት የመምህራኑን የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ለመፈተሽ የሚያስችል ቅጽ ለማዘጋጀት የሳሪጅን (1997)ን ሞደል ተክላይ (2000) በትግረኛ ቋንቋ አፋቸውን የፊቱ አስራ ሁለት የ8ኛ እና የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ንባብ ጊዜ የንባብ ብልሀት አጠቃቀምና የመምህራን ግንዛቤ ተጣጥሞ ለመፈተሽ በጥናታቸው የተጠቀሙበትን መነሻ በማድረግ የ9ኛ 10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመምህርና የተማሪ መጻህፍት ከመነሻ እስከ መጨረሻ በማየት ከተዘጋጀ በኋላ የጥናትና ምርምር ልምድ ባላቸው አንድባለሙያ ለማየት ተሞክሯል። የምልከታ ቅጹ፡- የቅድመ ንባብ፤ የንባብ ጊዜና የድህረ ንባብ የአንብቦ መረዳት ብልሀቶችን የክፍል ውስጥ አተገባበር ሁኔታ ለመገምገም የሚያስችሉ 18 የቅድመ ንባብ ፣ 8 የግዜ ንባብ እና 8 የድህረ ንባብ በድምሩ 34 ተግባራትንና የትግበራ መጠን በሚገልጽ መልኩ ከፍተኛ (4)፤ መካከለኛ (3)፤ ዝቅተኛ (2) እና በጭራሽ (1) በሚሉ አራት ደረጃዎች የተዘጋጀ ነው።

ከዚህም ሌላ ምልከታውን በአጥኚው ብቻ ለማከናወን አስቸጋሪ ስለሆነ በሁሉም ተጠኚ የ2ኛ ደረጃ ት/ቤት የት/ቤቶች የት/ት ተጠሪዎች ጋር በተፈጠረ መግባባት በዚሁ ስራ የተሻለ በጉድኝት ደረጃየሱፐርቪዥን ድጋፍ በሚሰጠው የጉድኝት ሱፐርቪዘር በእንግሊዝኛ ትም/ 2ኛ ድግሪ ያላቸዉ ባለሙያ እንድደግፉኝ በማድረግ የአንብቦ መረዳት ብልሀት ላይ ባለው የተሻለ ግንዛቤ መሠረት በተባባሪነት ጥናቱን አብረዉኝ እንድሰሩ በማድረግ በተግባቦት ተከናውኗል። በተጨማሪም ምልከታው ከመከናወኑ በፊት ለጥናቱ ተሳታፊ መምህራኑ ስለጥናቱ ዓላማ በአጥኚው ገለጻ ተደርጎ ፍቃደኛ መሆናቸው ተረጋግጧል። በእያንዳንዱ መምህር 2 ክፍለጊዜ በድምሩ በ9ኛ ክፍል 16 ሴክሽን 10ኛ 15 ሴክሽን በድምሩ 62 ክፍለ ጊዜ የክፍል ውስጥ ምልከታ ተከናውኗል።

3.3.2 ቃለ መጠይቅ

በዚህ ጥናት ቃለመጠይቅ ጥቅም ላይ የዋለው በክፍል ውስጥ ምልከታ የተገኘውን መረጃ ለማመሳከርና በምልከታ የማይገኙ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ታስቦ ነው። የተመረጠው የቃለመጠይቅ አይነት ከፊል ነፃ ቃለመጠይቅ (semi structured interiew) ሲሆን ይህ የቃለ መጠይቅ አይነት የተመረጠበት ምክንያት መላሹ ሀሳቡን እንዲገልጽ የሚያደርግ በመሆኑ ነው፤ ጠያቂውንም ከግል

ሀሳባዊነት ለመቀነስ ስለሚያስችል ነው። የቃለ መጠይቁ ጥያቄዎች የክፍል ምልከታውን መሰረት ያደረጉ አስቀድመው ያልተወሰኑ ጥያቄዎች ናቸው። በመሆኑም ለአንዱ የጥናቱ ተሳታፊ መምህር የቀረቡ ጥያቄዎች ለሌላኛው መምህር ከቀረቡት ጥቄዎች የተወሰኑት አንድ አይነት ሲሆኑ የተወሰኑት ደግሞ መጠነኛ ልዩነት አላቸው። ይህም በየጥያቄዎቹ ጎን ጥያቄዎች ለማን እንደቀረቡ የተገለጸ ሲሆን ባጠቃላይ 20 የግንዛቤ መመዘኛ ጥያቄዎች እና ተግባራቱን/ብልሀቶችን በክፍል ውስጥ ሲተገብሩ ተጽዕኖ ያሳደሩ ሁኔታዎችን የሚያመላክቱ 3 ጥያቄዎች ተጠይቀዋል።

ቃለመጠይቁ ምልከታውን ተከትሎ የተካሄደ ሲሆን በቅድሚያ ከእያንዳንዱ ተሳታፊ መምህር ጋር ኢመደበኛ በሆነ መልኩ ስለጥናቱ ዓላማ ውይይት ተደርጎ ፈቃደኛነታቸው ተረጋግጧል፤ እንዲሁም ለመደበኛው ቃለመጠይቅ ከተሳታፊዎች ጋር በመመካከር በተቻለ መጠን ለቃለመጠይቁ አመቺ ጊዜና ቦታ ተመርጦ ተከናውኗል። የቃለመጠይቁ ምልልስ በመቅረፀ ድምጽ እንዲቀረጽ ፈቃደኛ በመሆናቸው ተግባሩ ከተከናወነ በኋላ መረጃው በጽሁፍ ሰፍሯል። መቅረፀ ድምጽ መጠቀም አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት ለአጥኚዋ የጥናቱ ተሳታፊዎችን ሀሳብ ሙሉ በሙሉ በጽሁፍ የማስፈር ችግርን ለማቃለል ሲባል ነው።

## 3.4 የአጠናን ሂደት

በአስፋ ወሰን፣አጅባር፣ ደበቅ፣ ወርጠጅና መቅደላ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችበአመቺ የናሙና አመራረጥ ዘዴ (convenience sampling) ሦስት ትምህርት ቤቶች ተመርጠዋል። ጥናቱ ያተኮረው ከ9ኛ - 10ኛ ባሉት የክፍል ደረጃዎች በመሆኑ በ9ኛ እና10ኛ ክፍል በዓላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴ (purposive sampling) ለጥናቱ ተመርጧል። የጥናቱ ተሳታፊ መምህራንም ለጥናቱ በተመረጡት ትምህርት ቤቶች ውስጥ በ2013 ዓ.ም 9ኛና 10ኛ ክፍል አማርኛቋንቋ ትምህርት በማስተማር ላይ የሚገኙ በጠቅላይ የናሙና አመራረጥ ዘዴ (comprehensive sampling) ሁሉም ተመርጠዋል።

ለጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ የተመረጡት የክፍል ውስጥ ምልከታና ቃለመጠይቅ ሲሆኑ ምልከታውን ለማከናወን የሚያስችል ቅጽ ከተዘጋጀ በኋላ የጥናትና ምርምር ልምድ ባላቸው ሰዎችታይቷል። ከዚያም ማስተካከያ ተደርጎበት ተዘጋጅቷል። በምልከታ መረጃ ለመሰብሰብ አጥኚው ረዳት ሰላስፈለገው የጉድኚት ማእከል ሱፐርቫይዘር በረዳትነት ተጠቅሜበታለው። ይኸም የሆነው በረዳትነት የተመረጡት በእንግሊዝኛ ቋንቋ ሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው በመሆናቸው ለሙያ ካላቸው ቅርበት በመነሳት ነው። መምህራን መካከል ሙሉ ፈቃደኛ የሆነና ምልከታው ከመደበኛ የማስተማር ስራው በተቃራኒ ፈረቃ የሆነ ሰው መረጣ ተገቢ ስልጠና እንዲያገኝ አድርጋለች።

ለምልከታ የተዘጋጀው ቅጽ ተፈላጊውን መረጃ መሰብሰብ ማስቻሉን ለመፈተሽ ለሙከራ ጥናቱ በተመረጠው አስፋወሰን፣ አጅባር፣ ደበቅ፣ ወርጠጅና መቅደላ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 9ኛ እና 10ኛ ክፍልአማርኛ ቋንቋ የሚስተምሩ 31 መምህራን የክፍል ዉስጥ ምልከታ በማድረግ ተጠንቷል፡፡

በጥናቱ ዕቅድ መሰረት ከተሳታፊዎቹ ጋር በመነጋገር ምልከታው የሚጀመርበት ክፍለ ጊዜ ተወስኗል፡፡ የጥናቱ ተሳታፊ በሆኑ 31 የ9ኛ እና 10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በእያንዳንዳቸው 2 ክፍለ ጊዜ በድምሩ 62 ክፍለ ጊዜ በአጥኚዉናበረዳቱ አማካይነት የክፍል ውስጥ ምልከታ በማከናወን መረጃው ተሰብስቧል፡፡ ምልከታው ከተጀመረ ጊዜ አንስቶ የአንብቦ መረዳት ትምህርት በሚሰጥባቸው ተከታታይ ክፍል ጊዜ ተካሂዷል፡፡ አጥኚዉናረዳቱ የምልከታ ቅጹንና የማስታወሻ ደብተር በመያዝ ምልከታውን አከናውነዋል፡፡

በቃለመጠይቅ መረጃ አሰባሰብን በተመለከተም ቃለመጠይቁን ለማከናወን በቅድሚያ ከተሳታፊዎቹ ጋር አመቺ ጊዜና ቦታ ተመርጧል፡፡ ቃለመጠይቁ የክፍል ውስጥ ምልከታውን ተከትሎ በአተገባበራቸው ዝቅተኛ አፈፃፀምና ያላቸውን 6 መምህራን ሲሆን ለእያንዳንዱ የጥናቱ ተሳታፊ መምህር ከ25 - 30 ደቂቃ ባለው ጊዜ ተከናውኗል፡፡ አጥኚዉ የቃለመጠይቁ ጥያቄዎች የተጻፉበትን መጠይቅ ምላሺ በመቅረጸ ድምጽ በመያዝ ስለጥያቄዎቹ ምላሽ አሰጣጥ ግልጽ መመሪያ በመስጠት ቃለመጠይቁን አካሂዷል፡፡

በመጨረሻም ከጥናቱ ተሳታፊዎች በክፍል ምልከታውና ከቃለመጠይቁ የተሰበሰቡ መረጃዎች ኮድ ከተሰጣቸው በኂላ እንደየባህርያቸው በአግባቡ ተደራጅተው ተተንትነዋል፡፡

## 3.5የመረጃ አተናተን

ጥናቱ ገምጋሚ አይነታዊ የምርምር ስልትን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማ በ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሀቶችን የክፍል ውስጥ አተገባበር መፈተሽ ነው፡፡ ጥናቱ ይዞት የተነሳውን ዓላማ ለማሳካት ለመረጃ መሰብሰቢያነት በተመረጡት ምልከታና ቃለመጠይቅ አማካይነት የተገኙ መረጃዎች በአይነታዊ መተንተኛ ዘዴዎች ተተንትነዋል፡፡

በምልከታው የተገኙ መረጃዎችን እንደየባህሪያቸው በጭብጥ በጭብጣቸው በሰንጠረዥ በማስፈር ሊመለሱ ከታሰቡበት የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች ጋር በማዛመድ በመቶኛ ተሰልተው ከቀረቡ በኂላ በገለጻ ተተንትነዋል፡፡

ከምልከታ በተጨማሪ ለመረጃ መሰብሰቢያነት በዋለው ቃለመጠይቅ አማካይነት የተገኙት መረጃዎች የተሳታፊዎችን ምላሽ በቀጥታ ዋቢ በማድረግ በገለጻ ተተንትነዋል፡፡ትንተናው የተካሄደው በምልከታውና ከቃለመጠይቁ የተገኙትን መረጃዎች በማዋሀድ ሲሆን አይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎችም በጥምረት ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ ይህም የተሰበሰቡትን መረጃዎች በአግባቡ ለመተንተንና መደምደሚያ ላይ ለመድረስ እንዳስቻለ በአጥኚው ታምኖበታል፡፡

# ምዕራፍ አራት ፡-

# የውጤት ትንተና እና ማብራሪያ

## 4.1 የውጤት ትንተና

ጥናቱ ዋና ዓላማ አድጎ የተነሳው በ2ኛ ደረጃ ትምህት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች አተገባበርን መመርመር ነው፡፡ ይህን ለማሳካት በክፍል ምልከታ በቃለ መጠይቅ የተሰበሰቡት መረጃዎች በጥናቱ ከተነሱት መሰረታዊ ጥያቄዎች አንፃር ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ ጥያቄዎቹምየ2ኛ ደረጃ ትምህረት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአምብቦ መረዳት ብልሃቶችን በክፍል ውስጥ ምን ያህል ተግባራዊ ያደርጋሉ? የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለአንብቦ መረዳት ብልሀቶች የክፍል ውስጥ ትግባራ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮች ምን ምን ናቸው?የሚሉት ናችው ፡፡

### 4.1.1 የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ትንታኔ

በዚህ ጥናት እንዲመለስ የተጠናው የመጀመሪያው መሰረታዊ ጥያቄ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአምብቦ መረዳት ብልሃቶችን በክፍለ ውስጥ ምን ያህል ተግባራዊ ያደርጋሉ? የሚለው ነው፡፡ ይህን ጥያቄ ለመመለስ በምልከታ የተገኘው መረጃ በመጠናዊ ( በመቶኛ ) እና በአይነታዊ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ በተዘጋጀው መገምገሚያ ቅፅ 31 የጥናቱ ተሳታፊ መምህራን የአንብቦ መረዳት ትምህረት ሲያስተምሩ በእያንዳንዳቸቸው 2( ሁለት) ክፍለ ጊዜ ምልከታ በማካሄድ በአማከኝ ( በመቶኛ) ተሰልቷል፡፡ በመጨረሻም የሁሉም 31 መምህራን 62 ክፍለ ጊዜ ምልከታ ውጤት በመቶኛ ተሰልቶ እያንዳንዱ ብልሃት / ተግባር አተገባበር ከፍተኛመካከለኛ ዝቅተኛ በጭራሽ በሚሉ ደረጃዎች በቀጣይ ሰንጠረዥ ተደራጅተው ተተንትነዋል፡፡

## ሰንጠረዥ 4.2 የጥናቱ ተሳታፊ መምህራን የቅድመ ንባብ ብልሃቶች ክፍል ውስጥ አተገባበር

| ተ.ቁ | ቅድመ ንባብ ብልሃቶች | የአተገባበርሁኔታ አማካይ በመቶኛ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከፍተኛ ቁ | % | መካከለኛ ቁ | % | ዝቅተኛ ቁ | % | በጭራሽ ቁ | % |
| 1. | **የምንባብ ሀሳብ መገመት** | | | | | | | | |
| 1.1 | ተማሪዎች ርዕሱን አይተው ምንባቡ ስለምን ሊያስረዳ እንደሚችል እንድገምቱ መርዳት | 2 | 6.7 | 4 | 13.3 | 5 | 16.7 | 19 | 63.3 |
| 1.2 | ተማሪዎች ስዕሉን / ካርታውን አይተው የምንባቡን ይዘት እንዲገምቱ ማድረግ | | | | | 5 | 16.7 | 26 | 83.3 |
| 2 | **የቀደመ እውቀት መቀስቀስ** | | | | | | | | |
| 2.1 | ከቀረበው ስዕል /ወይም ካርታ ያዩትን ወይም የተረዱትን እንድገልፁ መጋበዝ | - | | 3 | 9.67 | 4 | 13.9 | 24 | 77.8 |
| 2.2 | በርዕሱና በስዕሉ መካከል ያለው ግኙኙነት እንድያንፀባርቁ መጠየቅ | | | | | | | 31 | 100 |
| 2.3 | ከሚነበበው ፁሁፍ ጋር ተዛምዶ ያላቸውን ቃላት አባባሎች ጽንሰ ሀሳቦች በመጠየቅ የቅድመ እውቀታቸውን መቀስቀስ | | | 12 | 38.7 | 11 | 35 | 7 | 23.3 |
| 3 | **ምስል መከሰት/ መገንባት** | | | | | | | | |
| 1. | ተማሪዎች ስዕሎችን ፣ ቻርቶችን ሌሎች አጋጣሚዎችን ተጠቅመው ስለሚነበበው ፁሁፍ በአዕምሮችሁ ምስል መከሰት እንድችሉ መረዳት | - | | - | | 8 | 26.7 | 23 | 73.3 |
| 4 | **የመምህሩ አርአያ መሆን ድጋፍ ማድረግ ማበረታታትና ግብረ መልስ መስጠት** | | | | | | | | |
| 4.1 | ተማሪዎች ውጤታማ ብልሃቶችን እንድጠቀሙ አርአያ መሆን | | - | 2 | 6.7 | 23 | 73.3 | 16 | 50 |
| 4.2 | ተገቢ ድጋፍ ማድረግ | | - | 5 | 16.7 | 17 | 53.3 | 9 | 30 |
| 4.3 | የተማሪዎችን ተሳትፎ ማበረታታት | 2 | 6.7 | 5 | 16.7 | 17 | 53.3 | 7 | 23.3 |
| 4.4 | ተገቢ ግብረ መልስ / ማስተካከያ መስጠት | 2 | 6.7 | 13 | 43.3 | 7 | 23.3 | 9 | 26.7 |

**ሠንጠረዥ 4.2** የአንብቦ መረዳት ትምህርት የመምህራንን የቅድመ ንባብ ብልሀቶች የክፍል ውስጥ አተገባባር የሚያመለክት መረጃ ነው፡፡ ከቅድመ ንባብ ብልሃቶች መካካል የምንባቡን ሀሳብ መገመት አንዱ ሲሆን ሰንጠረዥ 4.1 ቁ 1.1 እንድሚያመለክተው ተማሪዎቹ ርዕሱን አይተው ምንበባ ስለምን ሊያስረዳ እንደሚችል እንዲገምቱ በመርዳት ረገድ መምህራኑን በአማካይ 6.7% መካካለኛ 13.3% ዝቅተኛ 16.7% ብቻ ብልሀቱን ተግባራዊ ሲያደርጉ ከፍተኛውን ድርሻ ማላትም 63.3 በጭራሽ ተግባራዊ አላደረጉም ፡፡

ተማሪዎች ስዕሉን / ካርታውን ወዘተ መረጃዎችን አይተው የምንባቡን ይዘት እንዲገምቱ ማድረግን በተመለከተ ምልከታ በተግባራቸው 60 ክፍለ ጊዜያት ብልሃቱ የተተገበሩት (16.7%) በዝቅተኛ ደረጃ ብቻ ነው፡፡ ወደ ምንባቡ ሂደት ሽግግር ከማድረጉ በፊት ተማሪዎቹ ቢያንስ በመፅሀፍ የቀረበን ስዕል ወይም ካርታ ተመልክተው ምንባቡን ምን ሊያስተላልፍ እንደሚችል እንዲገምቱ በመጋበዝ ከመምህር 4፣7፣9፣29 በስተቀርቀሪዎቹ 27ቱ መምህራን በጭራሽ ተግባራዊ እንዳላደረጉ ምልከታ መረጃ ያሳያል፡፡

ሌላው ከመገመት  ብልሀት በተያያዘ ተማሪዎች በቅድመ ንባብ ጊዜ የገመቱት ትክክል መሆኑና አለመሆኑን በማንበብ ጊዜ እንድያረጋግጡ በማስገንዘብ ረገድ 31ዱም መምህራን ምንም ስራ አለመስራታቸው መረጃ ያሳያል፡፡ በሰንጠረዥ4.1 የቀረበው መረጃ እንደሚያሣየው መምህራኑ ተማሪዎች ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት የመገመት ብልሃትን ተጠቅመው የቀደመ እውቀታቸውን በመቀስቀስ ፣ ምንባቡን በተነሳሽነት እንድያነቡና ጊዜ ምን ተግባር እንዳላቸው እንዲገነዘቡ ከማድረግ አኳያ የሰሩት ስራ አናሳ ሁኖ ታይቷል፡፡

በአንብቦ መረዳት ትምህርት ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት የቀደመ እውቀታቸውንና ልምዳቸውን ማነሳሳት ቀዳሚ ተግባር ነው፡፡ በሰንጠረዝ 4.1 ተ.ቁ 2 ስር ሶስት ተግባራት የተመለከቱ ሲሆን የመጀመሪያ ተግባር ፣ ተማሪዎች ከቀረበው ስዕል ካርታ ያዩትን ወይም የተረዱትን እንድገልፁ መጋበዝ በተመለከተ 31 መምህራን በምልከታ በታዩባቸው 62 ክፍለ ጊዜያት ብልሃቱን ተግባራዊ ያደረጉ 8.3 መካካኛ እና 13.9% በዝቅተኛ  ደረጃ ሲሆን ቀሪው 77.8% በጭራሽ  ተግባራዊ እንዳላደረጉ የምልከታ ውጤት ያሣያል ፡፡ ከሰላሳ አንዱ መምህራን መካካልሁለቱ ( መምህር 5እና 31 ) ብልሃቱ በጭራሽ  ሳይተገበሩ ቀርተዋል፡፡

ተማሪዎች በርዕሱ፤ በስዕሉ እና ሌሎች መረጃዎች መካከል ያለው ግንኙነት እንዲያንፀባርቁ በመጠየቅ የቀደመ እውቀታቸውን በማነሳሳት ረገድ፣ መምህራኑ በምልከታ በታየባቸው ክፍለ ጊዚያት ተግባራዊ ሲያደርጉ አይታዩም፡፡

የቀደመ እውቀትን ለመቀስቀስ ከሚረዱ ተግባራት መካከል መምህራኑ በአንፃራዊ የተሻለ ተግባራዊ ያደረጉት ከሚነበበው ፁሁፍ ጋር ተዛምዶ ያላቸው ቃላት ፣ አባባሎች ፅንሰ ሀሳቦች በመጠየቅ ተማሪዎች ቅድመ እውቀት ለመቀስቀስ ያከናወኑት ተግባር ነው፡፡ ይህም ከፍተኛ (3.3%) ፣መካከለኛ ( 36.7%) እና ዝቅተኛ 36.7%  የተገበሩት ሲሆን ቀሪው 23.3 % አልተገበሩትም፡፡ መረጃው እንደሚያሳየው መምህራኑ ስለብልሀቱ የተለያየ የአተገባበር ደረጃ ላይ ቢሆኑም ከግማሽ በላይ የሚሆኑት 16ቱ አብዛሃኛው ድርሻ በመካካለኛ በላይ ተግባራዊ አድርገዋል፡፡

በሰንጠረገኙ 4.1 ተ.ቁ 3 የተገለፀው ምስል መከሰት ብልሃት ሲሆን በቅድመ ንባብ ጊዜ ተማሪዎች ስዕሎችን ፣ ቻርቶችን ሌሎች አጋጣሚዎችን ተጠቅመው ስለሚነበበው ፅሁፍ በአዕምሯቸው ምስል መከሰት እንዲችሉ መርዳት ተማሪዎች ሙሉ ስሜታቸው ለሚያነቡት ፅሁፍ እንዲሰጡ እድል ይፈጥርላቸዋል፡፡ ይሁንና መረጃውን እንደሚያሳየው መምህራኑ 26.7 በዝቅተኛ ደረጃ የተገበሩት ሲሆን 73.33 በጭራሽ  አልተገበሩትም፡፡ ይህም መምህራኑ ብልሃት ተማሪዎችን መርዳት አለመቻላቸውን ያሳያል፡፡

በተ.ቁ 4 ስር የመምህራን አርአያ መሆን ፣ ድጋፍ ማድረግ ፣ ማበረታታትና ግብረ መልስ መስጠት የሚሉ የአንብቦ መረዳት አቀራረብ ብልሃቶች ተዘርዝረዋል፡፡ የመጀመሪያው ተማሪዎች በቅድመ ንባብ ጊዜ ውጤታማ ብልሃቶች እንዲጠቀሙ የመምህራን አርአያ የመሆን ብልሃት የክፍል ውስጥ አተገባበር በተመለከተ መምህራኑ በምልከታ በታየባቸው ክፍለ ጊዚያት 6.7 በመካካለኛ (43.3%) በዝቅተኛ ደረጃ ሲተገብሩት ግማሽ ያህሉ ድረሻ ( 50%) ተማሪዎቹ ከለይ የተዘረዘሩትንም ሆነ ሌሎች ቅድመ ንባብ ውጤታማ ብልሃቶች እንደተጠቀሙ የመምራቱን ተግባር አላከናወኑም፡፡

ከተሳታፊዎቹ መካካል 15% የአርያነት ትግባር ( 50% ) ውስጥ 23.3% በዝቅተኛ 26.7 % በጭራሽ ተግባራዊ አላደረጉም፡፡

ተማሪዎች ተግባራትን ሲያከናውኑ ድጋፍ የማድረግ ብልሃት በተመለከተ መምህራኑ በአማካይ የተገበሩት መካከለኛ 16.7 እና በዝቅተኛ 53.3 ሆኖ ይህም 70% ያህሉን አልተገበሩትም፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም ተማሪዎች በቅድመ ንባብ ትምህርቱ ለሚያደርጉት ተሳትፎ ጥሩ ፣ በጣም ጥሩ ፣ ጎበዝ በማለት ሌሎችም ማበረታቻዎች ተጠቅሞ ለተማሪዎች ተሳትፎ እውቀትና በመስጠት ተማሪዎችን ማነሳሳት የሚጠበቅ ተግባር ሲሆን መምህራኑ 6.7 በከፍተኛ ( 16.7%) በመካካለኛ (53.3%) በዝቅተኛ ደረጃ ተተግብረዋል፡፡ ቀሪው ( 23.3%) ብልሃቱን በጭራሽ ተግባራዊ እንዳላደረጉ መረጃው ያመለክታል፡፡ ከ5 መምህራን በስተቀር አብዛኛዎቹ መምህራን ( 83.4) ክፍተኛውን ድርሻ በዝቅተኛደረጃ አከናውነውታል፡፡

በመጨረሻ የተመለከተው ቅድመ ንባብ ብልሃት በመማር ማተማሩ ሂደት ተማሪዎች የሚያደርጉትን ተሳትፎና ምላሽ መምህሩ በአግባቡ በማዳመጥ ግብረ መልስ /ማስተካከያ መስጠትን የሚጠይቅ ነው፡፡ ይህን ብልሃት በሚመለከት የ31 መምህራን የማጠቃለያ መረጃ በአማካይ ከፍተኛ ( 6.7%) ፣ መካከለኛ ( 43.3% ) እና ዝቅተኛ ( 23.3 %) ተግባራቱን ያከናወኑ ሲሆን ( 26.7% ) አላከናወኑትም፡፤ ይህ መረጃ የሚያሳየው ደረጃው ቢለያይም መምህራኑ ተግባራቱን አከናውነዋል፡፡ ይሁንና አብዛሀኞቹ መምህራን ( 23 መምህራንእና 5 ) ለብልሃቱ ትኩረት ሰጥቶ ያከናወነና ግብረ መልስ ለመስጠት የእውቀት ውስንነት መኖር ( በተለይ መምህር 5 እና 31) ችግር ታይቶባቸዋል፡፡

በጥቅሉ በቅድመ ንባብ አብዛሀኞቹ የጥናት ተሳታፊ መምህራን ስለሚነበበው ምንባብ የቀደመ እውቀታቸው ማነሳሳት ፣ የጋራ ግንዛቤ ይዘው እንዲያነቡና ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት ምን ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው ማስገንዘብ ውስንነት ፣ ስለ ብልሃቶች አተገባበር የግንዛቤ/ እውቀት ማነስና የተገነዘቡትን ያህል ተማሪዎች ተግባራዊ እንድያደርጉ አርአያ መሆን ትኩረት አለመስጠት ተጠቃሽ ችግሮች ናቸው፡፡ 15 ቱ ( 50% መምህራን የቅድመ ንባብ ተግባራትን በመዝለል በቀጥታ ምንባብ እንድነበብ ሲያደርጉ ታይተዋል፡፡

እነዚህ መምህራን አልፎ አልፎ ምንባብ ከመነበቡ በፊት የሚተገብሯቸው ተግባራትም ቢሆኑ ለሚነበበው ምንባብ ቅድመ ተግባራት የማይሆኑና ተለምዷዊ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ተማሪዎች ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት ባለፈው ክፍለ ጊዜውስጥ የተሰሩትን የቃላት አውዳዊና መዝገባዊ ፍች መስጠት ጥያቄዎች ሰዋሰው ጥያቄዎችን ተማሪዎችን እየጠየቁ በድጋሚ እንድሰሩ ካደረጉ በኋላ የምንባቡን ርዕስ በመንገር በቀጥታ ምንባቡ እንዲነበብ ሲያደርጉ ተስተውለዋል፡፡

### ሰንጠረዠ 4.3 የጥናቱ ተሳታፊ መምህራን የምንባብ ጊዜ ብልሃቶች ክፍል ውስጥ አተገባባር

| ተ.ቁ | የንባብ ጊዜ ብልሃቶች | የአተገባበር ሁኔታ አማካይ በመቶኛ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከፍተኛ ቁ | % | መካከለኛ ቁ | % | ዝቅተኛ ቁ | % | በጭራሽ ቁ | % |
| 1 | መረዳትን መከታተል መጠየቅ | | | | | | | | |
| 1.1 | ቅድመ ንባብ ግምታቸው ትክክል መሆን አለመሆኑን ማንበባቸውን እየተከታተሉ እንዲያረጋገጡ ማስገንዘብ | | - | | - | | - | 31 | 100 |
| 1.2 | የግምታቸው ትክክለኛነት ምንባቡን ቀሪ ክፍል በማንበብ እንዲያረጋግጡ ማስመዝገዘብ | | - | | - | 4 | 13.3 | 27 | 86.7 |
| **1.3** | ማንበባቸውን ገታ አድርገው ቀጥሎ ምን ሊከሰትእንደሚችልመጠየቅ | 2 | 6.7 | 8 | 26.7 | 3 | 10 | 18 | 56.7 |
| 1.4 | መረዳታቸውን እንዲከታተሉ የሚያስችሉ ጥያቄዎች መጠየቅ | | - | 5 | 16.7 | 8 | 26..7 | 18 | 56.7 |
| 2 | ማስታወሻ መያዝ | | | | | | | | |
| 2.1 | ሲያነቡ ግልፅ ያልሆነላቸውን በማስታዎሻ እንዲይዙ ማስገንዘብ | | - | | - | | -- | 31 | 100 |
| **3** | **የምንባቡ ዋና ሀሳብ መገንዘብ / መለየት** | | | | | | | | |
| 3.1 | የምንባቡን ዋና ሀሳብ እንዲገነዘቡ መርዳት | | - | 2 | 6.7 | 10 | 33.3 | 19 | 60 |
| **4** | **የመምህራኑ አርአያ መሆን ፣ ክትትል ፣ ግምገማና ድጋፍ ማድረግ ፣ ማበረታታትና ግብረ መልስ መስጠት** | | | | | | | | |
| 4.1 | ተማሪዎችውጤታማ ብልሃቶችን እንዲጠቀሙ አርአያ መሆን | | - | 9 | 30 | 20 | 66.7 | 1 | 3.3 |
| 4.2 | ተገቢ ክትትልና ግምገማ መድረግ | | - | 16 | 50 | 15 | 50 | | - |
| 4.3 | የተማሪዎች ተሳትፎ ማበረታታት | 2 | 6.7 | 1 | 3.3 | 19 | 60 | | - |
| 4.4 | ተገቢ ግብረ መልስ / ማስተካከያ መስጠት | 1 | 3.3 | 19 | 60 | 11 | 36.7 | | - |
| 4.5 | ችግር ላለባቸው ተማሪዎች ተጨማሪ ድጋፍ ማድረግ | | - | 4 | 13.3 | 23 | 73.3 | 4 | 13.3 |

**ሰንጠረዥ 4.3** የጥናቱተሳታፊ መምህራን የምንባቡን ጊዜ ብልሃቶች የአተገባበር ሁኔታ መረጃ የያዘ ነው፡፡ በተራቁጥር1 ስር የተገለፁት ተግባራት ተማሪዎች ምንባቡን በሚያነቡበት ጊዜ መረዳታቸውን እንዲከታተሉ የሚያስችሉ ተግባራት / ጥያቄዎች ናቸው፡፡ በተ.ቁጥር 1.1 ተማሪዎች በቅድመ ንባብ ጊዜ የገመቱት ትክክል መሆኑን አለመሆኑን ማንበባቸውን እየተከታተሉ እንዲያረጋግጡ በማስገንዘብ ረገድ ሁሉም ምህራን በምልከታ በታዩባቸው በሁሉም ክፍለ ጊዚያት የሰሩት ስራ የለም ፡፡ ይህ መረጃ የሚያሣየው መምህራኑ ስለ ብልሃቱ ግንዛቤ በመፍጠር ተማሪዎችን በማንበብ ጊዜ እንድጠቀሙ ማድረግአለመቻላቸውን ነው ፡፡

ተማሪዎች ምንባቡን በሚያነቡበት ጊዜ እንዲገምቱ የግምታቸውን ትክክለኛነት ከምንባቡ ቀሪ ክፍል በማንበብ እንዲያረጋግጡ የማስገንዘብ ተግባራትን ሲሆን ( 13.3%) በዝቅተኛ ደረጃ ብቻ ነው፡፡ይህን ተግባር ከመምህር 4፣7 እና 29 በስተቀር ቀሪዎች መምህራን አለመግተበራቸው የምልከታ መረጃው ያሳያል፡፡

በተ.ቁ. 1.3 የተገለፀው ከመገመት ብልሃት አንዱ የሆነውን፣ ተማሪዎች ማንበባቸውን ገታ አድርገው ቀጥሎ ምን ሊከሰት እንደሚችል እንድገምቱ የመጠየቅ ተግባር ሁሉም መምህራን ምልከታ በታዩባቸው ክፍለግዚያት በአማካይ (6.7%) በከፍተኛ (26.7%) በመካከለኛ እና ( 10% ) በዝቅተኛ ደረጃ ሲያከናውኑ ይህ ደግሞ በመገመት ብልሀት አተገባበር ላይ አሉታዊ ተጽእኖ አለውማለት ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ ከግማሽ በላይ የሆነው ( 56.6%) በጭራሽ ተግባራዊ አላደረጉትም፡፡ ተማሪዎች በቀጣዩ የምንባቡ ክፍል ምን ሊከሰት እንደሚችል ገምተው ማንበባቸውን ሲያከናውኑ ምንባቡ በተነሳሽነት በትኩረት እንድያነቡት ስለሚጋብዛቸው መረዳታቸው ክፍ ይላል፡፡ መረጃው እንደሚያሳየው 18ቱ መምህራን የተሰጠውን ተግባር ( 100 % ) በጭራሽ አላከናወኑም ፡፡ ቀሪዎቹ መምህራን ደረጃ ቢለያይም ተግባራዊ እንዳላደረጉት ያሣያል፡፡

ሌለኛው ብልሃት ተማሪዎች ምንባቡን ሲያነቡ መረዳታቸውን እንድከታተሉ ጥያቄዎች መጠየቅ ሲሆን ፣ ይህም በተመለከተው መረጃ እንደሚያሳየወው 16ቱ ተሳታፊዎች ምልከታ በተካሄደባቸው ክፍለ ጊዚያት ብልሃቱን በጭራሽ ሳይተገበሩ የማንበብ ጊዜ ሂደቱን አሳልፈዋል ፡፡

ቀሪዎቹ መምህራን 13ቱ በመካከለኛና በዝቅተኛ ሁኔታ ተግብረውበታል፡፡ የ31 መምህራን መረጃ በአማከይ በመካከለኛ ( 16.7% ) እና ዝቅተኛ ( 26.7% ) በልሃቱ ሲተገብሩት ቀሪውን ( 56. 7% ) በጭራሽ አልተገበሩትም፡፡

በሰንጠረዡ 4.2 ተ.ቁ 2 የተገለፀው ብልሃት ማስታወሻ መያዝ ነው፡፡ ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ ግልፅ ያልሆነላቸውን በማስታወሻ ቢይዙ ምንባቡን እንደገና አንብበውም ሆነ ከጓደኛ ጋር በመወያየት እንዲገነዘቡ የሚረዳ ተግባር ነው፡፡ ተማሪዎች ይህን ብልሀት በማንበብ ጊዜ እንዲጠቀሙበት በማስገንዘብ በኩል ሁሉም መምህራን ሲያስተምሩ በታየባቸው 62 ክፍለጊዜያት (100%) ያከናወኑት ተግባር የለም፡፡

በማንበብ ጊዜ ጥቅም ላይ ከሚውሉ ብልሀቶች መካከል የምንባቡን ዋና ሃሳብ መገንዘብ/መለየት አንዱ ነው፡፡ በመሆኑም በተ.ቁ. 3 የተመለከተውን ተማሪዎች ምንባቡን ዋና ሃሳብ እንዲገነዘቡ የመርዳቱን ተገባር መምህራኑ በምልከታ በታዩባቸው ጠቅላላ ክፍለጊዜያት የተገኘው መረጃ ሲተነተን ከፍተኛ (6.7%)፤ መካከለኛ (33.3%) ፤ እና ዝቅተኛ (60%) ነው፡፡ ሁለቱ መምህራን (መምህር 4 እና 29) ተግባሩን በከፍተኛና በምካከለኛ ሁኔታ በመተግበር ተማሪዎችን በተሻለ መርዳት የቻሉ ሲሆን፤ ቀሪዎቹ 29 መምህራን ግን በዝቅተኛ ደረጃ ማከናወናቸውን መረጃው ያሳያል፡፡

በማንበብ ጊዝ የምምህሩ አርአያ መሆን ክትትል፤ ግምገማና ድጋፍ ማድረግ፤ ማበረታታትና ግብረመልስ የመስጠት አቀራረብ ብልሀቶች እንደሌሎቹ ብልሃቶች በትኩረት ሊተገበሩ ይገባል፡፡

በመሆኑም እነዚህን ብልሃቶች የጥናቱ ተሳታፊዎች እንዴት ተግባራዊ እንዳደረጓቸው በምልከታ የተገኘው መረጃ ሲተነተን፤ በሰንጠረዥ 4.2 ተ.ቁ 4 ስር የተገለጸውን ተማሪዎች ውጤታማ ብልሀቶችን እንዲጠቀሙ አርአያ የመሆንን ተግባር ሁሉም መምህራን በምልከታ በታዩባቸው ክፍለጊዜያት በአማካይ ያከናወኑት (30%) በመካከለኛ እና (66.7%) በዝቅተኛ ደረጃ ነው፡፡ ቀሪው (3.3%) በጭራሽ አለመተግበሩን ያሳያል፡፡ ከመረጃው መምህራኑ በተለያየ ደረጃም ቢሆን ተማሪዎች ውጤታማ ብልሃቶችን እንዲጠቀሙ አርአያ ለመሆን ሙከራ ማድረጋቸውን መገንዘብ ይቻላል፡፡

በማንበብ ጊዜ ተማሪዎች ማከናወን ያሉባቸውን ተግባር እያከናወኑ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የመምህሩን ተገቢ ክትትልና ግምገማ ይጠይቃል፡፡ በተለይ  የተማሪዎች የክፍል  ደረጃ ከፍ እያለ በሄደ ቁጥር መምህሩ ለተማሪዎች የሚደርገው ክትትል ፣ እገዛና ግምገማ ቆራጥነት ትኩረት መስጠት ይጠይቃል፡፡የምልከታ መረጃው እንደሚያሳየው መምህራኑ ይህን ብልሃት በአማካይ (50% ) በመካካለኛ እና ( 50%) ዝቅተኛ ተግብረውተዋል፡፡ መምህራኑመተግበር ደረጃቸውን ቢይያይም እንድሁም አተገባበር ችግር ቢኖርባቸውም ይህን ብልሃት ተግባራዊ ያላደረገ መምህረ አለመኖሩ በብልሃቱ ቅርበት እንዳላቸው ያሣያል፡፡ መምህራኑ ድምፅ በማሰማትእንዲያነቡ እድል በሚሰጣቸው ውስን ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ ሆሄያትን ቃላትን በአግባቡ ማበባቸውን እንድሁም የማነብብ ፍጥነታቸው በመከታተል ለመገምገም ሙከራ ሲያደርጉ ታይተዋል፡፡ ነገር ግን ተማሪዎቹ በለሆሳስ እና በቡድን በሚያነቡብት ጊዜ የሚያደርጉት ክትትልና ግምገማ ችግር ያለበት መሆኑ በክፍል ምልከታ ታይቷል፡፡

በተ.ቁ 4.3 የተገለፀው ተማሪዎች በንባብ ጊዜ ላደረጉት ተሳትፎ ዋጋ መስጠት በቃላት በጭብጨባና በመሳሳሉት በማበረታታት ተማሪዎችን ተነሳሽነት መፍጠር የሚመለከት ነው፡፡ ይህን ብልሃት መምህራኑ በአማካይ ( 6.7 ) መካከለኛ ( 33.3%) እና ዝቅተኛ ( 60 ) ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ ከሌሎች መምህራን በተለየና በተሻለ መምህር ብልሃቱን በከፍተኛና በመካከለኛ ሁኔታ ተግብረውታል፡፡ በተቃራኒው 15ቱ  (%) በዝቅተኛ ደረጃ መተግበራቸውና  5ቱ መምህራን ( 20% ) በጭራሽ አለመተግበራቸው ያሳያል፡፡

ተማሪዎች በማንበብ ጊዜ ለሚተገብሯቸው ተግባራት ፣ ለተጠየቋቸው ጥያቄዎች ለሚሰጡት ምላሽ ማስተካከያ / ግብረ መልስ መስጠት ብልሃትን መምህራኑ በተሻለ ሁኔታ የተገበሩት በአማካይ ( 3.3) ከፍተኛ ( 60 ) መካከለኛ ( 36.7 ) ዝቅተኛ መሆኑን ያሣያል፡፡

በመጨረሻም ላይ የተገለፀው ብልሃት በተመለከተ ፣ መምህራኑ ችግር ላለባቸው ተማሪዎች ተጨማሪ ድጋፍ ያደረጉት በአማካይ  መካከለኛ ( 13.3) እና ዝቅተኛ ( 73.3) ነው፡፡ቀሪው ( 13.3) በጭራሽ አልተገበሩትም፡፡ በተለይ መምህር 2 ( 60) እና መምህር 4 ( 20) ብልሃቱን ተግባራዊ

አላደረጉም፡፡ የምልከታ መረጃ እንደሚያሳው አብዛሀኞቹ መምህራን ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ለይቶ የማገዙ ተነሳሽነት ትኩረት ዝቅተኛ ነው፡፡

የንባብ ጊዜ ብልሃቶችን አተገባር የጥናቱ ተሳታፊዎች ከቅድመ ንባብ ብልሃቶች አተገባበር በአንፃራዊ የተወሰኑትን መተግበራቸው ያሣያል ፡፡ ይሁንና በተለይ ተማሪዎች በማንበብ ጊዜ ማበባቸውን እንዲከታተሉ የሚረዱ ከመገመት ጋር የተያያዙትንም ሆነ ሌሎች የማስገንዘብ ብልሃቶች ተግባራዊ ማድረግን በተመለከተ መምህራኑ ስራ እንዳልሰሩ መረጃ ያሣያል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ መምህራኑ የንባብ ጊዜ ብላሃቶች ሊተገብሩ ተለያዩ ችግሮች ታይተዋል፡፡ እነዚህም በግዴየለሽነት መተግበር ፣ ተገቢ ክትትልና ድጋፍ አለማድረግ ፣ የተወሰኑ ተማሪዎች ብቻ ማሳተፍ ተማሪዎቹ አለማነሳሳት ጎልተው ተስተውለዋል፡፡

## ሰንጠረዥ 4.4 የጥናቱ ተሳታፊ መምህራን የድህረ ንባብ ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር

| ተ.ቁ | ድህረ ንባብ ብልሃቶች | የአተገባበር ሁኔታ አማከይ በመቶኛ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከፍተኛ ቁ | % | መካከለኛ ቁ | % | ዝቅተኛ ቁ | % | በጭራሽ ቁ | % |
| 1 | ጥያቄና ምላሽ | | | | | | | | |
| 1.1 | ግምታቸውን ትክክል እንደነበርና እንዳልነበር ከነ ምክንያቱ እንድገልጹ መጠየቅ | | - | | - | | - | 31 | 100 |
| 1.2 | መረዳታቸውን መገምገምና የሚያስችሉ ምንባብ ተኮር ጥያቄዎችን መጠየቅ | 11 | 36.7 | 20 | 63.3 | | - | | - |
| 1.3 | በመመስጠር /በአንድምታ የሚመለሱ ጥያቄዎች መጠየቅ | | - | 5 | 16.7 | 26 | 83.3 | | - |
| 2 | **በራስ አባባል መግለፅና ማጠቃለል** | | | | | | | | |
| 2.1 | ተማሪዎች የምንባቡን /አንቀፁን ዋና ሀሳብ በራሳቸው አባባል እንድያፀባርቁ ማድረግ | 7 | 23.3 | 23 | 73.3 | 1 | 3.3 | | - |
| 2.2 | ያነበቡትን ጹሁፍ ሀሳብ አጠቃሎ እንድገልፁ ማድረግ | | - | 3 | 10 | 13 | 43.3 | 15 | 46.7 |
| 3 | **ምስል መከሰት /መገንባት** | | | | | | | | |
| 3.1 | ተማሪዎች ስዕሎችን ቻርቶችንና ሌሎች አጋጣሚዎችን ተጠቅመው ስለሚነበበው ፅሁፍ በአዕምሮቸው ምስል መከሰት እንድችሉ መርዳት | | - | 4 | 13.4 | 24 | 76.6 | 3 | 10 |
| 4 | **የመምህሩ አርአያ መሆን ክትትል ግምገማና ድጋፍ ማድረግ ማበረታታት ግብረመልስና ማጠቃለያ መስጠት** | | | | | | | | |
| 4.1 | ተማሪዎች ዉጤታማ ብልሀቶችን እንድጠ ቀሙ አርአያ መሆን | | - | | - | 14 | 46.7 | 17 | 53.3 |
| 4.2 | ተገቢ ክትትልና ግምገማ ማድረግ | 1 | 3.3 | 11 | 36.7 | 19 | 60 | | - |
| 4.3 | የተማሪዎችን ተሳትፎ ማበረታታት | 3 | 10 | 13 | 40 | 14 | 46.7 | 1 | 3.3 |
| 4.4 | ተገቢ ድጋፍ ማድረግ | | - | 11 | 36.7 | 19 | 63.3 | | - |
| 4.5 | ተገቢ ግብረመልስና ማጠቃለያ መስጠት | 4 | 13.3 | 17 | 53.3 | 8 | 26.7 | 2 | 6.7 |

ሠንጠረዥ 4.3 የጥናቱ ተሳታፊ መምህራን ድህረ ንባብ ብልሀቶችን በክፍል ዉስጥ ምን ያህል ተግባራዊ እንዳደረጉ የሚያሳይ መረጃ ነው። ድህረ ንባብ ብልሀቶች ተማሪዎች ያነበቡትን ምንባብ እንደተረዱትና እንዳልተረዱት የሚፈተሽባቸው ናቸው ።

በሠጠረዥ በተ.ቁ 1.1 ተማሪዎች ግምታቸው ትክክል እንደነበረና እንዳልነበረ ከነምክንያቱ እንድገልፁ መጠየቅ ብልሀትን መምህራኑ በምልከታ በታዩባቸዉ ጊዜያት አንዳቸዉም ተግባራዊአላደረጉም ። ይህ የሚያሳየው መምህራኑ በአንብቦ መረዳት ትምህርቱ ተማሪዎች ከመገመት ጋር የተያያዙ ብልሀቶችን እንድጠቀሙ ግንዛቤ መፍጠር እንዳልቻሉ ነው ።

በድህረ ንባብ ጊዜ ተማሪዎችን መርዳት መገምገም የሚያስችሉ ምንባብ ተኮር ጥያቄዎችን የመጠየቅ ተግባርን ዘጠኝ  መምህራን ምን ያህል እንደተገበሩት በሠጠረዡ በተ.ቁ 1.2  የሰፈረዉ መረጃ እንደሚያሳየው፣  በአማካይ (36.7%) በከፍተኛ እና (63.3%) በመካከለኛ ደረጃ ከሌሎች ብልሀቶች ብልጫ ባለው ሁኔታ ተግባራዊ አድርገውታል ።መረጃው እደሚያሳየው መምህራኑ ይህን ድህረንባብ ብልሀት በተሻለ ሁኔታ መተግበራቸው የተማሪዎችን አንብቦ መረዳት ለመገምገም አዘውትረው የሚጠቀሙበት መሆኑን ነው።

ሌላው ተማሪዎችን በመመስጠር /በአንድምታ የሚመለሱ ጥያቄዎችን የመጠየቅ ተግባርን መምህራኑ በታዩባቸው 62 ክፍለጊዚያት ያከናወኑት( 16.7%) በመካከለኛ እና (83.3%) በዝቅተኛ ደረጃ ነው። ከእያንዳንዱ መምህር የተገኘው መረጃም እንደሚያመለክተው  31ቱም  መምህራን ተማሪዎች የቀደመ እውቀታቸውንና በፅሁፍ ውስጥ የሚገኙ ፍጮችን ተጠቅመው በቀጥታ ያልሰፈረ ሀሳብን ምን ያህል መገንዘብ እንደቻሉ ለመገምገም ያደረጉት ጥረት ዝቅተኛ ነው።

ተማሪውች ያነበቡትን ምንባብ ለመገምገም ከሚረዱ መግለፅና ማጠቃለያ ተጠቃሽ ናቸው ። በመሆኑም ተማሪዎች የምንባቡን ዋና ሀሳብ በራሳቸው አገላለጽ እንዲያንጸባርቁ ማድረግን መምህራኑ በምልከታ በታዩባቸው 62 ክፍለጊዜያት በአማካይ (23.3%) በከፍተኛ  (73.3%) በመካከለኛና (3.3%) በዝቅተኛ ደረጃ ተግብተውታል ። ከዚህ መረዳት የሚቻለው መምህራኑ ብልሀቱን በተሻለ እንደሚያዉቁትና እንደሚተገብሩት (አብዘሀኛውን በመካከለኛና ተከታዩን በከፍተኛ ደረጃ ) ነው።

በተቃራኒው በተ.ቁ 2.2 ተማሪዎች ያነበቡትን ፅሁፍ ሀሳብ አጠቃለው እንድገልፁ በማድረግ ረገድ መምህራኑ መካከላኛ (10%) እና ዝቅተኛ( 43.3%) ሲተገብሩት ወደ ግማሽ የሚጠጋውን ድርሻ (46.7%) አለመተግበራቸውን መረጃው ያሳያል ።

በድህረ ንባብ ጊዜ ተማሪዎች ስዕሎችን ቻርቶችንና ሌሎች አጋጣሚዎችን ተጠቅመው ስለተነበበው ፅሁፍ በአዕምሮቸው ምስል መከሰት እንድችሉ መርዳት ከፅሁፉ ያገኙትን መረጃ ለማብላላትና ለማዋሀድ ከማስቻሉም በላይ ፅሁፉን ዳግም እንዳስታውሱት ያደርጋል ፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎች ይህን ብልሀት ተግባራዊ ያደረጉት በአማካይ (13.4%) በመካከልኛ እና (76.6%) በዝቅተኛ ደረጃ ሲሆን (10%) በጭራሽ አልተገበሩትም ፡፡ ይህም አብዘሃኞቹ መምህራን ብልሀቱን በዝቅተኛ ደረጃ መተግበራቸውን ያሳያል፡፡

በድህረ ንባብ ጊዜ የመምህሩ አርአያ መሆን ክትትል ግምገማና ድጋፍ ማድረግ ማበረታታት ግብረመልስና ማጠቃለያ መስጠት በአግባቡ እንድተገብሩ የሚጠበቁ ብልሀቶች ናቸው ፡፡ በሠጠረዥ ተ.ቁ 4.1 ተማሪዎች ያነበቡትን ምንባብ መረዳት አለመረዳታቸውን መገምገም የሚስችሉ ውጤታማ ብልሀቶችን እንድጠቀሙ አርአያ የመሆን ተግባርን መምህራኑ በታዩባቸው ክፍለጊዜያት ተግባራዊ የደረጉት በአማካይ (46.7%) በመካከለኛና(53.3%) በዝቅተኛ ደረጃ ነው፡፡ ይህ የሚያመለክተው መምህራኑ ብልሀቱን ከቅድመ ንባብና ከንባብ ጊዜ በተሻለ ተግባራዊ እንዳደረጉት ነው ፡፡

በድህረ ንባብ ተማሪዎች የሚተገብሯቸውን ተግባራት የተለያዩ ዘዴ በመጠቀም መከታተልና መገምገም ይጠይቃል ፡፡ለምሳሌ እያንዳንዱን ተማሪ በተናጠል በጥንድ በቡድን በቃል በፅሁፍ ወዘተ የሚሰሩ ተገባራትን ማመቻቸት ተግባራዊነቱን መከታተልና መገምገም ይጠበቃል፡፡ ይህን ብልሀት በተመለከተ የመምህራኑ የክፍል ውስጥ አተገባበር በአማካይ (3.3%) ከፍተኛ (36.7%) መካከለኛ እና (60%) ዝቅተኛ ነው፡፡ መምህራኑ ለብልሀቱ ትኩረት ሰጥተው ባለመተግበራቸው አብዘሀኛውን ድርሻ በዝቅተኛ ደረጃ ተግብረውታል ፡፡ ከመምህራኑ መካከል 3ቱ መምህራን 4፣7 ና 29 ይህን ተግባር በተሻለ (20%) ከፍተኛ እና (80%) መካከለኛ ተግብረውታል ፡፡

በድህረ ንባብ ጊዜ መምህራኑ የተማሪዎችን ተሳትፎ ያበረታቱት በአማካይ ከፍተኛ (10%) መካከለኛ (40%) እና ዝቅተኛ (46.7%) ተግባራዊ ሲያደርጉ(3.3%) አልተገበሩትም ፡፡ ይህም አብዛኞቹ መምህራን በተለያየ ደረጃም ቢሆን ብልሀቱን ለመተግበር ሙከራ አድርገዋል ፡፡ ከሌሎቹ የጥናቱ ተሳታፊዎች በተለየና ተማሪዎቹን ሊያበረታታ በሚችል ሁኔታ ከፍተኛ (60%) እና መካከለኛ (40%) ተግባራዊ አድርገዋል ፡፡

በምድብ 4 ተ.ቁ 4.4 የተገለፀዉ ብልሀት ለተማሪዎች ተገቢ ድጋፍ ማድረግ የሚል ሲሆን ይህ ብልሀት ከክትትል ብልሀት ጋር የተሳሰረ ነው ፡፡ ተገቢ ክትትል ከተደረገ ማን ምን አይነት ድጋፍ

እንደሚያስፈልገው ማወቅ ይቻላል ፡፡ መምህራኑ በምልከታ በታዩባቸው ክፍለጊዜያት ብልሀቱን የተገበሩት በአማካይ (36.7%)በመካከለኛና (63.3%) በዝቅተኛ ደረጃ ነው ፡፡ ይህም መምህራኑ ከሚያስተምሩበት የክፍል ደረጃ አኳያ የሚጠበቅባቸውን ያህል ድጋፍ አላደረጉም፡፡

በሠጠረዡ በመጨረሻ የተገለፀውን ድህረ ንባብ ብለሀት ማለትም መምህራኑ ለተማሪውች ተገቢ ግብረመልስና ማጠቃለያ በመስጠት ረገድ አተገባበራቸው በአማካይ ሲተነተን (13.3%)ከፍተኛ (53.3) በመካከለኛ እና (26.7) በዝቅተኛ ደረጃ ሲሆን ቀሪው (6.7%) ግን ብልሀቱ በጭራሽ አልተተገበረም ፡፡ መረጃው እንደሚያመላክተው ከመምህር ሁለት በስተቀር ሌሎቹ አተገባበራቸው በቂ ባይሆንም እንድሁም ደረጃው ቢለያይም በአብሃኛው በቃል ግብረ መልስ በመስጠት ላይ በማተኮር ግብረመልስ ለመስጠት ጥረት አድርገዋል ፡፡ መምህር 5 -31 ግን ከአተገባበር ችግር ባለፈ ግብረመልስና ማጠቃለያ ለመስጠት መሰረታዊ ችግር እዳለባቸው የምልከታው መረጃ በግልጽ ያሳያል፡፡

በጥቅሉ የጥናቱ ተሳታፊዎች የድህረንባብ ብልሀቶች የክፍል ውስጥ አተገብበር ከቀደምት ደረጃዎች የተሸለ መሆኑን መረጃው ያመለክታል፡፡ በተለይ መምህራኑ ተማሪዎች የተነበበውን ምንባብ መረዳታቸውን መገምገም የሚያስችሉ ምንባብ ተኮር ጥያቄዎችን መጠየቅ ተግባርን በትኩረት እንደከናውኑትና ለብልሀቱ ቅርብ ግንዛቤ እንዳላቸው ያሳያል ፡፡ተማሪዎች የምንባቡን ዋና ሀሳብ በራሳቸው እዳፀባርቁ የማድረግ ተግባርንም በተሸለ ሁኔታ መተግበራቸው ታይቷል ፡፡በአንፃሩ አብዛኞቹ መምህራን ቀሪዎቹን ብልሀቶች በዝቅተኛደረጃ ማከናወናቸው የአተገባበር እና የግንዛቤ ችግር እዳለባቸው መረጃው ያሳያል፡፡ በተጨማሪም መምህራኑ ብልሀቶቹን ሲተገብሩ ከታዩት ችግሮች መካከል ተገቢ ክትትልና ድጋፍ አለማድረግ ፣ ተገቢ/አጥጋቢ ግብረመልስ አለመሲጠት ፣የተወሰኑ ተማሪዎችን ብቻ ማሳተፍ ፣ለተማሪዎች ተሳትፎ እውቅና አለመስጠት /አለማበረታታት፣ የተማሪዎች ተነሳሽነት ማነስ/ማጣት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

4.1.2 የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ትንታኔ

በዚህ ጥናት እድመለስ የታሰበው ሁለተኛው መሰረታዊ ጥያቄ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለ አንብቦ መረዳት ብልሀቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ያላቸው ግንዛቤ ምን ይመስላል የሚለው ነው፡፡ ይህ ጥያቄ ከመጀመሪያው መሰረታዊ ጥናቱ ጥያቄ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ በረዳት ብልሀቶችን በክፍል ውስጥ ምን ያህል ተግባራዊ ያደርጋሉ "ከሚለው ጋር በጥብቅ የተሳሰረ ነው፡፡በመሆኑም ይህ ጥያቄ ለመመለስ ሙከራ የተደረገው የአንብቦ መረዳት

ትምህርቱ መማር ማስተማር ሲከናዎን የተደረገውን የክፍል ውስጥ ምልከታ መረጃ መሰረት በማድረግ ነው፡፡የጥናቱ ተሳታፊ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሀቶችበክፍል ውስጥ ሲተገበሩ በአማካይ (በመቶኛ) ከፍተኛ፣ መካከለኛና ዝቅተኛ በሚል ሁኔታ የተገኘውን መረጃ መሰረት በማድረግ መምህራኑ ብልሀቱን በዚህ ደረጃ ሲተገብሩት ያላቸው ግንዛቤ ምን እንደሚመስል ለማመሳከር ቃለመጠይቅ ቀርቦላቸዋል፡፡ የቃለመጠይቁ ጥያቄዎች ምልከታውን መሰረት ያደረጉ አስቀድሞ ያልተወሰኑ ጥያቄዎች ናቸው፡፡በምልከታ ቅፁ ከቀረቡት ተግባራት መካከል አንዳዶቹን 31ዱም በጭራሽ ተግባራዊ ሳያደርጓቸው ታይተዋል ፡፡ ለነዚህ ተግባራት ምልከታዉን ብቻ መሰረት በማድረግትንተና ተሰጥቶባቸዋል፡፡

4.1.2.1 የቅድመ ንባብ ብልሀቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ትንታኔ

የቅድመ ንባብ ብልሀቶችበተመለከተ በሠጠረዥ 4.1 የምልከታው መረጃ እነደሚያሳየው ተማሪዎች ርዕሱን ፣ ስዕሉን ወይም ካርታውን ወዘተ መረጃ ምንባቡ ስለምን ሊያስረዳ እንደሚችል እኒድገምቱ መጋበዝን በተመለከተ አብዛኞቹ መምህራን ተግባሩን አላከናወኑትም ፡፡ በምልከታው እንደታየው መምህራኑ በእለቱ የሚነበበውን የምንባብ ርዕስ በአብዛኛው በጥቁር ሰሌዳላይ በመፃፍ አልፎ አልፎ ደግሞ በቃል ከማሳወቅ ባለፈ ተማሪዎች ከርዕሱ ፣ከስዕሉና ከካርታው ተነስተዉ የምንባቡን ይዘት እንድገምቱ እድሉን አልሰጡም ማለት ይቻላል፡፡ ይህም ስለመገመት ብልሀት አተገባበር በቂ ግንዛቤ እንደሌላቸው ያሳያል ፡፡ ከተጠኝዎች መካከል መምህር -4 እና 7 ከሌሎቹ መምህራን በተለየ ተማሪዎች ርዕሱን አይተው እንድገምቱ በማድረግ 6.45 ወይም (40%)ከፍተኛ 12.97 ወይም (60%) መካከለኛ ፣ ስዕሉን/ ካርታውን አይተው እንድገምቱ (100%) ዝቅተኛ መተግበራቸው መምህሩ/ሯ በአንፃራዊ ስለብልሀቱ ተገባበር ግንዛቤ እንደለላቸው ያመለክታል፡፡ ከመምህር -5 ቃለመጠይቅ ምላሽ የተገኘው መረጃም ከዚህ ጋር ተደጋጋፊነት አለው ፡፡

ይኸውም ይህን ተግባር ለምን እንዳከናወኑት ተጠይቀው የሰጡት ምላሽ ተማሪዎች ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት ስለ ርዕሱ/ስዕሉ ይዘት ግምት ይሰጣሉ ፣ ካነበቡ በህዋላ ግምታቸው ትክክል ይሁን አይሁን አንብበው ያገኙትን አገናዝበው ትክክለኛውን እንድለዩ ለማድረግ ነው ብለዋል ፡፡
ተማሪዎች ከቀረበው ስዕል /ካርታ ያዩትን ወይም የተረዱትን እንድገልጹ በመጋበዝ በኩል መምህራኑ በምልከታ በታዩባቸው 62 ክፍለ ጊዜያት 24 መምህራን ተግባሩን (100%) በጭራሽ አለመተግበራቸው ስለብለሀቱ ግንዛቤ እንደሌላቸው ያሳያል ፡፡ ከቀሪዎቹ ሁሉም መምህራን መምህር 3ቱ (9.67%) በመካከለኛ ደረጃ ብቻ መምህር -6 ደግሞ (50%) በመካከለኛ (50%) በዝቅተኛ ተግብረዋል ፡፡ እነዚህ መምህራን የአተገባበራቸው ደረጃ ቢለያይም በአንፃራዊ ብልሀቱን በዚህ ደረጃ

መተግበር በቻላቸው ስለብልሀቱ የተወሰነ ግነዛቤ እዳላቸው የምልከታው መረጃ ያሳያል ፡፡ በቃለመጠይቅ የተገኘው መረጃ ተቀራራቢነት አለው፡፡

ተማሪዎች ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት ከርዕሱ ያስተዋሉትን ወይም የተረዱትን እንድገልፁ ያደረጉት ለምን ይሆን / ለሚለው ጥያቄ መምህር 3 ምላሽ ሲሰጡ ፡-ተማሪዎች ስዕሉን አይተው የሀገራቸው ሯጮች እነማን እንደሆኑ መናገር መቻል አለመቻላቸውን ማለትም ቅድመ ግንዛቤ እዳላቸውና እንደሌላቸው ለማወቅ ነው " ሲሉ መምህር 31ም ተማሪዎች ስዕሉ ስለምን እንደሚያስተምር ሲገልፁ ቅድመ እውቀታቸውን ለመለካት ነው ብለዋል፡፡

ከምላሻቸው መረዳት የሚቻለው እነዚህ መምህራን ይህን ብልሀት የተገበሩት ብልሀቱ ያለውን ጠቀሜታ በመገንዘብ እንደሆነ ነው፡፡

በዚሁ ሠጠረዥ ተማሪዎች በርዕሱና በስዕሉ መካከል ያለውን ግንኙነት እዳፀባርቁ በመጠየቅ ረገድ የምልከታው መረጃ እንደሚያሳየው 31ም መምህራን ሲያስተምሩ በታዩባቸው 62 ክፍለጊዜያት (100%) በጭራሽ አለመተግበራቸው መምህራኑ ስለብልሀቱ ግንዛቤ እንደሌላቸው የሚያሳይ ነው፡፡ በጠቃላይ መምህራኑ ታሪዎች ምንባቡን ከማኒበባቸው በፊት ርዕሱን ፣ስዕሉን ፣ካርታውን ተጠቅመው የቀደመ እውቀታቸውን በመቀስቀስ ከሚነበበው ምንባብ ጋር እዳስተሳስሩት በማድረግ በኩል ከ4 እና 7 ላይ ካሉት የጥናቱ ተሳታፊ መምህራን በስተቀር ሌሎቹ ግንዛቤ እንደሌላቸው መረጃው ያሳያል፡፡

በቅድመንባብ ጊዜ መምህራኑ በተሻለ የተገበሩት ከሚነበበው ፅሁፍ ጋር ተዛምዶ ያላቸውን ቃላት አባባሎችና ፅንሰሀሳቦች በመጠየቅ የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት መቀስቀስ ነው፡፡ በሠጠረዥ 4.1 የሰፈረው መረጃ እንደሚያሳየው 31ቱ መምህራን አተገባበር በአማካኝ ከፍተኛ (3.3%) መካከለኛ (36.7%) እና ዝቅተኛ (36.7%) ተግብረዋል ፡፡ መምህራኑ በተለያየ የአተገባበር ደረጃ ላይ ቢሆንም ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ስለብልሀቱ ግንዛቤ እዳላቸው ያመላክታል፡፡ በቃለመጠይቅ የተገኘው መረጃም ተደጋጋፊነት አለው ፡፡ ለአብነት፡- መምህር-1 እና መምህር -3 ይህን ተግባር እዳከናወኑት ተጠይቀው የሰጡት ምላሽ፡- መምህር -1 ስለሚነበበው ምንባብ ይዘት ምን ያህል እንደሚያውቁ ለመገምገምና ቅድመግንዛቤቸውን ለማስፋት ነው፡፡ ሲሉ መምህር- 3 ደግሞ "ተማሪዎች ስለቀረበው ምንባብ ምን እንደሚያውቁና እውቀታቸውን እንዳገናዝቡ ለማድረግ ነው፡፡"ብለዋል፡፡

በጠቃላይአብዛኞቹ የጥናቱ ተሳታፊ መምህራን ጊዜ መተግበር ላለባቸው ተግባራት የግንዛቤ ውስንነት /አለመኖር ታይቷል ። ይህም አብዛኛውን ጊዜ ቅድመንባብ ተግባራትን ሳያከናውኑ ምንባቡ እንድነበብ ማድረጋቸው በክፍል ምልከታው ታይቷል። አንዳንዶቹ መምህራን ደግሞ በቅድመ ንባብ ጊዜ የተገበሯቸው ተግባራት ለቅድመንባብ ተግባርነት የማይሆኑ ናቸው። ተግባራቱን በተለምዶ እንደሚተገበሯቸውና ለምን እንዳልተገበሯቸም ግንዛቤው ያላቸው አይመስልም ። ለአብነት የቀረበው የቃለመጠይቅ መረጃም ይህንኑ ያመለክታል።

መምህር -4 ምንባቡ ከመነበቡ በፊት ባለፈው ክፍለጊዜ በክፍል ውስጥ የተሰሩትን ለቃላት አውዳዊና መዝገበቃላዊ ፍች መስጠት ጥያቄዎች በዛሬው ክፍለጊዜ በድጋሜ እድሰሩ ያደረጉት ለምን ይሆን? ለሚለው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ ፡-“ይህ በአዲስ ክፍለ ጊዜ የምንሰራው የአሰራር ደንብ ነው። ሌሰንፐላን ወጥቶ ይህንን ስራ እንድንሰራል የአሰራሩ ቅደም ተከተል ፣ መማሪያና ደንቡ ስለሚያዝ ነው።” ብለዋል።

4.1.2.2 የንባብ ጊዜ ብልሀቶች የክፍል ዉስጥ አተገባበር ግንዛቤ

የንባብ ጊዜ ብልሀቶች ተማሪዎች ማንበባቸዉን እየተከታተሉ የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ የሚረዱ ናቸው። በመሆኑም የጥናቱ ተሳታፊ መሞህራን ለነዚህ ብልሀቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ያላቸው ግንዛቤ በመረጃው መሠረት ቀጥሎ ተተንትኗል። በሠንጠረዥ 4.2 መጀመርያ ላይ እንደተመለከተው ተማሪዎች በቅድመ ንባብ ጊዜ የገመቱት ትክክል መሆን አለመሆኑን ማንበባቸውን እየተከታተሉ እንዲያረጋግጡ በማስገንዘብ ረገድ መምህራኑ በምልከታ በታዩባቸው 62 ክፍለ ጊዚያት ተግባሩ (100) በጭራሽ አላከናወኑትም። ይህም መምህራኑ ስለመገመት የአንብቦ መረዳት ብልሀት የክፎል ውስጥ አተገባበር ግንዛቤ እንደሌላቸው ያመላክታል። በተመሳሳይ ተማሪዎች ምንባቡን ሲያነቡ ግልጽ ያልሆነላቸውን በማስታወሻ እድይዙ የማስገንዘብ ብልሀትንም አንዳቸውም ተግባራዊ አላደረጉም። ይህም መምህራኑ ተማሪዎች በማንበብ ጊዜ ማንበባቸውን መከታተል እንዲችሉ የሚያግዙ ተግባራትን እንዲያከናውኑ በአንዱም ክፍለ ጊዜ አለማስገንዘባቸውን ግንዛቤው እንዴሌላቸው የምልከታው መረጃ ያሳያል።

ተማሪዎች ምንባቡን እያነበቡ እያሉ ምንባቡ ምን ሊያሥተላልፍ እንደሚችል የገመቱትን ግምት ትክክለኛነት የምንባቡን ቀሪ ክፍል በማንበብ እንድያረጋግጡ በማስገንዘብ በኩልም 31 መምህራን በምልከታ በታዩባቸዉ ክፍለ ጊዜያት በአማካይ (13.3%) በዝቅተኛ ደረጃ ብቻ ነዉ ያከናወኑት:: 31

ንዱ መምህራን መካከል 27ቱ ተግባሩን (100%) በጭራሽ አለመተግበራቸዉ ከላይ እንደተገለጸዉ ለዚህ የማስገንዘብ ብልሀትም ግንዛቤ እንደሌላቸዉ መረጃዉ ያሳያል::
ሌላዉ የማንበብ ጊዜ ብልሀት ተማሪዎች ማንማንበባቸዉን ገታ አድርገው ቀጥሎ ምን ሊከሰት እንደሚችል ግምት እንድሠጡ መጠየቅ ተግባርን መምህራኑ ሲያሥተምሩ በምልከታ በታዩባቸዉ ጊዜያት በአማካይ ከፍተኛ (67%); መካከለኛ (27%) እና ዝቅተኛ (10%) ተግባራዊ ሚያደርጉ (56%) አልተገበርቱም:: የእያንዳንዱ መምህር የምልከታ ጊዜያት በጭራሽ አለመከናወናቸዉ መምህራኑ ግንዛቤ እንደሌላቸዉ ያመላክታል:: ቀሪዎቹ 2ቱ መምህራን ተግባሩን ማከናወናቸዉ እንዳተገባበራቸዉ ሁኔታ መካከለኛ እና ዝቅተኛ ግንዛቤ እንዳላቸዉ ያሣያል:: በቃለ መጠይቅ የተገኘዉ መረጃም ከዚሁ ጋር ተቀራራቢነት አለዉ::

ምንባብ በሚነበብበት ጊዜ በምንባቡ በሳጥን ውስጥ  ያለበት ቦታ ሢደርሡ  ተማሪዎች ማንበባቸዉን ገታ አድርገዉ ጥያቄዉን እንድመልሡ /እንድገምቱ ያደረጉት ለምን ይሆን? ለሚለዉ; መምህር-1 እና 5 ምላሽ ሲሰጡ; መምህር-1 ትንበያቸዉን ከምንባቡ ጋር እንድዛመዱ እና የትንበያ ችሎታቸዉን እንዲያዳብሩ ለማድረግ ነዉ:: ሲሉ መምህር -5 ደግሞ ያዳመጡትን ምን ያህል እንደተገነዘቡና ቀጣዩንም እንድናገሩ ለማድረግ ነዉ:: ብለዋል::
ከምላሻቸዉ መረዳት የሚቻለዉ ተማሪዎች ማንበባቸዉን ገታ አድርገው ቀጥሎ ምን ሊከሰት እንደሚችል ቢገምቱ ብልሀቱ ስላለዉ ፋይዳ ግንዛቤ እንዳላቸዉ ቢያመላክትም በቂ እንዳልሆነ ያሳያል:: ለምሳሌ መምህር-5 ስለብልሀቱም ሆነ ስለመማር ማስተማሩ አተገባበር ያላቸዉ ግንዛቤ አዳምጦ መረዳትና አንብቦ መረዳት አንድ እንደሆኑ በማሰብ ነዉ::
በማንበብ ጊዜ የመምህሩ ክትትልና ግምገማ ማድረግ በተመለከተ በሰንጠረዥ 42 እንደተገለጸዉ መምህራኑ በአማካይ (50%) በመካከለኛና (50%) በዝቅተኛ ደረጃ አከናዉነዋል:: ብልሀቱን በዚህ ደረጃ መተግበራቸዉ ስለብልሀቱ አተገባበር ግንዛቤ እንዳላቸዉ ቢያሳይም በምልከታዉ ጊዜ እንደታየዉና የቃለ መጠይቁ መረጃም እንደሚያመለክተዉ አብዛኞቹ መምህራን ስለ አተገባበሩ በቂ ግንዛቤ እደሌላቸዉ ነዉ:: በቃለ መጠይቅ የተገኘዉ መረጃ ቀጥሎ ቀርቧል::
ተማሪዎችም ንባቡን በለሆሳስ በሚያነቡበት ጊዜ እርስዎ በተማሪዎች መካከል እየተዘዋወሩ የሚቃኟቸዉ ምን መተግበራቸዉን ለማየት ነዉ? ለሚለዉ ጥያቄ የሰጡት ምላሽ; መምህር-2 "ድምጽ ሳያሰሙ ማንበባቸዉን ነዉ:: ምክንያቱም ድምጽ አሰምተዉ የሚያነቡ ከሆነ ሌሎችን ስለሚረብሹ ለመከታተል ነው። ሲሉ መምህር  6 ደግሞ አንዳንድ ልጆች ያነበቡ መስለው ያጎነብሳሉ ስለዚህ በትክክል እያነበቡ እንደሆነ ለመከታተል ነው፡ ብለዋል።
ተማረዎች ምንባቡን በቡድን በሚያነቡበት ጊዜ እርሰዎ በተማሪዎች መካከል እየተዘዋወሩ እነሱን አስተካክሎ ትምህርቱን እድማሩ ለማድረግ ነው።

ከምላሻቸው መረዳት የሚቻለው መምህር 6 የተሻሻለ ግንዛቤ እዳላቸው ሲያሳይ መምህር ,2 እና 4 ግን ባብዛኛው ተማሪዎችን የሚከታተሉት አንብበው መረዳታቸውን ሳይሆን እንዳይረብሹ መቆጣጠር ላይ ያተኮረ ነው።

የተማሪዎችን ተሳትፎ ማበረታታትና ግብረ መልስ መስጠትን በተመለከተ የምልከታዉ መረጃ እደሚያሳየው አብዛኞቹ መምህራን ግንዛቤው እንዳላቸው ሲያሳይም በሌላ በኩል የአተገባበር ግንዛቤ ደረጃው እንደሚለያይ ያመላክታል። የቃለ መጠይቁ መረጃ ከዚሁ ውጤት ጋር ተዛማጅነት አለው።

በማንበብ ጊዜ ተሳትፎ ላደረጉ ተማሪዎች ጓደኞቻቸው እንዲያጨበጭቡላቸው ያደረጉት ለምንድን ነው ? ለሚለው ጥያቄ መምህር 1 - ምላሽ ሲሰጡ-የተሳተፉ ተማሪዎችን ለማበረታታትና ቃላዕቱም ሆነ በሌላ ጊዜ ሌሎች ተማሪዎች እድሳተፉ ለማነሳሳት ነው። ብለዋል።
መምህር -3: ተማሪዎች ድምጻቸውን ከፍ አድርገው በሚያነቡበት ጊዜ እርሶም ' አሁን አንተ ማንበብህ ነው ? /ማንበብሽ ነው ?" የሚሏቸው አንዳንድ ተማሪዎች አሉ። ይህን የሚሉት ለምን ይሆን? ለሚለው ጥያቄ ሲመልሱ:-'አንዳንዶቹ ቃላትን ይገድፈሉ፡ አንዳንዶቹ ደግሞ ፊደል ይቀንሳሉ ወይም የጨምራሉ። ይህን ለምን አደረጋችሁ በሚል ስህተታቸውን እንዲያስተካክሉ ነው። ብለዋል። መምህር 1- ተማሪዎችን ለማበረታታት የተገበሩት ተግባርና ለምን እደተገበሩት በቃል መጠይቁ የሰጡት ምላሽም እንደ ሚያመለክተው ስለ ብልሀቱ ጥሩ ግንዛቤ እንዳላቸው ነው። በተቃራኒው መምህር -3 ለተማሪዎችን ግብረ መልስ ለመስጠት የተጠቀሙበት አተገባበር ተማሪዎችን የሚያነሳሳሳ ይሆን በራሳቸው እንዳይተማመኑና ትምህርቱን እድጠሉት የሚያደርግ ነው።
በአጠቃላይ በማንበብ ጊዜ መምህራኑ ባብዛኛው የተወሰኑ ተማሪዎች ድምጻቸውን እያሰሙ ተራበተራ እድያነቡ -..አልፎ አልፎ በለሆሳስና በቡድን እንዲያነቡ በቂ ነው የሚሉትን ጊዜ ይሰጣሉ። ይሁንና በዚህ ሂደት ተማሪዎች ሊጠቀሙባቸው የሚገቡ ብልሃቶችን በማስገንዘብ ተግባራቱን እንዲያከናውኑ በማለማመድ ማበረታታት ተገቢ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ በኩል ያላቸው ግንዛቤ አነስተገኛ ነው።

### 4.1.2.3 የድህረ ንባብ ብልሀቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ትንታኔ

በሰንጠረዥ 4.3 የሰፈረው መረጃ የጥናቱ ተሳታፊ መምህራን ደረህረ ንባብ ብልሃቶችን በክፍል ውስጥ ምን ያህል ተግባራዊ እዳደረጉ የሚሳይ ነው። በመሆኑም የመምህራኑን አተገባበርና የቃለ

መጠይቁን መረጃ በማዋሃድ በመምህራኑ ስለብልሃቶቹ አተገባበር ያላቸው ግንዛቤ እንደሚከተለው ተተንትኖዋል፡፡
በሰንጠረዥ የተገለጸው የመጀመርያው ብልሃት ግምትን ማገናዘብ ሲሆን ተማሪዎች በቅድመ ንባብም ሆነ በማንበብ ጊዜ ስለማንበቡ ይዘት የገመቱትን ምንባቡን አንብበው ሲጨርሱ ግምታቸው ትክክል እንደነበረና እንዳልነብረ ከነምክንያቱ እድገልጹ መጠየቅ ሲሆን ይህን ተግባር በቃለ መጠይቁ የተጋበዙት ስድስቱም መምህራን በምልከታ በታዩባቸው ክፍለ ግዜያት አንዳቸውም አልተገበሩትም፡፡ በቀደሙት የንባብ ደረጃዎችም እንደተገለጸው መምህራኑ ከመገመት ብልሃት ጋር ለሚገናኙ ተግባራት ግንዛቤ እንደሌላቸው ያሳያል፡፡

ተማሪዎች የቀረበውንም ንባብ ከቀደመው እውቀታቸውና ከተለያዩ ፍንጮች በመነሳት ምን ያህል እንደተገነዘቡት መገምገም የሚያስችል በመመስጠር /በአንድምታ የሚመለሱ ጥያቄዎችን በመጠየቅ በበኩልም መምህራኑ በአማካይ ተግባራዊ ያደርጉት አብዛኛውን (83%) በዝቅተኛ ደረጃ ነው፡፡ ይህም መምህራኑ ስለብልሀቱ አተገባበር ያላቸው ግንዛቤ ዝቅተኛ መሆኑን ያመላክታል፡፡ ተግባሩን ካከናወኑት መምህራን መካከል መምህር 4፤-ተማሪዎች ከምንባቡ ለወጡ ጥያቄዎች መላሽ እድሰጡ በሚደረግበት ጊዜ አለፎ አልፎ ሌሎች ተዛማችጅ የሆኑ ጥያቄዎችን የሚጠይቋቸው ለምን ይሆን; ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ሲሰጡ፡-ምንባቡን ምን ያህል እንደተገነዘቡት ለመረዳት ነው፡፡ የሚሳሳቱት ጥያቄ ካለ ምንባቡን እንደገና አንብቤ ለማስረዳት ነው፡፡

ከመምህሩ ምላሽ መረዳት የሚቻለው ተግባሩን ቢያከናውኑትም ለምን እዳከናወኑት ገንዛቤው ያላቸው አይመስልም፡፡
በአንጻሩም ንባቡ ከተነበበ በኀላ ተማሪዎች መረዳታቸውን መገምገም የሚያስችሉ በመማርያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡ ምንባብ ተኮር ጥያቄዎችን የመጠየቅ ተግባርን ከሌሎች ድህረ ንባብ ብልሃቶች ብልጫ ባለው ሁኔታ በአማካይ (36.7) ከፍተገኛና (63.3) በመካከለገኛ ደረጃ መተግበራቸው ብልሃቱን አዘውትረው እንደሚጠቀሙበትና ስለ አተገባበሩ የተሻለ ግንዛቤ እንዳላቸው ያሳያል፡፡ የቃለ መጠይቁ መረጃም ከዚሁ ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡

ተማሪዎች ምንባቡን ካነበቡ በኀላ ከምንባቡ ለወጡ ጥያቄዎች መልስ እድሰጡ ያደረጉት ለምንድ ነው? ;ለሚለው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ መምህር 1 ከምንባቡ ምን ያህል ጭብጥ እድያዙ ወይም እደትረዱ ለመገምግም ነው፡፡ ሲሉ መምህር 2 ደግሞ ከምንባቡ ለወጡ ጥያቄዎች መልስ መስጠት መቻል አለመቻላቸውን ለማወቅ ነው፡፡ ብለዋል፡፡ መምህር 3፤5 እና 6 ተመሳሳይ ተማሪዎች ምንባቡን ምን ያህል እደተረዱትና አዳልተረዱት ለማወቅ፡፡ ሲሉ መምህር -4 ተማርዎች የንባቡ

ሀሳብ ምን ያህል አደገባቸው ለማወቅ ሲሆን ሳልገባቸው ደግሞ አንብበው አድረዱ ለማድረግ ነው። ይህ ሆኖ ካልገባቸው እኔ ግልፅ እዳደርግላቸው ነው ብለዋል። መምህራኑ ከላይ ከቀረበው ብልሀት ተቀራራቢ በሆነ ሁኔታ የተገበሩት የተነበበውን ምንባብ ሀሳብ በራሳቸው አባባል እድያንፀባርቁ ማድረግ ነው። ይህም በአማካይ ( 23.3 ) በከፍተኛ (73.3) በመካከለኛ (3.3) በዝቅተና ደረጃ ተግብረውታል። ከዚህ የክፍል ምልከታ ደረጃ መገዘብ የሚቻለው መምህራኑ ስለብልሀቱ የተሻለ ግንዛቤ እዳላቸው ነው። በቅድመ ንባብ በንባብ በድህረ ንባብ ጊዜ ተማሪዎች ስእሎችን፤ ቻርቶችንና ሌሎች አጋጣሚዎችን በመጠቀም ስለሚያነቡት፤ እያነበቡት ስላለው ወይም አብበው ከጨረሱት በኋላ ስላነበቡት ጽሁፍ በአምራቸውም ስልምከሰት ከቀደመ እውቀታቸው ጋር እድያዋህዱት፤ ለወደፊትም በአምራቸው በመሳል ሀሳቡን ለዳግም ትውስታ እዳበቁት ለማድረግ በኩል መምህራኑ የሰሩት ስራ ዝቅተኛ መሆኑ ስለብልሀቱ አተገባበር ያላቸው ግንዛቤ ዝቅተኛ መሆኑን ያመለክታል በድህረ ንባብ ጊዜ ከመምህሩ አቀራረብ ብልሀቶች መካከል መምህራኑ በተሻለ የተገበሩት ተግባር ግብረ መልስና ማጠቃለያ መስጠት ሲሆን መምህራኑ በምልከታ በታየባቸው ክፍለ ጊዜያት በአማካኝ ከፍተኛ (13.3) መካከለኛ (53.3 ) እና ዝቅተኛ( 26.7) መተግበራቸው አባዛኛዎቹ መምህራን ስለብልሀቱ አተገባበር ግንዛቤ እዳላቸው የሚያሳይ ነው። በቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃም ከዚሁ ጋር ተመሳሳይነት አለው። ለአብነት ተማሪዎች ለጥያቄዎች ምላሽ ከሰጡ በኃላ እርሰወ አልፎ አልፎም ላሰጡ ነበር ይህን የተገበሩት ለምድንነው ለሚለው ጥያቄ መምህር 1 ተማሪዎች ያልጨበጡት ካለ በደንብ እድጨብጡት ግብረ መልስ ለመስጠት ነው። ሲሉ መምህር 4 ተማሪዎች ከተወያዩ በኃላ አዳንድ ቅር ያላቸው ጉዳዮች ካሉ ትምህርቱን ተጨባጭ ለማድረግ ነው።

መምህር- 5 ደግሞ ተማረዎች የመለሱት ምላሽ አጥጋቢ ሳይሆን ሲቀር እኔ አንጸባራቂ ለመመለስ ነው። ብለዋል። ከምላሻቸው መረዳት የሚቻለው ተማረዎች ምላሽ ነው የሚሉትን ከገለጹ በኀላ መምህሩ ግብረ መልስ መስጠት እንደሚገባው ግንዛቤ እንዳላቸ ነው። ይሁንና በምልከታዉ አንደታየው ግብረ መልስ አሰጣጣቸው በአብዛኛው ለሁሉም ተማሪ በጅምላና በቃል መሆኑ ግንዛቤያቸው በቂ ነው የሚባል አይደለም። የተማሪዎችን ተሳትፎ ማበረታታትን በተመለከተ መምህራኑ በአማካይ ከፎተኛ (10%)፣ መካከለኛ (40%) እናዝቅተኛ (46%) ተግብረዋል። ግማሹን ድርሻ በዝቅተኛ ደረጃ መተግበራቸውና (3.3%) አለመተግበራቸው አብዛኞቹ መምህራን ( ከመምህር-1 በስተቀር ) ስለ ብልሀቱ አተገባበር ያላቸው ግንዛቤ ዝቅተኛ መሆኑን ያሳያል።

የቃለ መጠይቁ መረጃም ከዚሁ ጋር ተቀራራቢነት አለው። ለምሳሌ፡-

መሞህረሽ-1: ተማሪዎች ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን በቡድን ሰርተው እንድያንጸባርቁ ካደረጉ በኀላ ለቡድኖቹ በተማሪዎችና በእርሰዎ ደረጃ እንድሰጥና እድጨበጨብላቸው ያደረጉት ለምንድን ነው? ለሚለው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ፡-የተወዳዳሪነት ስሜታቸውን ለማዳበርና ለትምህርቱ ሁሉም ተማሪዎች እድነሳሱ ለማድረግ ነው። ሲሉ መምህር-2፡ ተማሪዎች ለተጠየቁት ጥያቄ መልስ ነው

የሚሉትን ሲገልጹ እርሰዎ ጎበዝ ,ጥሩ ነው ይላሉ። ይህን የተገበሩት ለምን ይሆን? ለሚለው ምላሽ ሲሰጡ ተማሪዎች ጥያቄዎችን ለመመለስ ተሳታፊ እድሆኑ ነው። ብለዋል። ከዚህ መረዳት የሚቻለው መምህር -1 ተማሪዎችን ለማበረታታት የተጠቀሙበት አተገባበርም ሆነ ለቃለ መጠይቁ የሰጡት ምላሽ ስለብልሀቱ ግንዛቤ እንዳላቸው ያሳያል::

መምህር 2-በአተገባበራቸውም ሆነ ለቃለ መጠይቁ የሰጡት ምላሽ በቂ ሆኖ ባለመታየቱ ከዚህ ተግባር ጋር ሊጨመር የሚችል ተግባር አለ? ተብሎ ለቀረበላቸው ተጨማሪ ጥያቄ 'የለም' በማለት መልሰዋል:: ይህም መምህሩ/ሯ ግንዛቤያቸው ውስን እንደሆነ ያመልክታል::

የምልከታው መረጃ በሠንጠረዝ 4:3 እንደተመለከተው ተማሪዎች የሚያከናውኑትን ክትትል ማድረግና መገምገም ,ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማረዎች ድጋፍ በማድረግ በኩል የመምህራኑ የአተገባበር ሁኔታ ዝቅተኛ መሆኑ ግንዛቤያቸዉ ዝቅተኛ አንደሆነ ያሳያል::

በጥቅሉ ሲታይ መምህራኑ ስለ ድህረ ንባብ ብልሀቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ያላቸው ግንዛቤ በአንጻራዊ ከቅድመ ንባብና የንባብ ጊዜ ብልሀቶች አተገባበር የተሻለ እንደሆነ ያሳያል::

4.1.3 በአንብቦ መረዳት ብልሀቶች የክፍል ውስጥ ትግበራ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ተላውጦች

በዚህ ጥናት እንድመለስ የተነሳው የመጨረሻ ጥያቄ በመምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች የክፍል ውስጥ ትግበራ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ተላውጦች ምን ምን ናቸው? የሚለው ነው። ይህን ጥያቄ ለመመለስ ሶስት ልቅ የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች የቀረቡ ሲሆን የተገኘው መረጃ በአይነታዊ የትንተና ዘዴ እንደሚከተለው ቀርቧል።

በቃለ መጠይቁ በቀዳሚነት የቀረበው ጥያቄ፣ "የአንብቦ መረዳት ተግባራትን በክፍል ውስጥ ለመተግበር ያጋጠመዎት ችግር ቢገልጹልኝ።" የሚል ነው። ለዚህ ጥያቄ አብዛኞቹመምህራን በቀዳሚነት እንደችግር ያነሱት ተማሪዎች ለአንብቦ መረዳት ትምህርቱ ተነሳሽነት ማጣት፣ትኩረት አለመስጠት፣መረበሽ፣ወዘተ ናቸው።በማስከተልም በዚህ የክፍል ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎች ቁጥጥርና ክትትል የሚጠብቁ ናቸው፤በዚህም ላይ በአንድ ክፍል ውስጥ እስከ 40 የሚደርሱ ተማሪዎች የሚገኙበት ሁኔታ አለ፤አንዳንድ ወጣ ያሉ ተማሪዎችም ስላሉ መምህሩ እነሱን አስተካክሎ መማር ማስተማሩን ለማከናወን አስቸጋሪና ጊዜን የሚሻማ ነው በማለት ገልጸውታል።

ከጥናቱ ተሳታፊዎች መካካል መምህር-1 የተማሪዎችን የቀደመ እውቀትና የቋንቋ ችሎታ መለያት እንደ አንድ መሰረታዊ ችግር ጠቅሰዋል። መምህሩ/ሯ ሲያብራሩ፣ተማሪዎች በችሎታቸው በከፍተኛ፣በመካከለኛና በዝቅተኛ ደረጃ እንደሚመደቡ ይታወቃል። በመሆኑም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያሉ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችግር ስላለባቸው በትምህርቱ ከሌሎች ጋር እንዲራመዱ ለማድረግ አስቸጋሪ እንደሆነ ገልጸዋል።

በዚህ የቃለመጠይቅ ክፍል በሶስተኛነት የቀረበው ጥያቄ "የአንብቦ መረዳት ተግባራት የክፍል ውስጥ አተገባበርን በተመለከተ በትምህር ክፍልዎ(በድፓርመንትዎ) ከሚገኙ መምህራን ጋር የርስ በርስ የልምድ ልውውጥና አጫጭር ስልጠናዎችን ያደርጋሉ? የሚያደርጉ ከሆነ መጠኑን ቢገልጹልኝ (በተደጋጋሚ፣አልፎ አልፎ፣ከስንት አንዴ)። የሚያደርጉ ከሆነ ደግሞ ምክንያቱን ቢገልጹልኝ" የሚል ነው። ለዚህ ጥያቄ ከአብዛኞቹ መምህራን ምላሽ የተገኘው መረጃ የሚያመለክተው የልምድ ልውውጥ እንደማያደርጉ ነው። የተወሰኑት ደግሞ አልፎ አልፎ በአንድ ፈረቃ ከሚያስተምሩ መምህራን ጋር ሲገናኙ ወይም ለማስተማር ያስቸገራቸው ተግባር ሲኖር እንደሚነጋገሩ እና በመማር ማስተማር የይዘት ጥናት ላይ አንድ በሚያረጋቸው ሃሳብ ላይ የሚወያዩ መሆኑን ገልጸው ከዚህ የልቅ ትኩረት ሰጥተው የሚከናኙት በጋራ ፈተና ለማውጣትና በተማር ውጤት ላይ መገማገም ላይ  እንደሆነ ነው።

የልምድ ለውውጡን ለምነን እንዳላደረጉ የሰጡት ምክንያትም የመምህራኑ ቸልተኝነት፣እኔም እሱም (እሷም) ስለ በአድሱ የ9 ና 10ኛ መጽሀፍ ስልጠና ስላላገኘን የልምድ ልውውጥ ብናደርግም ጠቀሜታ የለውም ብሉ ማሰብ፣ስልጠና ካገኙት መምህራንም ነበር መምህርን በ1ኛ ደረጃ ምይታቸው ያገኙትን ልምድ መካከልም የሰለጠኑትን ለማካፈል ተነሳሽነት ማጣት፣ለመገናኘት ጊዜ የመስጠት ፍላጎት አለመኖር የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው።

በአጠቃላይ ከላይ የቀረበው የጥናቱ ውጤት ትንተና የጥናቱ ተሳታፊዎች የቅድመ ንባብ.የንባብ ጊዜና የድህረ ንባብ የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች የክፍል ውስጥ አተገባበርና ስለ አተገባበሩ ያላቸው ግንዛቤ ምን እንደሚመስል እንድሁም በትግበራ ጊዜ ያጋጠሟቸው ተግዳሮቶች ምን ምን እንደሆኑ ያመላከተ ነው።

ከመረጃው ጥልቅ ውጤት መረዳ የሚቻለው የአንብቦ መረዳት ትምህርቱ በክፍል ውስጥ ሲከናወን መምህራኑ፣ተማሪዎች ምንባን ለማበብ ከመሸጋገራቸው በፊት ምንባን ለምን አላማ እንደሚያነቡ፣እንዴት እንደሚያነቡና በተነሳሽነት እንድያነቡ የሚረዱ የቅድመ ንባብ ብልሀቶች የክፍል ውስጥ አተገባበርና ግንዛቤቻውም ቢሆን ከመጀመሪያው ደረጃ ብዙም የተለየ አይደለም፤ተማዎች ማንበባቸውን እንደከታተሉ የሚያስችሏቸውን ብልሀቶች እየተጠቀሙ እንድያነቡ በማስገንዘብ ረገድም ሆነ ለአንብቦ መረዳት ተግባራቱ ተገቢውን ልምምድ እንድያደርጉ በመጋበዝ፣ክትልና ድጋፍ በማድረግ በኩል የመምህራኑ አፈጻጸምና ግንዛቤ ዝቅተኛ ነው። በአንጻራዊ መምህራኑ ድህረንባብ ብልሀቶችን በተሸለ የተገበሩ ሲሆን በተለይ ተማሪዎች ምንባቡን ካነበቡ በኂላ የተማሪዎችን መረዳት ለመገምገም ከምንባቡ ለወጡ ጥያቄዎቸች ምላሽ እንድሰጡና ከምንባቡ የተገነዘቡትን በራሳቸው አባባል እንድያንጸባርቁ የማድረግ ብልሀቶችን አዘውትረው እንደሚጠቀሙባቸውና ግንዛቤው እንዳላቸው አመላክቷል። እንድሁም በመምህራኑ የአንብብ መረዳ

ብልሀቶች የክፍል ውስጥ ተግበራ ተፅዕኖ ያደረሱ ሁኔታዎች፡- የተማሪዎች ተነሳሽ አለመሆን፣ በተማሪዎች መካከል የቀደመ እውቀትና የቋንቋ ችሎታ መለያየት፣የመምህሩ ወቅታዊ ስልጠና አለማገኘት/በቂ አለመሆንና የርስበርስ የልምድ ልውውጥ ለማድረግ ተነሻሽነት ማጣት ተጠቃሽ መሆናቸውን ትንተናው ማመላከት ችሏል፡፡

## 4.2 የውጤት ማብራሪያ

የጥናቱ ዋና ዓላማ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርር ቤቶች የአማረኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሀቶችን የክፍል ውስጥ አተገባር መመርመር ነው፡፡ ዝርዝር ዓላመዎችን ለመፈተ በክፍል ምልከታና በቃለመጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች በመጠናዊ(በመቶኛ) እና በገለጻ ተተንትነዋል፡፡

የመጀመሪያው ዓላማ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሀቶችን በክፍል ውስጥ ምን ያህል ተግባራዊ እያደረጉ እንደሆነ መፈተሸ ሲሆን በውጤት ትንተናው መሰረት በቅድሚያ የታየው የቅድመ ንባብ ብልሀቶች አተጋባር ሁኔታ ነው፡፡ መምህራኑ የቅድመ ንባብ ብልሀቶችን በክፍል ውስጥ በFielding ና Pearson (1994) ዋቢ ከተደረጉት Dorkia (1978-1979) በአንብቦ መረዳት ትምህርት መምህራን ለቅድመ ንባብ ብልሀቶች ተግባራዊነት የሚሰጡት ትኩረትም ሆነ ያላቸው ግንዛቤ ዝቅተኛ መካከለኛና ከፍተኛ ቁጥር በጣም ያነሰ እንደሆነ በጥናቱ ከተገለጸው ሀሳብ ጋር ይደጋገፋል፡፡

ይህም በሠንጠረዥ 4.1 ስር ከቀረበና በ2.1.77 በ2፡2 100% በ3.1 ስር 73.3 መሆኑ የአተገባበሩ ሁኔታ እጅግ በጣም ዝቅተኛ መሆኑ በጥናቱ ከተገለፀው ሀሳብ ጋር ይረጋጋል፡፡

በተቃራኒ በአንብቦ መደራት ትምህርት የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት በመቀስቀስ/በመገንባት ስለምንባቡ አጠቃላይ መልዕክት አስቀድመው እንደገምቱ በመሳገንዘብና በመርዳት ምንባቡን በተነሳሽነት እንድያነቡና የአንብቦ መረዳት ጥረታቸው እንዳይደናቀፍ መምህራን የድርሻቸውን ሊወጡ እንደሚገባ  ለቀረበው ውጤት በገለፀው ክፍል መሆኑ ተገልጿል፡፡ ይህም ጠቅሶ በጥናቱ ውጤት ይኸ ተግባራዊ አለመደረጉና ውጤቱም ብልሃቶቹን አለመጠቀማቸውን እንደሚያሳይና ከነ Pearson ውጤት እንደሚስማማ ቢገለጽ ነው የሚሻል  ከHedge (1985) እና ከBensissan (1998) ጥናት ድምዳሜ ጋር ተደጋጋፊ ሆኖ አያሳይም፡፡ እንድሁም ከConley (1992)፣ ከDavis (2011)፣ ከAjibeh (2006)፣ ከTankersley (2005)፣ ከAloqaili (2012)፣ ከNega (2007) እና ከEphram (2009) ሀሳብ ጋር አይደጋገፍም፡፡ ይህም መምህራኑ ተማሪዎች ቅድመ ንባብ ብልሀቶችን በመጠቀም ምንባቡን በተነሳሽነት እንዲያነቡና የአንብቦ መረዳት ክሂላቸውን ማጎልበት እንዲችሉ ማስገንዘብና መረዳት የቻሉት በ74.8% በዝቅተኛ ሁኔታ እንደሆነ ሊያመላክት ይችላል፡፡

የትንተናው ውጤት በተጨማሪ መምህራን የንባብ ጊዜ የአንብቦ መረዳት ብልሀቶችን በክፍል ውስጥ ምን ያህል ተግባራዊ እንዳደረጉ የገለጎው ውጤት /አሃኑን ጥቅስ/ አሳይቷል፡፤ የተገኘው ውጤትም መምህራኑ ተማሪዎች የንባብ ጊዜ ብልሀቶችን በመጠቀም ማንበባቸውን በንቃት እየተከታተሉ የጸሀፊውን ሃሳብ እንድረዱ ማስገንዘብም ሆነ መረዳ የቻሉት በዝቅተኛ ሁኔታ መሆኑን አመላክቷል፡፡ ይህ ውጤት ከማስተዋል(1989) እና በFielding ና Pearson (1994) ዋቢ ከተደረጉት Dorkin (1978-1979) ጥናትና ውጤት ጋር ተደጋጋፊነት አለው፡፡

በታቃራኒው Kilerek ና Silberton (1997)፣ Ephram (2009)፣ Othman ና Zare (2013) እና Foley (2011) መምህራን ተማሪዎች ጽሁፉን አንብበው እንዲጨሪሱ  እድል መስጠት ብቻውን በቂ አለመሆኑን ሊረዱ ይገባል፤ይልቁን የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ብቃት እንድጎለብት በማስተማር ዘዴያቸውና አቀራረባቸው ተማሪዎች በተስማሚ የንባብ ብልሀቶች እየተለማመዱ የአንብቦ መረዳት ተግባትን እንድያከናውኑ ማበረታታት፣ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ወሳኝ እንደሆነ በጥናታቸው ከደረሱበት ድምዳሜ ጋ የተስማማ ሆኖ አልተገኘም፡፡ እንድሁም ከ Onthrio (2003)፣ ከHarvey (ዓ/የ)፣ ከTrehery ና Doctrew (2004) እና ከDavis (2011) ሀሳብ ጋር ተደጋጋፊነቱ ጎልቶ አልታየም፡፡ ይህም መምህራኑ ተማሪዎች ተስማሚ የንባብ ጊዜ ብልሀቶችን እንድጠቀሙ ማስገንዘብ፣ተገቢ ክትትል በማድረግ መቼ የትኛውን ብልሀት መጠቀም እንዳለባቸው፣መቼ የመምህር ወይም የጓደኛ እገዛ እንደሚያስፈልግ በመገንዘብ መርዳት የቻሉት በዝቅተኛ ሁኔታ መሆኑን ሊያመላክት ይችላል፡፡

ሌላው በጥናቱ ቀዳሚ ዓላማ ስር በውጤት ትንተናው  የታየው የመምህራን የድህረ ንባብ ብልሀቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ሁኔታ ምን እንደሚመስል ነው፡፡ በትንተናው የተገኘው ውጤት መምህራኑ በአንጻራዊ ድህረ ንባብ ብልሀቶችን በተሻለ ሁኔታ መተግበራቸውን አመላክቷል፡፡ በተለይ ተማሪዎች የተነበበውን ምንባብ መረዳታቸውን መገምገም የሚያስችሉ ምንባብ ተኮር ጥያቄዎችን መጠየቅ ተግባርን በትኩረት እንዲከናወኑት እንድሁም ተማሪዎች የምንባቡን ዋና ሃሳብ በራሳቸው አገላለጽ እንድያንጸባርቁ እድል የመስጠት ተግባርንም በተሸለ ሁኔታ ተግባራዊ ማዲረጋቸውን አሳይቷል፡፡ ይህም ውጤት በመምህራን ዘንድ ብዙ ጊዜ የተለመደው የአንብቦ መረዳት ትምህርት አተገባበር ተማሪዎች እንድ ጽሁፍ እንድያነቡ ከተደረገ በኋላ የቀረ ሀሳብ አለ፡፡ ያመላከቱት ነገር መገለጽ አለበት! ካመላከቱት ከይታያል (2003) እና በFieldingና Pearson (1994) ዋቢ ከተደረጉት Dorkin (1978-1979) የጥናት ውጤት ጋር እንድሁም ከማረው (1998) ሀሳብ ጋር ይደጋገፋል፡፡

የጥናቱ ሁለተኛው ዓላማ መምህራን ስለአንብቦ መረዳት ብልሀቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ያላቸው ግንዛቤ ምን እንደሚመስል ማመላከት ነው፡፡ በውጤት ትንተናው እንደተመለከተው መምህራኑ ስለአንብቦ መረዳት ብልሀቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ያላቸው ግንዛቤ ከአተገባበራቸው ሁኔታ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው፡፡ በመሆኑም መምህራኑ ስለ ድህረ ንባብ ብልሀቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር በተለይም ምንባቡ ከተነበበ በኋላ የተማሪዎችን አንብቦ መረዳት መገምገም የሚያስችሉ ምንባብ ተኮር ጥያቄዎችን በመጠየቅና ተማሪዎች ከምንባቡ የተረዱትን ዋና ሃሳብ በራሳቸው አባባል እንድገልጹ በመጋበዝ በኩል የተሻለ ግንዛቤ እንዳላቸው አሳይቷል፡፡ ይህ በድህረ ንባብ ምባባት ከተገኛ ውጤት አንፃር ሲታይ ምንባት ማስፈራራት መስፈርቱ የሰጡት ርዕስ ከላይና መካከል በተቃራኒው ተማሪዎች የቅድመንባብና የንባብ ጊዜ ብልሀቶችን እንዲጠቀሙ የማስገንዘብ፣አርአያ የመሆን እንድሁም ተገቢ ክትትትልና ድጋፍ የማድረግ ግንዛቤያቸው ዝቅተኛ መሆኑን አመላክቷል፡፤ ይህም ውጤት ይታያል (2003) እና Nega (2007) መምህራን ሲያከናውኑት የነበረው የአንብቦ መረዳት ትምህርት ጥንታዊ ዘዴ እንደሆነና ስለ አንብቦ መረዳ ትምህርት አተገባበር ያላቸው አረዳድ ዝቅተኛ መሆኑን ከጠቆሙት የጥናቱ ውጤት ጋራ ተደጋጋፊነት አለው፡፡ በተቃራኒው ግን የኔ ሰው (1990) እና እንግዳ (1992) ባካሄዱት ሙከራዊ ጥናት ድምዳሜ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሻሻል መምህራን በብልሀት የተደገፈ ትምህርት የመተግበር ግንዛቤ ሊኖራቸው እንደሚገባ ከተገለጸው ሀሳብ ጋር እምብዛም የሚደጋገፍ ሆኖ አልታየም፡፡ ይህም መምህራኑ ተማሪዎች ውጤታማ የአንብቦ መረዳት ብልሀቶችን እንድጠቀሙ ማስገንዘብና መርዳት የቻሉት በዝቅተኛ ሁኔታ መሆኑን ሊያመላክት ይችላል፡፡ ይህ ደግሞ በሠ.4.1 ከ4.1 44 ባሉት ምልከታ ነጥቦች ዝቅተኛ ከፈፃፀም መሆኑን 31 ያህሉ ተጠኝዎች ያስመዘገበት ውጤት ያሳያል፡፡

የጥናቱ ሌላው ዓላማ በመምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች የክፍል ውስጥ ትግበራ ተጽዕኖ የሚሳድሩ ተላዉጦችን ማመላከት ነው፡፡ በጥናቱ ውጤት ትንተና እንደተገለጸው፣የተማሪዎች ተነሳሽነት ማጣት ለአንብቦ መረዳት ትምህርቱ ትኩረት አለመስጠት፣ በአንብቦ መረዳ ብልሀቶች/ተግባራት የክፍል ውስጥ አተገባበር ተጽዕኖ አሳድሯል፡፡ ይህም ውጤት በGuthraና ሌሎች(2006) ጥናት ከተገለጸው ሀሳብ ጋር ተዛምዶ ታይቷል፡፡

የተማሪዎች የቀደመ እውቀትና የቋንቋ ችሎታ መለያየት የአንብቦ መረዳት ብልሀቶችን/ተግባራትን በክፍል ውስጥ ለመተግበር ሌላው አሉታዊ ተጽዕኖ አድራሽ መሆኑ የውጤት ትንተናው ጥቆማ ሰጥቷል፡፡ ይህም ውጤት Androwed (1987) እና Fielding ና Person (1994)ን ዋቢ በማድረግ Threhery ና Doctrew (2004) በአንድ መማሪያ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች የተለያየ ዳራዊ

እውቀትና የቋንቋ ችሎታ ስለሚኖራቸው አስቀድሞ መፈተሸ ካልተቻለ ተጽዕኖ ሊፈጥር እንደሚችል ከተገለጸው ሀሳብ ጋር ይደጋገፋል፡፡

ይህ ለአንፃራዊነት መምህራን የተማሪዎቻቸውን የቀደመ ዳራዊ ዕውቀት ፈትሾ ወደ ትምህርት አለመግባት ባንብቦ መረዳት ላይ ተጽኖ ማሳየቱ ጥናቱ ተቁሟል፡፡ መምህራን ወቅታዊ ስልጠና አለማገኘታቸውና የስልጠና እድል አለ ማግኘታቸውና ፣በተመሳሳይም መምህራኑ የርስበርስ የልምድ ልውውጥ የማድረግ ተነሳሽነት አለመኖር ሌላው ተጽዕኖ አድራሽ እንደሆነ የጥና ውጤት አሳይቷል፡፡ ይህም በNega (2007) ጥናትና ውጤት፣በመምህራን መካከል የአንብቦ መረዳ ብልሀቶች የጽንሰ ሀሳብና የአተገባበር ልዩነት መታየቱንና ይህን ልዩነትለማጥበብ መምህራን ተከታታይ ሙያዊ ስልጠና እንድያገኙና ከጓደኞቻቸው ጋር የርስበርስ የልምድ ልውውጥ እንድያደርጉ ምቹ ሁኔታ መፍጠር ካልተቻለ ተጽዕኖማሳደሩ እንደማይቀር ከተጠቆመው ሀሳብ ጋር ይደጋገፋል፡፡ ባጠቃላይ ከጥናቱ ተጽእኖ ያሳደሩ ሁኔታዎች መኖራቸውን የጥናቱ ውጤት ጠቁሟል፡፡ በመሆኑም መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሀቶችን በክፍል ውስጥ ውጤታማ በሆነ መልኩ መተግበር እንዳልቻሉ ሊያመላክት ይችላል፡፡ ለዚህ አሁን በ2ኛ ደረጃ የተጀመሩት የለስንስተዲ / የይዘት ጥናት/ እንዲጠናከሩ ማድረግ ሲቻል በየት/ቤቱ የሚታዩት እንቅስቃሴና ለማየት ተችሏል፡፡ በጥቅሉ የዚህ ጥናት ውጤት በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማረኛ ቋንቋ መምህራን በተለይ የቅድመንባብና የንባብ ጊዜ የአንብቦ መረዳት ብልሀቶችን ተማሪዎች በክል ውስጥ እየተጠቀሙ የአንብ መረዳት ክሂላቸውን እንድያጎለብቱ አርአያ መሆን፣ማስገንዘብና መርዳት የቻሉት በዝቅተኛ ሁኔታ መሆኑን አሳይቷል፡፡ እንድሁም በመምራኑ የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች የክፍል ውስጥ ትግበራ ተጽዕኖ ያሳደሩ ተላውጦች መኖራቸውን ጠቁሟል፡፡

# ምዕራፍ አምስት፡-

# ማጠቃለያ መደምደሚያና መፍትሄ

## 5.1 ማጠቃለያ

የጥናቱ ዓብይ ዓላማ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የ9ኛ እና 10ኛ ክፍል የአማረኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሀቶችን የክፍል ውስጥ አተገባር መመርመር መሆኑ በቀዳሚዎቹ ምዕራፎች ተገልጽዋል፡፡ በዚህ መሰረት ሊመለሱ የታሰቡት መሰረታዊ ጥያቄዎች የሚከተሉት ነበሩ፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በተለይ ደግሞ በ9ኛ እና 10ኛ ክፍሎች፡-

1. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሀቶችን በክፍል ውስጥ ምን ያህል ተግባራዊ ያደርጋሉ?
2. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለአንብቦ መረዳት ብልሀቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ያላቸው ግንዛቤ ምን ይመስላል?
3. በመምህራን የአንብቦ መረዳ ብልሀቶች የክፍል ውስጥ ትግበራ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ላውጦች ምን ምን ናች? የሚሉት ናቸው፡፡

እነዚህን መሰረታዊ ጥያቄዎች በአግባቡለመመለስ እንድቻል በመጀመሪያ የጥናቱ ተሳታፊዎችና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ተመርጠዋል፡፡ የጥና ተተኳሪዎች በደቡብ ወሎ ተንታ እና መቅደላ ወረዳ ከሚገኙ አምስት( የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች መካከል በአመቺ ጠቅላይ አመራረጥ ዘዴ(convenience sampling) አስፋወሰን፣አጅባር፣ደበቅ፣ወርጠጅናመቅደላ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ተመርጠዋል፡፡ በነዚህ ትምህርትቤቶች ካሉት የክፍል ደረጃዎች ጠቅላይ የናሙና አመራረጥ ዘዴ (purposive sampling) የ9ኛና 10ኛ ክፍል የተመረጠ ሲሆን በዚህ የክፍል ደረጃ በ2012-2013ዓ.ም አማረኛ ቋንቋ ትምህርት በማስተማር ላይ የሚገኙ መምህራን በጠቅላይ ናሙና አመራረጥ ዘዴ ( comprehensive sampling) ሁሉም 31 የጥናቱ ተሳታፊዎች ሆነዋል፡፡ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ምልከታና ቃለመጠይቅ ናቸው፡፡

የጥናቱ ዋና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ምልከታ ሲሆን 9ኛ ና 10ኛ ክፍል የአማረኛ ቋንቋ የመምህርና የተማሪ መጽሀፍት በማየት የጥናቱ ተሳታፊዎችን የቅድመንባብ፣የንባብ ጊዜና የድህረንባብ የአንብቦ መረዳት ብሀቶችን የክፍል ውስጥ አተገባበር ሁኔታ በመገምገም የጥናን መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመፈተሽ የሚያስችል ቅጽ ተዘጋጅቷል፡፡ ቅጹ ለጥናቱን መረጃ መሰብሰቢያነት ከመዋሉ በፊት የምርምር ልምድ ባላቸው ሰዎችና በጥናቱ አማካሪ ተገምግሞ

ማስተካከያ ተሰጥቶበታል፡፡ ከዚያም በሙከራ ጥናት ተፈትሾ በእያንዳንዱ መምር ሁለት ክፍለ ጊዜ ምልከታ በማካሄድ ለመረጃ መሰብሰቢያነት ውሏል፡፡

የጥናቱ ሁለተኛ መረጃ መሰብሰቢያ ቃለመጠይቅ ሲሆን በክፍል ውስጥ ምልከታ የተገኘውን መረጃ ለማመሳከርና ተጨማሪ መረጃ ለማገኘት ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ቃለመጠይቁ ምልከታውን መሰረት በማድረግ አስቀድመው ያልተወሰኑ የግንዛቤ መመዘኛ ጥያቄዎችና መምህራኑ ብልሀቶችን በክፍል ውስጥ ሲተገብሩ ያጋጠሟቸውን ችግሮች የሚያመላክቱ 5 ጥያቄዎች ቀርበው መረጃው ተሰብስቧል፡፡ በመቀጠልም በምልከታውና በቃለመጠይቁ የተሰበሰቡት መረጃዎች በማዋሀድ በመጠናዊ(በመቶኛ) እና በአይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች ተተንትነዋል፡፡

የጥናቱ ውጤትም ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የ9ኛእና 10ኛ የአማረኛ ቋንቋ መምህራን የቅድመ ንባና የንባብ ጊዜ የአንብቦ መረዳት ብልሀቶችን በክፍል ውስጥ ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ በአጠቃላይ የምልከታ ውጤት ዝቅተኛ መሆኑን፣ በንጽጽር ድህረ ንባብ ብልሀቶችን በተሸለ ሁኔታ መተግበራቸውን አመላክቷል፡፡ በተመሳሳይ መምህራኑ ስለ ቅድመ ንባብና የንባብ ጊዜ የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ያላቸው ግንዘቤ ዝቅተኛ እንደሆነ በምልከታና በቃለመጠይቅ የተገኘው ውጤት አሳይቷል፡፡ እንድሁም በመምህራኑ የአንብቦ መረዳ ብልሀቶች የክፍል ውስጥ ትግበራ ተጽዕኖ ያሳደሩ ተውላጦች መኖራቸው በቃለመጠይቅ የተገኘው ውጤት አመልክቷል፡፡ ጥቅል ሲታይ የመምህራን ወቅታዊ ስልጠና አለማገኘት/በቂ አለመሆን፣መምህራን የርስበርስ የልምድ ልውውጥ ለማድረግ ተነሳሽነት ማጣት፣የተማሪዎች

የቀደመ እውቀትና የቋንቋ ችሎታ መለየት እና አንዳንድ ተማሪዎች ለአንብቦ መረዳት ትምህርቱ ተነሳሽነት ማጣት ጎልተው ታይተዋል፡፡

## 5.2 መደምደሚያ

የጥናቱን ውጤትና ማብራሪያ መሰረት በማድረግ ከሚከተሉት መደምደሚያዎች ላይ ተደርሷል፡፡ በመሆኑም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ማለትም በአስፋወሰን፣በደበቅ፣በአጅባር፣በወርጠጅ እና መቅደላ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የ9ኛ እና 10ኛ ክፍል ፡-

1. የአማረኛ ቋንቋ መምህራን በአንብቦ መረዳት ትምህርት ተማሪዎች ውጤታማ የአንብቦ መረዳት ብልሀቶችን እንድጠቀሙ አርአያ መሆን፣ማስገንዘብና መርዳት የቻሉት በዝቅተኛ ሁኔታ ነው፤በተለይ የቅድመ ንባብና ጊዜ የአንብቦ መረዳት ብልሀቶችን (በአብዛሀኛው) በክፍል ውስጥ ተግባራዊ እያደረጉ አይደለም፡፡ ይህም መምራኑ፣ ተማሪዎች ውጤታማ የአንብቦ መረዳት ብልሀቶችን እየተጠቀሙ የአንብቦ መረዳት ክሂላቸውን እንድያጎለብቱ በክል

ውስጥ ተግባራዊ ከማድረግዎ አኳያም ሆነ ስለአተገባበሩ የግንዛቤ ውስንነት/አለመኖር ስለሚታይባቸው ግንዛቤ ሊፈጠርላቸው ይገባል የሚል አንድምታ አለው።

2. በመምህራኑ የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች የክል ውስጥ ትግበራ ተጽዕኖ ያደረሱ ተላዉጦች፦ መምህራን ወቅታዊ ስልጠና አለማገኘታቸው/በቂ አለመሆን፣ ከሙያ አጋሮቻቸው ጋር የርስበርስ የልምድ ልውውጥ በማድረግ ግንዛቤያቸውን ለማሻሻል ተነሳሽ አለመሆናቸው፣የተማሪዎች የቀደመ እውቀትና የቋንቋ ችሎታ መለያት እንድሁም አንዳንድ ተማሪዎች ለአንብቦ መረዳት ትምህርቱ ያላቸው ተነሳሽነት ዝቅተኛ መሆን በዋናነት ተጠቃሽ ናቸው። በመሆኑም የተማሪዎችን አንብቦ መረዳት ችሎታ ለማዳበር እነዚህ ተግዳሮቶች ሊቀረፉ ይገባል።

## 5.3 መፍትሄ

ከጥናቱ ውጤትና ድምዳሜ በመነሳት የሚከተሉት የመፍትሄ ሃሳቦች ተሰንዝረዋል።

1. ለጥናቱ የተመረጡ የክፍል ደረጃ  የተዘጋጀው የአማረኛ ቋንቋ መጽሀፍ የአንብቦ መረዳት ትምህርት ተግባራት/ብልሀቶች አቀራረብ ከዚህ በፊት ከነበረው መጽሀፍ የተለየ ነው። በመሆኑም መምህራኑ ይህን በውል በመረዳት ተከትለው እንድስሩ፣ከዚህ በፊት ስልጠና ያልወሰዱትም ሆኑ የወሰዱት መምህራን የክፍል ውስጥ መማር ማስተማሩ እየተከናወነ በተግባር የተደገፈ ስልጠና በስፋትና በጥልቀት ቢወስዱ፣ ተማሪዎች ውጤታማ ብልሀቶችን እየተጠቀሙ የአንብቦ መረዳት ክሂላቸውን እንድያጎለብቱ በክፍል ውስጥ ተግባራዊ ከማድረግ አኳያም ሆነ ስለ አተገባበሩ  የተሸለ ግንዛቤ ያገኛሉ።
2. የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ማለትም የ9ኛ እና 10ኛ ክፍል የአማረኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች የክፍል ውስጥ አተገባበርና የመምህራኑን ተነሳሽነት በተመለከተ ወደፊት ጥናት ቢካሄድ እና ለተሻለ የመማር ማስተማር ስራ እገዛ የሚያደርግ ልዩ ልዩ ስልጠናዎች ቢሰጡ የተሻለ አተገባበርና ግንዛቤ ሊገኝ ይችላል።

# ዋቢ መፅሐፍት


ማስተዋል ውበቱ፡፡

/1989/፡፡ "የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ፣ በአዲስ አበባ በሚገኙ አራት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ላይ ተካሄዶ ጥናት " በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለማስተማርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት ፡፡ /ያልታተመ/

ማረው አለሙ፡፡

/1998/፡፡ የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ፡፡ አዲስ አበባ ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

ተክላይ ትእዛዙ፡፡

/2000/፡፡ "በትግርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የስምንተኛ ክፍልና የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ንባብ ጊዜ የንባብ ብልሀት አጠቃቀምና የመምህራን ግንዛቤ ተጣጥሞ ፍተሻ ፣ በአክሱም ከተማ 1ኛ ደረጃና 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መነሻነት"በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለማስተርስ ዲግሪ የቀረበ ጥናት፡፡ /ያልታተመ/

እንግዳ ዘውዴ፡፡

/1002/፡፡ የ"ቶፐዳውን" (Top-down) የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር ያለው ተግባራዊነትና ውጤታማነት ፣ በዘጠንኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፣ ለማስተርስ ዲግራ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡ /ያልታተመ/

እንድሪስ አባይ፡፡

/2000/፡፡ "የአንብቦ መረዳት ብልሀቶችን መማር ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለው ተካምዶ፡፡" በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ ለድህረ ምረቃ ፕሮግራም የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ፡፡ /ያልታተመ/

የኔሰው ደሴ፡፡

/1990/፡፡ "በኦሮምኛ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች አማርኛ አንብቦ የመረዳት ክሂላቸውን ለማዳበር ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል በክፍል ውስጥ ተጠቅሞ ማስተማር ያለው አስተዋጽኦ"በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፣ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡ /ያልታተመ/

ይታያል ወርቁ።

/2003/።”የንባብ ትምህርት አተገባበር ግምገማ በቡለን ወረዳ በተመረጡ ሦስት አንደኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤቶች በስምንተኛ ክፍል ተተኳሪነት ” በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፣ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት። /ያልታተመ/

Ajideh, P. (2003). *Schema theory-based pre-reading tasks: A neglected essencial in the ES! reading class.* The Matrix Vol. 3, no. 1.

Ajideh, p. (2006). *Schema theory based consideration on pre-reading activities in ESP text book* : The Asian EFL journal teaching articles, Vol. 16

Alfassi, M. (1998). *Reading for meaning: The efficacy of reciprocal teaching in fostering reading comprehension in high school students in remedial reading classes.* BaP Ilan University, Israel. Vol. 35, no. 2.

Aloqaili, A.S. (2012). *The relationship between reading comprehension and critical thinking: A theoretical study*, Journal of King Saud University-Language And Translation. Retrieved from WWW.Sciencedirect.com

Bens1ssan, M. (1998). *Schema effects in EFL reading comprehension.* University ef Haifa, Israel. Vol. 21, Issue 3.

Block, E. (1986). *The comprehension strategies of second language readers.* TESOL. Quarterly, 20, 463-494.

Bloc, C.C. (1997). *Teaching the language arts: Expanding thinking through student centerd.* Boston: Allyn & Bacon.

Conley, M.W. (1992). *Content reading inst uction: Communication approach.* New York: Mc Graw-Hill.

C & I. (2010). *Reciprocal teaching and reading comprehension.* Univerity of Western Illinois.

Davis, A. (2011). *Building comprehension strategies for the primary years.* Eleanor Curtain Publishing. Level1. Cuite 3.

Deighton, L. (1971). *Incyclopedia of education.* The Macmillan: Company the free press.(12).

Denton & etal. *(2-KE.ffective instruction for middle studnts with reading difficulties:The reading teachers sourcbook.* University of Texas system/Education Agency.

Ephram, K. (2009). *Reading comprehension instruction for expositori text in elementary education.* Liberty University.

Feeters & etal. (2011). *An exploration of strategy: Based reading instruction using ?expositors science texts in the elementary grades.* Vol. 2, no. 2.

Fielding, L. & pearson, P. (1994). *Reading comprehension: What works.* Vol. 51, no. 5.

Foley, L.S. (2011). *Exploring K-3 teachers ' implementation of comprehension strategy instruction (CSI) using expectancy-value theory:* Literacy Research And Instruction, 50(3), 195-215.

Gray, A. (2008). *Constructivist teaching and learning.* Retrieved from http:!/WWW .saksschoolboards.c a/old//Reaserch And Development/ Instruction/. 097-07

Gray, D. E. (2004). *Doing research the real world.* SAGE Publication Ltd. London.

Gove, A. & Wetterberg, A. (2011). *The early grade reading assessmen: Applications andinterventions to improve basic literacy.* RTI Press publication.

Gra', N. (1987). *Making the most of your textbook.* London: Lpngman.

Guthri, T. & etal. (2006). *Influences of stimulating tasks on reading motivation andcomprehension.* University of Mary land. Vol. 99, no. 4.

Harvey, M. (n.d). *Reading comprehension strategies for elementary and secondary school students.* Lynchburg College.

Hedge, J. (1985). *Using readers in language teaching.* London: Macmillan PublishersLtd.

Hill, C. (2011). *An examination of second language reading research and implicationsfor English language teaching practices.* The Arbutus review, vol. 2, no. 1.

Johnson, A.P (2008). *Teaching reading and writing: Aguidebook for tutoring and 'remediating students.* J\Jew York.

